# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 3ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ግሩም ጥበቡ

ከበደ አየለ

**አርታኢዎች**

እሸቱ አጋ

አንበሴ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምሥል ገለጻ**

ጆናታን ግርማ

© የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

# ማዉጫ

**ይዘት** **ገጽ**


ማዉጫ.......iii

ምዕራፍ አንድ ጤና.......1

ምዕራፍ ሁለት ጎረቤታሞች.......17

ምዕራፍ ሶስት ስነቃል.......31

ምዕራፍ አራት የጊዜ አጠቃቀም.......44

ምዕራፍ አምስት መጓጓዣ.......59

ምዕራፍ ስድስት ስነምግባር.......72

ምዕራፍ ሰባት ግብርና.......85

ምዕራፍ ስምንት ስራ.......99

ምዕራፍ ዘጠኝ ባህል.......114

ምዕራፍ አስር ገበያ.......128

መርሀ ትምህርት.......140

## መግቢያ

ይህ 'የመምህር መምሪያ' የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀውን 'የተማሪ መፅሐፍ' መሰረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች እንዴት ማስተማርና ተግባራቱን (መልመጃዎቹን) እንዴት ማሰራት እንደሚገባ ሁኳቀፍ የሆነ ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ያስቀምጣል። በዚህም መምህራን የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መፅሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መፅሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካትተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎችም ናሙና መልሶች እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ አማራጭ ምላሾች የቀረቡትም በቋንቋ ትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሂያድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህርና ተማሪዎቹ እንደየ ሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

## ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች

- የየትኛውም ክፍለ ጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነ (በተቀናጀ) መልኩ ያካተተ ሊሆን ይገባል
- የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴን መርህ የተከተለ ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ ተማሪን ማዕከል ያደረገ መሆን)
- የልስራ፣ እንስራ ስሩ አካሄድ ሁልጊዜም ይተግበር፣ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ (መልመጃ) ሲቀርብ ሊተገበር ይገባል
- ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaffolding) በመተግበር ማገዝ ያስፈልጋል

- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የአካቶ ትምህርትን መርህ በመከተል ተገቢ እገዛ ያድርጉላቸው፤
- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጀን በመምጣት ማትጋት ይገባል
- በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባናል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ ወዘተ አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት ይ

# ምዕራፍ አንድ

## ጤና

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው መልሰው እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎቹ ለደረጃው የሚመጥኑ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱና የመሰረቷቸውንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚታወስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- አዳምጠው የቃል ዘገባ ያቀርባሉ፣
- የቀረበ ምንባብን አቀላጥፈው ያነባሉ፣
- ምንባብን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣
- ከምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፣
- አያያዦችን ለይተው በአረፍተ ነገር ምስረታ ወቅት ይጠቀማሉ፣
- አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ምንባቡን ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- ተራን እየጠበቁ ለመናገር ማዳመጥ

### 2.3. መናገር

- የራስንና የአካባቢ ንፅህናን ስለመጠበቅ መናገር
- ጤናማ መሆን የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ማስረዳት
- ጤናማና ጤናማ ስላልሆኑ ሰዎች መገለጫዎች መዘርዘር

### 2.4. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ

### 2.5. ቃላት

- የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍቺ መፈለግ
- የቃላትን አገባባዊ ፍቺ መፈለግ
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም

### 2.6. መፃፍ

- ቃላትን አገጣጥሞ አረፍተነገር መመስረት
- የተሰጡ ቃላትን በመንተራስ አረፍተነገሮችን መመስረት
- አጫጭር አረፍተነገሮችን መፃፍ

- የአረፍተነገር ተዋቃሪዎችን በትክክለኛው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ።

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ጤናማና ደስተኛዋ ደራርቱ

- በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች አዳምጠውና ያዳመጡትንም መሰረት አድርገው የቃል ዘገባ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል

### ክፍለጊዜ አንድ

### ቅድመማዳመጥ

ምንባቡ ስለምን እንደሆነ እንዲገምቱ መጠየቅ፣ የሁለት ወይም የሦስት ተማሪዎችን ምላሽ መቀበል፤ ስዕሉን እንዲመለከቱ መጋበዝ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ጽዳታቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ፣ ራሳቸው ጤናማ ሆነው ለመገኘት ምን ምን እንደሚያደርጉ ወይም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እንደሚያምኑ የየራሳቸውን ምላሾች እንዲሰጡ (እጅ በማስወጣት ወይም ተራ ቁጥር በመጥራት ወይም አቀማመጣቸውን መሰረት በማድረግ መጋበዝ፤ እዚህ ጋር ልክ ወይም ልክ ያልሆነ ምላሽ አይኖርም ሁሉም የየራሱን ልምድ ስለሚያጋራ!)
2. ተማሪዎች ጤናማ ሆነው ለመገኘት ምን እንደሚያደርጉ ልምዳቸውን እንዲናገሩ መጋበዝ (አመጋገብ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ኳስ፣ ዋና፣ ሩጫ) (ከአምስት ደቂቃ ያልበለጠ)

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እነዚህ ጥያቄዎች ምንባቡ ውስጥ የሚገኙና ምንባቡ እየተነበበ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሲሆኑ በያዙት ቅደም ተከተል መሰረት ይጠየቃሉ። የሚጠየቁትም ምንባቡ በመጀመሪያ ጊዜ ሲነበብ ይሁን።

**መምህር እባክዎትን ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ይህንን ምንባብ ተገቢውን ፍጥነትና አገላለፅ በመከተል ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው።**

## ጤናማና ደስተኛዋ ደራርቱ

ደራርቱ ሁልጊዜ ደስተኛና ጤናማ ሆና የምትታይ ልጅ ናት። ደራርቱ በሰፈሯ ወስጥ የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ ትታወቃለች። አትክልት፣ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬና የእንስሳት ተዋፅዖዎች የደራርቱ የተለመዱ ምግቦች ናቸው።

*1. ደራርቱ የምትመገባቸው የምግብ አይነቶች ________፣ ________ እና ________ ናቸው፡፡*

በተጨማሪም ደራርቱ የግል ንፅህናዋን ዘወትር ትጠብቃለች። ከምግብ በፊትና በኋላ እጆቿን በሳሙናና በውሃ ትታጠባለች፤ ጥርሷን ታፀዳለች፤ በሳምንት ሦስት ጊዜ ሰውነቷን ባግባቡ ትታጠባለች።

*2. ደራርቱ እጆቿን ከምግብ ________ እና ________ በሳሙናና በውሃ ትታጠባለች፡፡*

ከዚህም ሌላ ደራርቱ ጤንነቷን ለመጠበቅ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ትሰራለች። በዚህም ሩጫ፣ መረብ ኳስና እግር ኳስ ሁልጊዜም የምትመርጣቸው ጨዋታዎቿ ናቸው።

3. ደራርቱ ጤንነቷን ለመጠበቅ የምትሰራቸው አካላዊ እንቅስቃሴዎች ________፣ ________ እና ________ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ ተግባራት ደራርቱን ጤናማና ደስተኛ አድርገዋታል። ከዚህም ባሻገር በትምህርቷ ጎበዝ እንድትሆንና በጓደኞቿና በአካባቢዋ ማህበረሰብ ዘንድ ተወዳጅነትን እንድታገኝ አስችለዋታል።

የማዳመጥ ተግባሩ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀረው ጊዜ ተማሪዎች ታሪኩን (ስለጤናማዋና ደስተኛዋ ደራርቱ) መልሰው በቃል እንዲናገሩ ማድረግ፣ ለዚህም በቡድን ወይም በጥንድ ማቧደንና አፈፃፀሙንም መከታተል፣ ድጋፍ ለሚሹት ድጋፍ ማድረግና የሚነሱ ጥያቄዎች ካሉ እያሳተፉ በጋራ መስራት

## ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ ስለጤናማዋና ደስተኛዋ ደራርቱ የተወሰኑ ነጥቦችን በክለሳ መልክ እያስታወሱ እንዲናገሩ በመጋበዝ ይጀምሩ። ቀጥሎም መልመጃዎቹን እያነበቡ በትእዛዛቱ መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ። (አማራጭ መልሶቹ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ቀርበዋል።)

ጥያቄዎቹ እንደየክፍሉ ተጨባጭ ሁኔታ መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ በጥንድና መጨረሻም ከቡድን ውይይት በኋላ በተወካይ አማካኝነት ሊመለሱ ይችላሉ።

## ክፍለ ጊዜ ሦስት

### መልመጃ ሁለት

ክፍለ ጊዜውን ሁለት ወይም ሦስት ተማሪዎች 'የጤናማዋና ደስተኛዋ ደራርቱ'ን ታሪክ በቃል እንዲያቀርቡ በመጠየቅ ማስጀመር ይቻላል።

- የቀረቡትን ቃላት ወይም የምንባቡን ታሪክ ተጨባጭ የሚያደርጉ (ለምሳሌ የጤናማ ልጅ ምስልን) መርጃዎችን አዘጋጅቶ ወይም ተውሶ መምጣትና መጠቀም።
- የተሰጡትን ቃላት ሰሌዳ ላይ መፃፍ፣በታሪኩ ውስጥ ያሉበትን አረፍተ ነገር እየመረጡ ማንበብና ፍቻቸውን ከአውዱ እንዲሰጡ ማበረታታት።
- በመጨረሻም የተሻለ የሆነውን ፍቺ ሰሌዳ ላይ መፃፍና ያንንም መሰረት አድርገው ተማሪዎቹ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲፅፉ ማበረታታት፣
- ሲሰሩ እየተዘዋወሩ መቃኘት፣ የሰሩትን በመመልከት እርማትና ምጋቤ ምላሽ መስጠት።

## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎቹ ሀሳብ እንዲለዋወጡ የሚያስችሉ ተግባራት ተካትተው ቀርበዋል። እባክዎ መምህር ሁሉም ተማሪዎች በቀረቡት ተግባራት ላይ መሳተፋቸውንና የመናገር እድሉን ማግኘታቸውን ክትትል እያደረጉ ያረጋግጡ።

## ተግባር አንድ

- ተማሪዎችዎን አምስት ወይም ስድስት ስድስት እያደረጉ ያቧድኑ፤
- ከዚያም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ (አንድ ሰው ጤና አጣ የሚባለው ምን ሲሆን እንደሆነ) ሀሳብ እንዲያዋጡ ያበረታቱ፤ ለደቂቃዎች (ለምሳሌ 10 ደቂቃ) ከተወያዩ በኋላም
- ሁለት ሁለት ተወካዮች ከየቡድኑ ጉዳዩን አስመልክቶ የቃል ዘገባ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያበረታቱ
- የቃል ዘገባው ሲቀርብ የሚነሱ ነጥቦችን ተጨባጭነትና የሀሳብ ፍሰትን ይመዝኑ፤ እንዳስፈላጊነቱ ምጋቤ ምላሽ ይስጡ
- በመጨረሻም ስለቀጣዩ ተግባር መመሪያ ያቅርቡ (እባክዎ ተግባር ሁለትን መረጃ አሰባስበው እንዲሰሩት አስቀድመው ይንገሯቸው)

## ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር ሁለት

- እባክዎ መምህር ሁሉም ተማሪዎች የተባሉትን መረጃ ጠይቀው ስለመምጣታቸው ያረጋግጡ።
- ከዚያም ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ተራበተራ እየተነሱ ጤናማ ያልሆነ ሰው ምን ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሙት እንዲናገሩ ያድርጉ (በአቀማመጥ ወይም በተራ ቁጥር ቅደም ተከተላቸው መሰረት፤)
- የቃል ዘገባው ሲቀርብ ማን የተሻለ እንዳቀረበ ይመዝኑና ድጋፍ የሚሹ ካሉም እየለዩ ተገቢውን እገዛ ይስጧቸው፤ ስለተማሪዎችዎ አፈጻጸምም ማስታወሻ ይያዙ
- በመጨረሻም እርስዎ ጉዳዩን አስመልክቶ የማጠቃለያ ሀሳብ ያቅርቡ

## ክፍለጊዜ ስድስት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## የተመጣጠነ ምግብ

## በንዑስ ትምህርት ክፍሉ የሚበቁ ውጤቶች

- ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ በትክክል አንብበው ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

- የቀረበውን ምስል እያዩ የሚያውቋቸውን የምግብ አይነቶች እንዲናገሩ መጠየቅ፤ የሦስት ወይም አራት ተማሪዎችን መልስ መቀበል
- ለመኖር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ልምዳቸውን መሰረት አድርገው እንዲናገሩ መጋበዝ፤ የተወሰኑ ተማሪዎችን ምላሾች መቀበል

## የንባብ ጊዜ

- ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ መጋበዝ፤ አፈፃፀሙንም እየተዘዋወሩ ምልከታ በማድረግ መከታተል
- የንባብ ጊዜ ጥያቄዎቹንም እያነበቡ እንዲመልሷቸው ማሳሰብ
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምንባቡን አንዴ በሞዴልነት ማንበብ

## ክፍለጊዜ ሰባት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

- በየቡድናቸው ሆነው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን እንዲሰሯቸው ማበራታት
- እንደስልትም ወደኋላ ተመልሰው ምንባቡን መልሰው እንዲያነቡት መንገር
- አፈጻፀሙን እየተዘዋወሩ መቃኘት፤
- ድጋፍ ለሚሹ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ
- የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል

## ክፍለጊዜ ስምንት

- በ 'ለ' እና 'ሐ' ስር የቀረቡትን መልመጃ ጥያቄዎች ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲሰሩ መከታተልና ድጋፍ ማድረግ

- ሲጨርሱ ደብተራቸውን ሰብስቦ ተገቢውን እርማት መስጠት (እባክዎ መምህር ክፍለጊዜው ካልበቃዎ ደብተሮቻቸውን ከክፍል ውጪ በመውሰድ አርመው ይመልሱላቸው)

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ተግባር ሦስት

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ንባብን በተግባር ይለማመዱታል።

- ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድን ያደራጇቸው
- የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች(ከ1-4) ተራ በተራ እንደሚያነቡ ይንገሯቸው፤ እየተዘዋወሩም ይቃኟቸው
- በመጨረሻም ከየቡድኑ አንዳንድ ተወካይ ድምፅን ከፍ አድርጎ እንዲያነብ ይጋብዙ (ሴትና ወንድ ተማሪዎች በተመጣጠነ ቁጥር መሳተፋቸውን ልብ ይበሉ)
- አስፈላጊ ሲሆን (ተማሪዎችዎ ንባቡ ላይ ሲቸገሩ ካዩ) አረፍተ ነገሮቹን ያንብቡላቸው

## ክፍለጊዜ አስር

## ተግባር አራት

መምህር ዛሬም ተማሪዎችዎ ንባብን በተግባር የሚያከናውኑበት ክፍለጊዜ ነው።

- በጥንድ ወይም በቡድን እየሆኑ ድምፅ አሰምተው የቀረበውን አንቀፅ ተራ በተራ እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹ
- በዕጣ (ተራ ቁጥር በመጥራት) የተወሰኑ ተማሪዎች ምንባቡን ለክፍሉ ድምፃቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ ማድረግ
- በሚነበበበት ወቅት ምዘና ማካሄድ፤ ምዘናው የተማሪዎችን አቀላጥፎ የማንበብ ችሎታ ደረጃ የሚገመግም ነው
- በምዘና ወቅት ለትክክለኛነት፣ ለፍጥነትና ለገለፃ ትኩረት ይሰጥ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት እንዲችሉ ልምምድ ያደርጋሉ

- ቀደም ሲል በማንበብ ትምህርት ክፍል ያነበቡትን ምንባብ እንዴ መልሰው እንዲያነቡት ማድረግ

- በአዛምድ ስር የቀረቡት ቃላት በምንባቡ ውስጥ የት የት እንደሚገኙ እንዲጠቁሙ ማድረግ (አንቀፁንና መስመሩን)
- በደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲያዛምዱ ማድረግና መከታተል
- በመጨረሻ እርማትና ምጋቤ ምላሽ መስጠት
- ተጨማሪ ጊዜ ከተገኘ ቃላቱን ተጠቅመው አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ማድረግም ይቻላል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## ተግባር አምስት

### መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎን ጥንድ ጥንድ እያደረጉ ያደራጇቸው

- በመቀጠል በአካባቢያቸው በቁርስ፣ በምሳ፣ በመክሰስ፣ በመቆያና በእራት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ አይነቶችን እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው
- ከዚያም ሰንጠረዡን ደብተራቸው ላይ እንደፅፉትና (እንዲገለብጡትና) የዘረዘሯቸውን የምግብ አይነቶች በየምድባቸው እንዲያስቀምጧቸው ማትጋት
- ምጋቤ ምላሽ መስጠት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

## መልመጃ አምስት

- አረፍተ ነገሮቹን ደብተሮቻቸው ላይ እንዲፅፉ ማድረግ
- የተሰመረባቸው ቃላት አረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የያዙትን ፍቺ አውዱን እያዩ እንዲገምቱ ማበረታታት፤ ምላሻቸውን በፅሁፍ እንዲሰጡ መንገር
- የሰጧቸውን ምላሾች ይዘው ከጎናቸው ካለ ሰው ጋር እንዲያስተያዩ ማድረግ
- ቃላቱን ሰሌዳ ላይ ፅፎ በጋራ አውዳዊ ፍቻቸውን አብሮ መስራት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

## መልመጃ ስድስት

- በትዕዛዙ መሰረት የተሰጡትን ቃላት እየተጠቀሙ አረፍተ ነገሮቹን እንዲያሟሉ ማድረግ
- ደብተራቸውን ሰብስቦ ማረም፤ ምጋቤ ምላሽ መስጠት
- ትክክለኛውን ምላሽ በጋራ መስራት
- አውድን ከግምት እያስገባን የማናውቃቸውን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ማወቅ እንደምንችል ገለፃ መስጠት

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### ከተማሪዎቹ የሚጠበቅ ውጤት

በዚህ ንዑስ ትምህርት ተማሪዎች አረፍተነገሮችን መስርተው ያቀርባሉ

### መልመጃ ሰባት

- አረፍተነገሮቹን ባሉበት ሁኔታ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፏቸው ማሳሰብ
- የፃፏቸውን አረፍተነገሮች ቅደም ተከተል እንዲያስተካክሉ መጠየቅ
- ያስተካከሉትን ከጎናቸው ካለ ጓደኛ ጋር እንዲጋሩ ማድረግ
- የቅደም ተከተሎቹን ትክክለኛነት በጋራ ውይይት ማረጋገጥ
- አረፍተ ነገሮቹን በትክክለኛው ቅደም ተከተል ደብተራቸው ላይ መልሰው እንዲፅፏቸው ማሳሰብ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

- ቃላቱን ሰሌዳ ላይ መፃፍ
- በአንደኛው ቃል አረፍተነገር በመመስረት ምሳሌ መስጠት
- ቃላቱን ተጠቅመው የየራሳቸውን አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ማበረታታት
- አፈፃፀማቸውን እየተዘዋወሩ መቃኘት
- ድጋፍ ለሚሹት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ
- የፃፏቸውን አረፍተነገሮች እንዲጋሯቸው እድል መስጠት
- የተወሰኑ ተማሪዎች የፃፏቸውን አረፍነገሮች ለክፍሉ ማስነበብ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

- ሰንጠረዡ ውስጥ ያሉ ቃላትን እያገጣጠሙ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ
- በደብተራቸው ላይ የፃፏቸውን አረፍተነገሮች ለጓደኞቻቸው እንዲያጋሩ ማሳሰብ
- የተወሰኑት አረፍተነገሮቻቸውን ለክፍሉ በማንበብ እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- (ለክፍሉ በማንበብ ወቅት ቀደም ሲል እድሉን ያላገኙ ተማሪዎች ከግምት መግባት አለባቸው፤ ለዚህም አስቀድሞ ማስታወሻ ደብተር ላይ መመዝገብ ወይም የነጥብ መያዣ ወረቀት ላይ ምልክት ማድረግ ይገባል)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## ተግባር ስድስት

- ስዕሎቹን እንዲመለከቱ (እንዲያጠኗቸው) ማድረግ
- ስዕሎቹን የተመለከቱ አረፍተ ነገሮች ሊፅፉ እንደሆነ መንገር
- ምሳሌ የሚሆን አረፍተ ነገር ሰሌዳ ላይ መፃፍ
- በምሳሌው መሰረት የየግላቸውን አረፍተነገሮች እንዲፅፉ ማበረታታት
- ድጋፍ ወይም ማበልፀጊያ የሚሹ ተማሪዎች ካሉ ድጋፍ ለሚሹት ተጨማሪ ምሳሌዎች፣ ማበልፀጊያ ለሚየስፈልጋቸው ደግሞ ሌሎች ስዕሎችን በተጨማሪነት ማቅረብ ወይም ክፍሉ ውስጥ ያሉ ነገሮችን እያዩ ተጨማሪ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

# ምዕራፍ አንድ

**ክፍለጊዜ አንድ**

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎቹ የየራሳቸውን ልምድ ያጋራሉ
2. *የየግል ተሞክሮዎቻቸውን ያጋራሉ (ጥያቄውን ካልተረዱት የእረስዎን ያጋሯቸው)*

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አትክልት፣ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬና የእንስሳት ተዋፅዖዎች
2. በፊት እና በኋላ
3. ሩጫ፣ መረብ ኳስ እና እግር ኳስ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## መልመጃ አንድ

**ተማሪዎቹ ተከታዮቹን ምላሾች ከሰጡ ተቀባይነት ይኖረዋል**

1. የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ፣ የግል ንፅህናዋን ዘወትር በመጠበቅ፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ፣ በትምህርቷ ጎበዝ በመሆን
2. ጤነኛ ለመሆን ወይም ጤነኛና ደስተኛ ለመሆን ብለው ሊመልሱ ይችላሉ
3. የተመጣጠነ ምግብ መመገቧ፣ የግል ንፅህናዋን መጠበቋ፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረጓ፣ በተለይ በትምህርቷ ጎበዝ መሆኗ

4. ስለተመጣጠነ ምግብ ጠቀሜታ፣ የግል ንፅህናን ስለመጠበቅ አስፈላጊነት፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ፣ ባጠቃላይ ጤናማና ደስተኛ ህይወት ለመምራት ስለሚቻልባቸው መንገዶች
5. የግል ንፅሕናን መጠበቅ፣ በትምህርት መጎበዝ፣ መታዘዝ፣ ሰውን ማክበር፣ መጥፎ (ነውር) የሆኑ ተግባራትን አለመፈፀም (ለምሳሌ አለመሳደብ፣ አለመስረቅ…) ብለው ሊመልሱ ይችላሉ፤

***እባክዎ መምህር ጥያቄዎቹ ግልፅ ካልሆኑላቸው ምሳሌ የሚሆን ምላሽ በመስጠትና ጥያቄዎቹን መልሶ በማስረዳት እገዛ ያድርጉላቸው፡፡***

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## መልመጃ ሁለት

1. **ተወዳጅነት** …ተፈላጊነት፣ መከበር(ተከባሪነት)፣ ተፈቃሪነት…
2. **ንፅህና** … ከቆሻሻ መፅዳት፣ ንፁህ መሆን፣ መታጠብ ወዘተ
3. **ደስተኛ** … ያላዘነ፣ የተመቸው፣ የማይጨናነቅ፣ ሀዘን የሌለበት...
4. **የተመጣጠነ** …የተስተካከለ፣ ሁሉንም አይነት የያዘ፣ የማይጎዳ…
5. **ተዋፅዖዎች**… ከአንድ ነገር የተገኘ ውጤት ለምሳሌ **ከወተት** ቅቤ፣ አይብ
6. **ጤናማ** … በሽታ የሌለበት፤ ያልታመመ

***ለቃላቱ የሰጣችሁትን ፍቺ መሰረት አድርጋችሁ አረፍተ ነገር ፃፉ። (እንደመሰላቸው ቃላቱን እንዲጠቀሙባቸው ማበረታታት)***

1. *እኔ በቤተሰቤ ውስጥ **ተወዳጅ** ልጅ ነኝ።*
2. ***ንፅሕናን** መጠበቅ ተገቢ ነው።*
3. *እሱ **የተመጣጠነ** ምግብ ስለሚመገብ ጤነኛ ነው።*
4. ***የተመጣጠነ** ምግብ የሚመገብ ሰው ጤናማ ነው።*
5. *ቅቤ፣ አይብ፣ እርጎ የወተት **ተዋፅዖዎች** ናቸው።*
6. ***ጤናማ** ሰው ሁልጊዜ ደስተኛ ነው።*

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

ጤና አጣ ለሚባል ሰው የሚከተሉት መገለጫዎች ይሆናሉ

- *እንደልቡ ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀስም*
- *ድካም ይታይበታል*
- *በደንብ ማውራት አይችልም*
- *ሊያቃስት ይችላል*
- *ሰውነቱ ይከሳል ወይም ያለአግባብ ይነፋፋል፤ ይጠቁራል*
- *ስራ መስራት አይችልም*
- *ምግብ አይመገብም*
- *ብዙ መድሃኒቶች ይወስዳል*
- *ለረጅም ጊዜ አልጋ ላይ ይተኛል ወዘተ*

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ተግባር ሁለት

- *ስራ መስራት አይችልም*
- *ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀስም*
- *ከሰዎች ይገለላል*
- *ሀይወቱን መምራት አይችልም*
- *በሌሎች ላይ ጥገኛ ይሆናል*
- *ለህክምናና ለመድሃኒት መግዣ ገንዘብ ስለሚያስፈልገው ብዙ ወጪ አለበት*
- *ደስተኛ አይሆንም፤ የመነጫነጭ፣ የመከፋት ስሜቶች ይጠናወቱታል ወዘተ በማለት ያሰባሰቡትን መረጃ በቃል ያቀርባሉ*

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. *ስዕሉን እያዩ የሚያውቋቸውን የምግብ አይነቶች ይጠራሉ*
2. *ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ አየር...እያሉ ሊመልሱ ይችላሉ*

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ***ከአንቀፅ አንድ፡*** *ስለጠቃሚ የምግብ አይነቶች (ሀይል ሰጪ፣ ገንቢና በሽታ ተከላካይ)፤* ***ከአንቀፅ ሁለት*** *የሀይል ሰጪ ምግቦች ጠቀሜታና ምሳሌዎች*
2. *ስለገንቢ ምግቦች፤ ስለበሽታ ተከላካይ ምግቦች ወይም ማንኛውም ይሆናል ብለው የሚመልሱት ነገር ልክ ነው፤ ትንቢያ (ግመታ) ስለሆነ*

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. በምንባቡ መሰርት እየተወያያችሁ መልሱ።**

1. *ስለሀይል ሰጪ ምግቦች (ጠቀሜታና አይነት)*
2. *ስለሰውነት ገንቢ ምግቦች፤ ለንፍሰጡሮችና ህፃናት ስለማስፈለጉ፤ ለሰውነት ገንቢ ምግብ ምሳሌ የሚሆኑ ምግቦች*
3. *ስለበሽታ ተከላካይ ምግቦች፤*
4. *ድንች፣ ዳቦ፣ ማር፣ ፓስታ፣ መኮሮኒ፣ የሸንኮራ አገዳ (ከነዚህ ሦስቱን)*
5. *ሁሉም ጠቃሚ ናቸው። ምክንያቱም ሰውነታችን የተመጣጠነ (ከሁሉም የተውጣጣ ምግብ ያስፈልገዋል) ስሆነም ሀይል ሰጪም፣ ገንቢም፣ ከበሽታ ተከላካይ ምግብም ያስፈልጉታል*

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ለ. በ ‘ሀ’ ስር የቀረቡትን የምግብ አይነቶች በ ‘ለ’ ስር ካሉ ምሳሌዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

*1. ለ  2. ሐ  3. ሀ*

**ሐ. ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

*1. ሰውነት ገንቢ  2. አትክልትና ፍራፍሬዎች  3. ገንቢ ምግቦች*

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ተግባር ሦስት

**ድምፅ ከፍ ተደርጎ ሲነበብ መከታተል (ትክክለኛነት፣ ፍጥነትና አገላለፅ(ስርዓተ ነጥቦች) ትኩረት ይሰጣቸው)**

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## ተግባር አራት

*ድምፅ ከፍ ተደርጎ ሲነበብ መከታተል (ትክክለኛነት፣ ፍጥነትና አገላለፅ(ስርዓተ ነጥቦች) ትኩረት ይሰጣቸው)፤ በትክክል ያልተነበቡ ብለው ተማሪዎች ያቀረቧቸውን ቃላት በትክክለኛው አነባበብ እንዲያነቧቸው መጠየቅ*

## መልመጃ አራት

**ሀ. በ ‘ሀ’ ስር የተሰጡትን ቃላት በ ‘ለ’ ስር ከቀረቡ ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

*1. መ  2. ሀ  3. ለ  4. ሐ*

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ተግባር አምስት

**በአካባቢያችሁ ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ አይነቶችን ዘርዝሩ።**

| ከእንስሳት የሚገኙ | ከእህል ዘሮች የሚገኙ | አትክልት የሆኑ | ፍራፍሬ የሆኑ |
|---|---|---|---|
| ስጋ አይብ<br>እንቁላል ወተት<br>አሳ እርጎ<br>ቋንጣ ጥብስ<br>ዶሮ ወጥ … | እንጀራ ቅንጬ<br>ዳቦ ሩዝ<br>ቆሎ ገንፎ<br>ቂጣ … … | ዱባ ቆስጣ<br>ጎመን ካሮት<br>ድንች ቃሪያ<br>ቀይ ስር<br>… | ማንጎ ጊሽጣ<br>ብርቱካን ሎሚ<br>አቮካዶ ትርንጎ<br>እንጆሪ አናናስ<br>… |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## መልመጃ አምስት

**በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

1. *መውሰድ ፡ መዋጥ፣ መወጋት ወይም መጠጣት ወይም መጠቀም*
2. *ማፅዳት ፡ እንዳይቆሽሽ ማድረግ፣ መቦረሽ፣ መፋቅ ወይም ማጠብ*
3. *ያጎለብታል፡ ያጠነክራል፣ ያፈረጥማል፣ ያዳብራል*
4. *ጉዳት፡ አደጋ፣ ችግር፣ መጎዳት፣ መሰበር*
5. *የበለፀጉ፡ የዳበሩ፣ የተመረቱ፣ በብዛት የያዙ፣ ያካተቱ*
6. *ስላገረሸባት፡ እንደገና ስለተነሳባት፣ መልሶ ስላመማት፣ ዳግም ስለመጣባት*

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## መልመጃ ስድስት

**በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት እየመረጣችሁ ቀጥለው የቀረቡ አረፍተነገሮችን አሟሉ።**

1. *መሠረታዊ* 2. *መመገብ* 3. *አቀዝቅዞ*
4. *ሲታመሙ* 5. *እንዳንጠቃ* 6. *ተገቢ*

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

## መልመጃ ሰባት

**ትክክለኛው ቅደም ተከተል፡** 2፣ 5፣ 4፣ 1፣ 3

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## መልመጃ ስምንት

**የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

ተማሪዎቹ የሚፅፏቸው አረፍተ ነገሮች ተከታዮቹን ሊመስሉ ይችላሉ

ሀ. የታመመ ሰው **መታከም** አለበት።

ለ. አንድ **ህመምተኛ** በአምቡላስ ተወሰደ።

ሐ. የታመመችው እህቴ አሁን **ማገገም** ጀምራለች።

መ. ተላላፊ **በሽታ** ብዙ ሰው ያጠቃል።

ሠ. **ጤናማነት** እጅግ አስፈላጊ ነው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

## መልመጃ ዘጠኝ

**በሰንጠረዥ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በማገጣጠም የተሟላ አረፍተ ነገር መስርቱ።**

*1. ሁሴን ክፍሉን አፀዳ።*

*2. ቀጀላ መፅሐፍ አመጣ።*

*3. ትዕግስት ሀሳቧን አካፈለች።*

*4. ሶፊያና ሶሊያና ድሬዳዋ ሄዱ።*

*5. እኔ ተማሪ ነኝ።*

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

## ተግባር፡ ስድስት

## ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕሎች በማየት አጫጭር አረፍተነገሮች ፃፉ።

ስዕሎቹን መሰረት ያደረገና የሰዋስው ስህተት የሌለበት ማንኛውም አረፍተነገር በመልስነት ሊቀርብ ይችላል። ከነዚህ መካከልም፡-

1. እናቴ እጅ ማፅጃ ገዝታ መጣች።
2. የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ እንጠቀም።
3. ሀኪሟ የእጅ ጓንት አድርጋለች።
4. እኔ ወደፊት ሀኪም መሆን እፈልጋለሁ።
5. ኮረና ብዙ ሰው ገድሏል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ኅረቤታሞች

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

**ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-**

- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው መልሰው እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሆነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ቅድመ፣ ጊዜና ድህረ ማዳመጥና ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺዎችን እየሰጡ ልምምድ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን እያመቻቹ ድጋፍ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎቹ ለደረጃው የሚመጥኑ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱና የመሰረቷቸውንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው አረፍተ ነገሮች ተገቢዎቹን ስርዓተነጥቦች ስለመጠቀማቸው ያረጋግጣሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጡትን ታሪክ በቃላቸው መልሰው ይናገራሉ፣
- ካዳመጡት ምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣
- ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ምንባብ ያነባሉ፣
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ይሰጣሉ፣
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፣
- በምንባብ ውስጥ ስሞችን ከሌሎች ቃላት ይለያሉ፣
- ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን እየተጠቀሙ አረፍተ ነገር ይፅፋሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- ምንባቡን ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- ተራን እየጠበቁ ለመናገር ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- ስለጎረቤትና አኗኗራቸው መናገር
- ጥሩ ጎረቤት የሚባሉት የሚያሟሏቸውን ነገሮች ማስረዳት
- የተጣሉ ሰዎችን እንዴት ማስታረቅ እንደሚገባ በተመለከተ መናገር
- በጎረቤቶች መካከል አለመግባባት እንዳይፈጠር ምን ማድረግ እንደሚገባ መግለፅ

### 2.3 ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ድምፅ እያሰሙ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት በጥልቀት ማንበብ
- ቃላትን ከአውዳቸው ለመረዳት መላልሶ ማንበብ

### 2.4 ቃላት

- የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍቺ መፈለግ
- ለቃላት አገባባዊ/አውደዊ ፍቺ መስጠት

- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መፈለግ
- ስም የሆኑ ቃላትን መለየት
- ቃላትን መጠቀም

### 2.5 መፃፍ

- የተሰጡ ቃላትን በመንተራስ አረፍተነገሮችን መመስረት
- አጫጭር አረፍተነገሮችን መፃፍ
- ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ስም የሆኑ ቃላትን መለየት
- ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን መመስረት

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ/ብልሀቶች

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ አካሄድን መተግበር
- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ።

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ-መደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ሲሰጡ ተገቢነታቸውን መፈተሽ
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## 6. መርጃ መሳሪያዎች

- ስዕሎች፣ እውናዊ ቁሳቁሶች፣ የሚደመጡ ወይም የሚታዩ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ በሞባይል የተቀረፁ ድምፆችና ቅንጫቢ ቪዲዮዎች)

## ዝርዝር አቀራረብ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ተሊሴና አበበች

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ምንባብን አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

### ቅድመማዳመጥ

- የተሰጡትን ቃላት ያውቁ እንደሆነ መጠየቅ፤ የተወሰኑ ተማሪዎችን ምላሻቸውን መቀበል፤
- ቃላቱን ሰሌዳ ላይ ፅፎ መተው

ጎረቤት   መንደር   ይቅርታ   ማስታረቅ

**መምህር አሁን ምንባቡን ደረጃቸውን በሚመጥን ፍጥነት ያንብቡላቸው፤ በመጀመሪያው ንባብ ወቅትም የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያቅርቡላቸው፤ ጥያቄዎቹ በሁለተኛ ጊዜ ማንበብ አይደገሙ።**

### ተሊሴና አበበች

ተሊሴና አበበች በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ቤተሰቦቻቸውም ጎረቤታሞች ስለነበሩ ተሊሴና አበበች አብሮ የመጫወት፣ አብሮ ትምህርት ቤት የመሄድና አብሮ የማጥናት እድሉ አላቸው፡፡ በትምህርታቸውም ጎበዞች ስለነበሩ መምህሮቻቸውና ሌሎች ተማሪዎች ይወዷቸዋል፡፡ የተሊሴና አበበች ቤተሰቦችም በዚህ በጣም ደስተኞች ናቸው፡፡

**እያዳመጣችሁ ያላችሁት ታሪክ የሚነግረን ስለነማን ነው?**

ይሁን እንጂ በአንድ ወቅት የተሊሴና አበበች ቤተሰቦች ባልተገባ ምክንያት ተጣሉ፡፡ በዚህም ተኮራርፈው ለረጅም ጊዜ ሳይነጋገሩ ቆዩ፡፡ ተሊሴና አበበችም አብረው ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ከለከሏቸው፡፡ ልጆቹም በዚህ በጣም ተከፉ፡፡ ነገር ግን እነሱ ትምህርት ቤት ሲደርሱ አብረው ይጫወቱና አብረው ያጠኑ ነበር፡፡

**ተሊሴና አበበች አብረው ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ የተከለከሉት ለምንድን ነው?**

ከእለታት አንድ ቀንም ቤተሰቦቻቸውን ለማስታረቅ ተነጋገሩ፡፡ ዛሬ ወደ ሰፈራችን ተያይዘን ነው የምንሄደው አሉ፡፡ ሰፈራቸው ሲደርሱም ወደ አንድ የተከበሩ አዛውንት ሄደው ጉዳዩን አስረዱ፡፡ አዛውንቱንም ቤተሰቦቻቸውን ለማስታረቅ አብረዋቸው እንዲመጡ አግባቡ፡፡

**ቤተሰቦቻቸውን ለማስታረቅ የወሰኑት እነማን ናቸው? ቤተሰቦቻቸውን ለማስታረቅ ምን አደረጉ?**

አብረዋቸው የመጡት አዛውንትም ቤተሰቦቻቸውን ጠሯቸው፡፡ ለምን እንደተጣሉም ጠየቁ። የአበበች አባትም ታምሜ አልጠየቁኝም አሉ፡፡ የተሊሌ ቤተሰቦች ደግሞ ኸረ ፈፅሞ አልሰማንም ነበር አሉ፡፡ አዛውንቱም የታመመ መጠየቅና ማስታመም የቆየ ባህላችን ነው፤ ይህን ባለማድረጋችሁ ትቀጣላችሁ፤ መጀመሪያ ግን ተሊሌንና አበበችን ይቅርታ ጠይቁ አሉ፡፡

**አዛውንቱ የቆየ ባህላችን ነው ያሉት ምኑን ነው?**

ቤተሰቦቹም በራሳቸው ችግር ልጆቹን በማስጨነቃቸው በጣም አዘኑ፡፡ ይቅርታም ጠየቋቸው፡፡ በመጨረሻም ሁለቱ ቤተሰቦች ተቃቅፈው እርቅ አወረዱ፡፡ ተሊሌና አበበችም በዚህ ደስ አላቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላም ቤተሰቦቻቸው ተጣልተው አያውቁም፡፡

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የድህረማዳመጥ ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

- ባዳመጡት ምንባብ መሰረት ጥያቄዎቹን 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' እያሉ እንዲመልሱ ያትጓቸው፤ እውነት ወይም ሀሰት ያሉበትንም ምክንያት እንዲያስረዱ ይጠይቋቸው።
- መጀመሪያ በግላቸው ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ መልሶቻቸውን እንዲያነፃፅሩ የክፍል አደረጃጀቱን ለዚሁ ያመቻቹ
- ታሪኩን በቃላቸው እንዲናገሩ በፈቃደኝነት የተወሰኑ ተማሪዎችን ይጋብዙ፤ ወይም በቡድን አደራጅተው ስለተሊሌና አበበች የሚያስታውሱትን እንዲናገሩ ያትጓቸው
- እባክዎ መምህር ታሪኩን ማስታወስ የሚቸገሩ ሆነው ከተገኙ አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

## መልመጃ ሁለት

- መጀመሪያ ታሪኩን ተማሪዎቹ አስታውሰው እንዲናገሩ በመጋበዝ (ዋና ዋና ነጥቦችን በቅደም ተከተል፤ መጀመሪያ፣ ከዚያ...እያሉ)፣ በመጨረሻም መልመጃውን (ማዛመድ) እንዲሰሩ ያድርጉ።
- ተግባር አንድን በየቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡ ይንገሯቸው (እንዴት እንደሚሰሩም ያሳውቋቸው)

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ተማሪዎች ጎረቤትንና የጉርብትና አኗኗርን በተመለከተ የቀረቡ ተግባራትን መሰረት አድርገው ንግግር ያደርጋሉ።

## ተግባር አንድ

ያሰባሰቡትን መረጃ መሰረት አድርገው፡-

- ጎረቤቶቻቸው እንዴት በሰላም እንደሚኖሩ
- አለመግባባቶች ሲፈጠሩ እንዴት እንደሚፈቱ
- እርቅ ለማድረግ የሚሄዱባቸውን ደረጃዎች (ምን ምን እንደሚያደርጉ) እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፤ ያበረታቷቸው
- የሀሳብ ፍሰቱንና ተጨባጭነቱን እያዩ ምዘና ያድርጉ፤ መናገር ክሂል ላይ ያላቸውን አፈፃፀም እያዩ ነጥብ ይስጧቸው (በክፍለጊዜው ሁሉንም ካላዳረሱ በቀጠይ ክፍለጊዜዎች ያሟሉ)

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ተግባር ሁለት

ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው ልምዳቸውን መሰረት ያደረጉ ምላሾች ለክፍሉ ያቅርቡ። **በተግባር አንድ** እድሉን ያላገኙ በዚህ ተግባር ቅድሚያ ይሰጣቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የአቀላጥፎ ማንበብ አቅማቸውንና አንብቦ የመረዳት ችሎታዎቻቸውን ያጎለብታሉ

## መልመጃ ሦስት

ኮረናን(ኮቪድ 19) በተመለከተ የቀረቡትን ሁለት አንቀፆች ተማሪዎች ድምፅ እያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ። ሲያነቡም ውጤት (ነጥብ) ይስጧቸው (ትክክለኛነት፣ ፍጥነትና አገላለፃቸውን ይመዝኑ)፤ አንዴ ሞዴል ሆነው ቢያነቡላቸውም ተመራጭ ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## መልመጃ አራት

- የቀጣዮቹን ቃላት ፍቺ እንዲገምቱ ይጠይቋቸው፤ በድህረ ምንባብ ወቅት ስለሚያረጋግጡ እንዲሁ ይለፉት (ተጨማሪ ማብራሪያ ለቃላቱ አይስጡ፤ ሰሌዳ ላይ ግን ሊጽፉላቸው ይችላሉ)

| ማህበራዊ ህይወት ጉርብትና መቻቻል |
|---|

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

- ስዕሉን እንዲመለከቱ ይጠይቋቸው፤ ያዩትንም እንዲናገሩ ይጋብዟቸው
- ስለጎረቤቶቻቸው ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው (ለምሳሌ እነማን እንደሆኑ፤ የትኞቹን ይበልጥ እንደሚወዱ፣ ለምን)
- የቀረበውን ምንባብ እያነበቡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## መልመጃ አምስት

**በምንባቡ መሰረት ተገቢውን መልስ ስጡ።**

- እባክዎ መምህር ምንባቡን አንዴ ያንብቡላቸው
- መጀመሪያ ምንባቡን መሰረት አድርገው በግላቸው ለጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ሀሳብ ይቀያየሩ
- በመጨረሻ እጅ እያወጡ በየጥያቄዎቹ ላይ ዕብረቃ ያቅርቡ
- የተወሰኑ ምላሾችን አጠር አጠር እያደረጉ ሰሌዳ ላይ ሊፅፉላቸው ይችላሉ
- ተግባር ሦስትን በተመለከተ ለቀጣዩ ክፍለጊዜ በየቤትስራ መልክ መረጃ አሰባስበው እንዲመጡ ይንገሯቸው

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ተግባር ሦስት

- ከጎረቤት ጋር መኖር ስለሚኖረው ጠቀሜታና ያለጎረቤት መኖር የሚያስከትለውን ጉዳት በተመለከተ መረጃ አሰባስበው በፅሑፍ ይዘው የመጡትን በንባብ ተራ በተራ ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ እድሉን ያመቻቹላቸው
- እያነበቡ በሚያቀርቡበት ወቅትም የስራቸውን ጥራት (ሀሳብና ቋንቋ) ይመዝኑ
- በመጨረሻም በሰሌዳ ላይ ዋና ዋና ነጥቦችን እየፃፉ ሁለቱን ጥያቄዎች ይቋጩ

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## መልመጃ ስድስት

ይህንን መልመጃ በአማራጭነት አስቀድመው በየቤት ስራ መልክ በመስጠት ፅፈው እንዲመጡ ማድረግ ይችላሉ። ካሆነም ክፍል ውስጥ በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉት አድርገው ሊያሰሯቸው ይችላሉ።

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፣ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ ይለያሉ እንዲሁም የተሰጧቸውን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ

## መልመጃ ሰባት

**ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለተከታዮቹ ቃላት ፍቺ ስጡ።**

- ወደ ምንባቡ እየተመለሱ ቃላቱ በአውዱ ውስጥ የያዙትን ፍቺ መሰረት እያደረጉ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው
- ከተማሪዎችዎ ጋር የጋራ ውይይት እያደረጋችሁ የቃላቱን ፍቺ ስሩ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ለ. በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት እየመረጣችሁ አረፍተ ነገሮቹን አሟሉ።**

| | | |
|---|---|---|
| መተጋገዝ | መተሳሰብ | ጎረቤት |
| ወዳጅነትን | መመስረት | ሰፈራችን |

- ጥያቄዎቹን ፅፈው በባዶው ቦታ ላይ ቃላትን ከሳጥኑ እየመረጡ እንዲያሟሉ ይንገሯቸው

- የፃፉትን ደብተሮቻቸውን በመሰብሰብ አርመው ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው (ጊዜ ካልፈቀደ ከክፍል ውጪ ደብተሮቻቸውን በመውሰድ አርመው ይመልሱላቸው)

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

- የቀረቡትን ምስሎች(ተቃርኖን የሚገልፁ፤ አጭር ረዥም፣ ነጭ ጥቁር) እያዩ ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጉ
- የሚያውቋቸውን ተቃራኒ ቃላት እንዲናገሩ ጥቂት ደቂቃዎች ይስጧቸው (እስከ አምስት የሚደርሱ ተማሪዎችን ሊያሳትፉ ይችላሉ)
- ተማሪዎቹ የሰጧቸውን ተቃራኒ ቃላት ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው
- በ'ሐ' ስር የቀረቡትን ቃላት ፅፈው እንዲያዛምዱ ያድርጉ፤
- መልሶቻቸውን ደብተር በመቀያየር እንዲያነፃፅሩ ያድርጉ
- በመጨረሻም ትክክለኛውን ምላሽ ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው (ፊደሎቹን ብቻ)

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

- በምሳሌው መሰረት በሳጥኑ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት እየመረጡ ከአረፍተነገሮቹ እንዲጽፉ ያትጓቸው
- አረፍተነገሮቹን ደብተራቸው ላይ ፅፈውና አሟልተው ከጨረሱ በኋላ ሰብስበው እርማት ያድርጉበት
- ትክክለኛውን ምላሽም ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### ሠ. የተሰመረባቸውን ቃላት ተቃራኒ መርጣችሁ መልሱ።

- ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲሰሩ (መልሶቹን እንዲመርጡ) ያደርጉ
- መልሶቻቸውን በጥንድ ወይም በቡድን እየሆኑ እንዲያነፃፅሩ ያበረታቷቸው
- በመጨረሻም ትክክለኛ መልሶቹን ከተማሪዎችዎ ጋር በጋራ ሆናችሁ አረጋግጡ፤ ትክክለኛ ምላሽ የያዙት ፊደላትም በቁጥሮቹ ትይዩ ይፃፉ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

### መልመጃ ስምንት

መልመጃው ህፃናት ተማሪዎቹ ስሞችን እንዲለዩ የሚያስችል ነው

- ደብተራቸው ላይ ፅፈው -ኦች ያለባቸውን ቃላት እንዲያሰምሩባቸው ያድረጉ
- ቀጥሎ ስሞቹ (የተሰመረባቸው) በነጠላ ቅርፃቸው እንዴት እንደሆኑ (-ኦች ሳይኖር) እንዲናገሩ ያድርጉ

- እነዚሁ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ስሞችን ለይተው እንዲያመለክቱ ይጠይቋቸው (ለምሳሌ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር ውስጥ ‘መስከረም’ ቃል ክፍሉ ስም ነው)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተከታተሉ በኋላ ስም የሆኑ የቃል ክፍሎችን መመስረት ይችላሉ፣ የሚሰጧቸውን ቃላት ተጠቅመው የየራሳቸውን አረፍተነገሮች መመስረት ይችላሉ፣ ተገቢ ስርዓተነጥቦችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

### መልመጃ ዘጠኝ

### ሀ. በተሰጧችሁ ቃላት አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

- ምሳሌውን ሰሌዳ ላይ ፅፈው ያሳዩአቸው
- ጥያቄዎቹን አንዳንድ መስመር እያስቀሩ እንዲፅፉ ያድርጓቸው
- በምሳሌው መሰረት የተሰጡትን ቃላት ተጠቅመው የተሟሉ አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ያትጓቸው
- የፃፉትን እንደአጨራረስ ቅደም ተከተላቸው እርማት ያድርጉላቸው
- በመጨረሻም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

## ስርዓተ ነጥቦች

- ከዚህ ቀደም የሚያውቋቸውን ስርዓተ ነጥቦች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው
- የጠቀሷቸውን ስርዓተ ነጥቦች የተወሰኑ ተማሪዎችን በመጋበዝ ምልክቶቹን ሰሌዳ ላይ ፅፈው እንዲያሳዩ ያድርጉ
- ስርዓተ ነጥቦቹ ለምን ለምን ተግባር (በምን ወቅት ጥቅም ላይ) እንደሚውሉ እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው

### መልመጃ አስር

### ለ. ተከታዮቹን አረፍተነገሮች ትክክለኞቹን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም መልሳችሁ ፃፏቸው።

- በምሳሌዎቹ መሰረት ትክክለኞቹን ስርዓተ ነጥቦች እየተጠቀሙ አረፍተነገሮቹን አሟልተው መልሰው እንዲፅፉ ያድርጉ
- እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው

- በመጨረሻም ደብተራቸውን ሰብስበው እርማት ይስጧቸው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## መልመጃ አስራ አንድ

- የተሰጡትን ፊደላት ተጠቅመው የቻሏቸውን ያህል ስሞች እንዲመሰርቱ ይጠይቋቸው
- ለመነሻ የሚሆኑ ምሳሌዎችን ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው
- እየተዘዋወሩ በትክክለኛው አካሄድ ላይ መሆናቸውን ይገምግሙ
- በርካታ ስሞችን የመሰረቱ ሦስት ልጆችን (በደረጃ) መርጠው ያስጨብጭቡላቸው፤ ሌሎቹም እንዲተጉ ያበረታቷቸው

# የመልመጃዎችና ተግባራት መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**ቅድመ ማዳመጥ**

**ጎረቤት፣ መንደር፣ ይቅርታ** እና **ማስታረቅ** ለሚሉት ቃላት ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ እንዳለ መቀበል

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ስለተሊሌና አበበች
2. ወላጆቻቸው ስለተጣሉ
3. ተሊሌና አበበች፤ የአገር ሽማግሌን አማከሩና አግባብተው ወደ ቤተሰቦቻቸው ይዘዋቸው ሄዱ
4. የታመመ መጠየቅና ማስታመም

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የድህረማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

1. ሐሰት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. ሐሰት 5. እውነት 6. እውነት

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**መልመጃ ሁለት**

1. ሰ 2. ረ 3. ሠ 4. ቀ 5. ሸ 6. ለ 7. ሀ 8. ሐ 9. መ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ተማሪዎች ያመጡትና ያጋሩት ማንኛውም ምላሽ ተቀባይነት አለው፤ ከርዕሰ ጉዳዮቹ እስካልወጣ ድረስ

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር ሁለት**

ማንኛውም ትክክለኛ ምላሽ ተቀባይነት አለው።

ምሳሌ የሚሆኑ

1. ችግራቸው ምን እንደሆነ መጠየቅ (መነሻውን ማወቅ)፤ ማስታረቅ (አንተም ተው አንቺም ተይ ማለት)
2. አይመስለንም፤ ምክንያቱም ህፃናት ፍቅር ናቸው፤ ቢጣሉም ቶሎ ይታረቃሉ፤ የቤተሰቦች ጉዳይ የቤተሰቦች ነው
3. እንጠይቀዋለን፤ ሀኪም ቤት እንዲሄድ እንመክረዋለን፤
4. አለመግባባቶችን በሰላም መፍታት፤ ነገሮችን አለማክረር፣ ይቅርታ መጠያየቅ፤ ከሚያጋጩ ድርጊቶች መራቅ፤ መተሳሰብና መረዳዳት፤ አምዱ የሌላውን ሀሳብ ማክበር

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**መልመጃ ሦስት**

አንቀፆቹን ተከፋፍለው ሲያነቡ መከታተል፤ ፍጥነት፣ ትክክለኛነትና አገላለጽን በጥሞና መከታተል፤ ስህተትን ራሳቸው እንዲያርሙ ፍንጭ መስጠት

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**መልመጃ አራት**

- ስዕሎቹን እንዲመለከቱና ሀሳብ እንዲሰጡ ማበረታታት

**የቅድመንባብ ጥያቄዎች**

- የተመለከቱንና የገባቸውን ማንኛውንም መልስ ይቀበሉ
- ማንኛውም የተጋራ ልምድ

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ጎን ለጎን 2. መከባበር፣ መቻቻልና መተማመን

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**መልመጃ አምስት**

- አብሮ በመኖር፤ በመከባበር፣ በመቻቻልና በመተማመን
- በደስታም ሆነ በችግር ወቅት አብረው ሲሆኑ፤መከባበር፣ መቻቻልና መተማመንን ሲቀበሉና ሲኖሩት
- በሆነው ባልሆነው መጋጨት ይፈልጋሉ፤ በችግርም ሆነ በደስታ ወቅት አብረው መሆን አይፈልጉም፤ ይቅርታ ማድረግም መቀበልም አይሆንላቸውም ወዘተ
- በመከባበር፣ በመቻቻልና በመተማመን፤ በስራ በመተጋገዝ፣ በዓላትን አብሮ በማክበር፤ በችግር ጊዜ በመረዳዳት

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ተግባር ሦስት**

1. ለመረዳዳት፣ ችግርንና ደስታን አብሮ ለመጋራት፤ ለሰላማዊ ህይወት መኖር፤ አካባቢያዊ ደህንነት ለማረጋገጥ፤ በስራ ውጤታማ ለመሆን ወዘተ
2. አከባቢያዊ ሰላም አይኖርም፣ ደስታ ይርቃል፤ ማህበራዊ ህይዎት ይላላል፤ ችግርን ለመቋቋም አይቻልም ወዘተ ብለው ሊመልሱ ይችላሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**መልመጃ ስድስት**

1. <u>ሐ</u> 2. <u>ለ</u> 3. <u>መ</u> 4. <u>ሀ</u> 5. <u>ሐ</u>

**ትምህርት አምስት፡ ቃላት**

**መልመጃ ሰባት**

1. መንገዶች … ዘዴዎች፣ አኗኗሮች፣ ብልሃቶች
2. ግንኙነታቸውን … ትስስራቸውን፣ አብሮ መኖራቸውን፣ ተግባቦታቸውን
3. መከባበር … አለመናናቅ፣ መተሳሰብ፣ አንዱ ለአንዱ ዋጋ መስጠት
4. ተናፋቂ … ሊታይ የሚያጓጓ፣ የሚወደድ፣ የማይጠላ
5. ይተጋገዛሉ … ይረዳዳሉ፣ አንዳቸው ላንዳቸው ይደርሳሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

1. **መመስረት** 2. **መተጋገዝ** 3. **ጎረቤት** 4. **ምቹ** 5. **ወዳጅነትን** 6. **መተሳሰብ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**አዛምድ**

1. **ሠ** 2. **ረ** 3. **መ** 4. **ለ** 5. **ሀ** 6. **ሐ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

1. **ሰረገላ** 2. **ቴሌቪዥን** 3. **ኩንታል** 4. **መፅሐፍ** 5. **ብዕር** 6. **ጤፍ** 7. **መቀስ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

1. **ለ** 2. **ሐ** 3. **ሀ** 4. **መ** 5. **ለ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ ስምንት**

1. መስከረም አዳዲስ **ልብሶች** ገዛች።
2. **ተክሎች** እንክብካቤ ይፈልጋሉ።
3. ሊበን ብዙ **መፅሐፎች** አነበበ።
4. አቶ መሐመድ የዛፍ **ችግኞች** ተከሉ።
5. **አበቦች** በየመንገዱ ፈክተው ይታያሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ትምህርት አምስት፡ መፃፍ**

**መልመጃ ዘጠኝ**

1. እህቴ የታመመ ጠየቀች።
2. እኔ ቁርሴን በላሁ።
3. አባቴ ተረት ነገረኝ።
4. ሶፍያ በትምህርቷ ጎበዝ ናት።
5. እናቴ ሀኪም ሆነች።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ስርዓተ ነጥቦች**

**መልመጃ አስር**

1. ስምሽ ማን ነው?
2. ብርሃኔ ሁለት እህቶችና አንድ ወንድም አላት።
3. ጎበና፣ ግርማና ቶለሺ የክፍል ጓደኞቹ ናቸው።
4. ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ማንጎና ፓፓያ በአካባቢያችን ይገኛሉ።
5. በእረፍት ቀንሽ ዘመድ ለመጠየቅ አስበሻል?

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መልመጃ አስራ አንድ**

ብር፣ ስብ፣ ሳል፣ ሳር፣ ኳስ፣ ሎሚ፣ አገር፣ ምርት፣ ማገር፣ ስደት፣ ብድር፣ ተማሪ፣ ምስር፣ አንገት፣ ብስክሌት …

# ምዕራፍ ሶስት

# ስነቃል

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎቹ ስነቃልን አዳምጠው ደግመው እንዲተርኩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎቹ ዋና ዋና ባለታሪኮችን ከተረት ወይም አፈታሪክ አውጥተው እንዲናገሩ ያተጋሉ
- ድምጽ አሰምተው አጫጭር ስነቃሎችን አስተካክለው እንዲያነቡ ያደርጋሉ
- የታሪኩን ዋና ሀሳብ እንዲፅፉ ይጠይቃሉ፤ ያበረታታሉ
- ከምንባብ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ፍቺ ገምተው እንዲናገሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ቅድመ፣ ጊዜና ድህረ ማዳመጥና ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ስም የሆኑ የቃል አይነቶችን ለይተው እንዲያመለክቱ የሚያስችሉ መልመጃዎችን ይሰጣሉ
- ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው አረፍተ ነገሮች ተገቢዎቹን ስርዓተነጥቦች ስለመጠቀማቸው ያረጋግጣሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት (የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት፡፡

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስነቃልን አዳምጠው ደግመው ይተርካሉ፣
- ዋና ዋና ባለታሪኮችን ከስነቃል ውስጥ አውጥተው ይናገራሉ፣
- ድምጽ አሰምተው አጫጭር ስነቃሎችን አስተካክለው ያነባሉ፣
- የታሪኩን ዋና ሀሳብ ይፅፋሉ፣
- ከምንባቡ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ፍቺ በመገመት ይናገራሉ፣
- ስሞችን ከምንባብ ውስጥ ይለያሉ፣
- አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- አንበሳና ሰጎን የተሰኘውን ምንባብ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- ተራን እየጠበቁ ለመናገር ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- ታሪክን አዳምጦ መልሶ መናገር
- የተጓደለ ቃለመጠይቅ አሟልቶ ምልልሱን ማቅረብ
- መጠየቅ ስለሚፈልጉት ነገር አንስተው መጠያየቅ
- ተረት ወይም አፈታሪክ መናገር

### 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ድምፅ እያሰሙ ማንበብ (የተጠማችው ቁራ)
- የፅሑፍን ፍሬ(ዋና) ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት በጥልቀት ማንበብ
- ቃላትን ከአውዳቸው ለመረዳት መላልሶ ማንበብ

### 2.4. ቃላት

- ለቃላት አገባባዊ/አውደዊ ፍቺ መስጠት
- ስም የሆኑ ቃላትን መለየት
- ቃላትን መጠቀም

### 2.5. መፃፍ

- ክፍል ውስጥ ያሉ ነገሮችን ስያሜዎች መፃፍ
- አጫጭር አረፍተነገሮችን መፃፍ
- ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ስም የሆኑ ቃላትን መለየት፣ መመስረት
- ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን መመስረት

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ/ብልሀቶች

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ አካሄድን መተግበር
- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ።

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ-መደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጦ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- ስም የሆኑ የቃል ክፍሎችን (አይነቶችን) ለይተው ማወቃቸውንና መጠቀማቸውን ማረጋገጥ
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፣ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## 6. መርጃ መሳሪያዎች

- ስዕሎች (ለተረቶቹ የተመቹ)፣ እውናዊ ቁሳቁሶች፣ የሚደመጡ ወይም የሚታዩ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ በሞባይል የተቀረፁ ድምፆችና ቅንጫቢ ቪዲዮዎች)

# ዝርዝር አቀራረብ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### አንበሳና ሰጎን

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ታሪክን አዳምጠው መልሰው ይናገራሉ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከቤተሰባቸው ተረት የሚነግራቸው ማን እንደሆነ መጠየቅ
2. የሚያውቋቸውን የተረት ስሞችን (ርዕሶችን) እንዲናገሩ ማበረታታት
3. ስለአንበሳና ሰጎን ሰምተው ያውቁ እንደሆን መጠየቅና ምን አይነት እንስሳት እንደሆኑ መጠየቅ (አጥቢና የአዕዋፍ ዘር ስለመሆናቸው)

### የማዳመጥ ጊዜ ተግባራት

- እያዳመጡ ስዕሎቹን እንዲያጠኑ(እንዲቃኙ) መንገር
- በመጀመሪያው ንባብ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ በሁለተኛው ግን ማለፍ
- የተማሪዎቹን ደረጃ ያገናዘበ ልከኛ የንበት ፍጥነትን መከተል

**አንበሳና ሰጎን**

በድሮ ጊዜ ጎረቤታሞች የሆኑ አንድ አንበሳና አንድ ሰጎን ነበሩ። አንበሳው በሬ ሲኖረው፣ ሰጎኗ ደግሞ ላም ነበራት። ከእለታት አንድ ቀን የሰጎኗ ላም ጥጃ ወለደች። አንበሳውም ጥጃዋን አንስቶ የራሱ በሬ ስር አስቀመጣት። ላሚቷ አጠገብ ደግሞ ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ አስቀመጠ። ሰጎን ከሄደችበት ቆይታ ተመለሰች። አንበሳውም በሬዬ ጥጃ ወለደልኝ፤ ያንቺ ላም ደግሞ ይህንን ድንጋይ ወለደች አላት።

***ተማሪዎች ሰጎኗ አንበሳውን የምታምነው ይመስላችኋል? እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?***

ሰጎኗም አያ አንበሳ እኔ ይህን አላምንም አለች። ቀጥላም “ጥጃውን ልትወልድ የምትችለው ላሜ ናት” አለችው። አያ አንበሳም “አይ ተሳስተሻል የወለደው የኔ በሬ ነው” አላት። “ከፈለግሽ እንስሳትን ጠርተን ፍርድ ይስጡበት” ብሎ ተናገረ። ሰጎኗም በዚህ ተስማማችና የዱር እንስሳት በሙሉ ተጠሩ።

***ተማሪዎች የዱር እንስሳቱ ምን የሚወስኑ ይመስላችኋል? እናንተ ዳኛ ብትሆኑ ምን አይነት ውሳኔ ትሰጣላችሁ?***

*ቀጭኔ፣ ዝንጀሮ፣ ጅብ፣ ሚዳቋ፣ የሜዳ አህያ፣ አሳማ፣ ጎሽ፣ዝሆን በወቅቱ የተገኙ እንስሳት ነበሩ። አንበሳውም "የኔ በሬ ጥጃ ወለደልኝ የሷ ደግሞ ድንጋይ ወለደች። ነገር ግን ሰጎን አላመነችኝም እስቲ እናንተ ፍረዱ" አላቸው። እንስሳቱም ተመካከሩና አንበሳውን ስለፈሩት በሬው ነው ሊወልደው የሚችለው ብለው ፈረዱለት።*

*በኋላም ጦጣ ከሩቁ እየሮጠች ስትመጣ ታየች። አንበሳም "አንቺ ጦጣ ለምን ዘገየሽ!?" ብሎ ተቆጣት። ጦጣም "መሬት ተሰንጥቃ ስሰፋ ነበር" አለችው። አንበሳም "አንቺ ውሸታም መሬት ይሰፋል?" አላት። ጦጣም "ታዲያ በሬ ይወልዳል?" ብላ ወደመጣችበት እየሮጠች ሄደች። ሌሎቹ እንስሳትም በውሸት በመመስከራቸው በጣም አፈሩ። እኛ ተሳስተናል እሜት ጦጣ ልክ ናት አሉ። ሰጎኗንም ይቅርታ በመጠየቅ ወደየመጡበት አቀርቅረው ተመለሱ።*

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## መልመጃ አንድ

- *ታሪኩን የዘነጉት ከሆነ አንድ ጊዜ ደግሞ ማንበብ (ለማስታወስ)*
- *በምንባቡ መሰርት ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ መጋበዝ*
- *ጥያቄዎቹ እንዲናገሩና እንዲያዳምጡ እድል ስለሚፈጥሩላቸው በትኩረት ይሰራ*
- *እባክዎ መምህር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች እድል የሚያገኙበትን ሁኔታ ይፍጠሩ*

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## መልመጃ ሁለት

***ሀ. 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' በማለት መልሱ።***

- *በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት እያሉ እንዲመልሱ ይጋብዟቸው*
- *አንዳቸው ሲመልሱ ሌሎቹ እንዲያረጋግጡ እድል ይፍጠሩላቸው፤ያበረታቷቸው*

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ተግባር አንድ

- *ታሪኩን ተራ በተራ እያስታወሱ መልሰው እንዲናገሩ በቡድን በቡድን ማደራጀት*
- *አብዛኛው ተማሪ ታሪኩን መልሶ በመናገር መሳተፉን እርግጠኛ ይሁኑ፤ እየተዘዋወሩ ይከታተሉ*

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### መልመጃ ሦስት

- ቃላቱን በደብተራቸው ላይ ፅፈው ከፍቺያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያበረታቷቸው
- ሲጨርሱም መልሶቹን እንደክፍል በጋራ ከተማሪዎቹ ጋር ይስሩ
- ተረት ወይም አፈታሪክ ቤተሰባቸውን ወይም የአካባ ሰው ጠይቀው በቀጣዩ ክፍለጊዜ ለክፍል እንዲያቀርቡ ጥቆማ ይስጧቸው

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

- ከቤተሰባቸው አባል ወይም ከአካባቢ ሰው ጠይቀው የመጡትን ተረት ወይም አፈታሪክ አጥንተው መጀመሪያ ለቡድን አባላቶቻቸው ከዚያም የተመረጠውን ለክፍል እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው
- እየተዘዋወሩ ቅኝት ያድርጉ
- በመጨረሻም በየቡድኑ የተሻሉ የተባሉ ታሪኮችን ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

### ተግባር ሦስት

- ቃለመጠይቁን በምሳሌው መሰረት የተጓደሉትን አስቀድመው እንዲያሟሉ ማድረግ (በቡድን በቡድን እየሆኑ ቢሰሩት ይመረጣል)
- ከዚያም በምላሾቹ ላይ በጋራ (እንደ ክፍል) የተሻሉ የተባሉት ላይ መስማማት
- በመጨረሻም የተሟላውን ቃለመጠይቅ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በቃል እንዲለማመዱት ማድርግ (በዕለቱ ለማቅረብ ጊዜው ካልበቃ በሚቀጥለው ክፍለጊዜ በቃል እንደሚያቀርቡት መጠቆም)

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

### ተግባር አራት

**ምን ብጠየቅ ደስ ይለኛል?**

- በምሳሌነት የተሰጠውን ጥቆማ መሰረት በማድረግ ምን ቢጠየቁ ደስ እንደሚላቸው እንዲወስኑ ማበረታታት
- መጠየቅ የሚፈልጓቸውን ነጥቦች ከዘረዘሩ በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን ነጥቦቹን ተቀያይረው ተራ በተራ እንዲጠያየቁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ማበረታታት

- ትግበራውን እየተዘዋወሩ መቃኘት፤ ኢመደበኛ ምዘና ማካሄድ

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ምንባብን አቀላጥፈው የማንበብ አቅማቸውን ያጎለብታሉ፤ የቀረበን ምንባብ አንብበው ይረዳሉ

## የተጠማችው ቁራ

- እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ተራ በተራ ድምፃቸውን እየሰሙ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው
- በንባብ ወቅትም እያሳዩ ያሉትን የንባብ ችሎታ ለውጥ ይገምግሙ (ለትክክለኛነት፣ ፍጥነትና አገላለፅ ትኩረት ይስጡ)
- ቢቻል ሁሉም ተማሪ የማንበብ እድሉን እንዲያገኝ ይደረግ

## ክፍለጊዜ፡ አስር

## መልመጃ አራት

- የእውነት ሀሰት ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ያድርጉ
- ጥያቄዎችንም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ምንባቡን መልሰው በማንበብ እንዲሰሯቸው ያበረታቷቸው
- በጥንድ ጥንድ የሰጧቸውን መልሶች በቡድንእንዲመለከቷቸው ያድርጉ፤
- በመልሷቻቸው ላይ ልዩነት ካለ የምንባቡ ክፍልን መልሰው ማየት እንደሚችሉ ይጠቁሟቸው
- በመጨረሻም ሁሉንም ጥያቄዎች በጋራ (እንደክፍል) ስሯቸው

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

- ይህንን ንዑስ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፤ እንዲሁም የቃል ክፍላቸው ስም የሆኑ ቃላትን ከሌሎች ቃላት ለይተው ያመለክታሉ

## መልመጃ አምስት

- የቀረቡትን አምስት ቃላት ወደ ምንባቡ መልሰው በመሄድ ያላቸውን አውዳዊ ፍቺ እንዲያመለክቱ ያበረታቷቸው

- ምላሾቻቸውንም እንዲያፃፅሩ እድሉን ይስጧቸው፤ እየተዘዋወሩ ምልከታም ያድርጉ
- በመጨረሻም ቃላቱን እየተጠቀሙ አረፍተ ነገሮችን በቃል እንዲመሰርቱ ይጠይቋቸው
- ቃላቱን ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የተሻለ የሚሉትን የተማሪዎች ፍቺ ከጎናቸው ይፃፉ

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## መልመጃ ስድስት

- ከቀረቡት ቃላት መካከል ስም የሆኑትን አስቀድመው በየግላቸው እንዲለዩ ማድረግ
- ቀጥሎም በጥንድ ወይም እንደብዛታቸው ሁኔታ በቡድን እየሆኑ ስም ተብለው የተመረጡትን ቃላት እንዲመረምሩ ማድረግ፤ የቀሩ (ያልተመረጡ ካሉ) እንዲያጣሩ መጋበዝ፤
- ቃላቱን ስም ናቸው ያሉበት የተለየ ምክንያት ያላቸው እንደሆን መጠየቅ፤ ማጋራት
- በጋራ እንደክፍል መስራት፤ ምጋቤ ምላሽ መስጠት

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## ተግባር አምስት

- የተጠማችው ቁራ ወደሚለው ምንባብ እንዲመለሱና ስም የሆኑ ቃላትን ፈልገው እንዲያወጡ ማበረታታት
- ምሳሌ የሚሆኑ የተወሰኑ ቃላትን አብሮ ማፋለግና ሰሌዳ ላይ መፃፍ

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## መልመጃ ሰባት

- በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ስሞች በተጓደሉት አረፍተነገሮች ውስጥ እያስገቡ አረፍተነገሮቹን እንዲያሟሉ መጋበዝ
- እየተዘዋወሩ መቃኘት፤ ድጋፍ ለሚሹ ድጋፍ ማድረግ
- ጥንድ ጥንድ ወይም በአበስተኛ ቡድን (አራት ወይም አምስት) እየሆኑ መልሶቻቸውን እንዲያነፃፅሩ መጠየቅ
- በመጨረሻ መልሶቹን በጋራ ማረጋገጥ

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

የህንን ትምህርት ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ስሞችን ለይተው በአረፍተነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ፤ የየራሳቸውን አረፍተነገሮችም ይመሰርታሉ

### ተግባር ስድስት

- በማዳመጥና በማንበብ ወቅት ቀርበው የነበሩ ምንባቦችን (አንበሳና ሰጎን፤ የተጠማችው ቁራ) በማስታወስ ታሪኮቹ የያዟቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች ጽፈው ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ሁኔታውን ያመቻቹላቸው

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

- በክፍላቸው ውጥ ያሉ ነገሮችን (ቁሶችንና መገልገያ ነገሮችን) መጠሪያ እንዲፅፉ መጠየቅ
- ምሳሌዎችን መስጠትና ሲሰሩ እየተዘዋወሩ መመልከት
- በተቻለ መጠን በርካታ የተንቀሳቃሽና ቋሚ ነገሮችን በስማቸው እየለዩ እንዲፅፉ ማበረታታት
- ሲጨርሱ መልሶቻቸውን በቡድን በቡድን እየሆኑ እንዲያነፃጽሩ መጋበዝ፤ አፈጻፀሙን መከታተል

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

- የተሰጧቸውን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ማድረግ
- በባለቤትነትና ተሳቢነት ወይም መሙያነት የገቡትን ስሞች ከየአረፍተ ነገሮቹ ለይተው እንዲያሰምሩባቸው ማበረታታት
- ሰርተው ሲጨርሱ ደብተሮቻቸውን ሰብስቦ ማረም
- በመጨረሻም በጋራ ስሞቹን ለይቶ ማመላከት

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### ተግባር ሰባት

- የተሰጧቸውን ፊደላት እየገጣጠሙ የቃል ክፍላቸው ስም የሆኑትን ቃላት እንዲመሰርቱ ማድረግ፤ ለዚህም መነሻ ይሆናቸው ዘንድ ምሳሌዎችን መስጠት

- እባክዎ መምህር ምሳሌዎችዎ ባለ ሁለት ፊደል፣ ባለሦስት ፊደል፣ ባለአራት ፊደል ወዘተ ቃላት ይሁኑ
- እየተዘዋወሩ በማየት አፈፃፀማቸውን ይመዝኑ፤ ቃላት ምስረታው ላይ የሚቸገሩ ተማሪዎች ካጋጠሙዎት ድጋፍ ያድርጉላቸው

## የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. አያት፣ እናት ወይም አባት ወዘተ
2. አዎ/አይ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**መልመጃ አንድ**

1. አንበሳና ሰጎን
2. በተወለደ ጥጃ፤ አንበሳ የኔ ነው በማለቱ
3. ቀጭኔ፣ ዝንጀሮ፣ ጅብ፣ ሚዳቋ፣ የሜዳ አህያ፣ አሳማ፣ ጎሽ፣ዝሆን
4. ጥጃው ለአንበሳ ይገባዋል፤ በሬው ነው የወለደው ብለው
5. ጦጣ
6. መሬት ተሰንጥቃ ስሰፋ
7. አዎ/አይ ብለው መልሰው ምክንያት ሊሰጡ ይችላሉ
8. የራስ ያልሆነ ነገርን አለመፈለግ፤ ፍርድ አለማዛባት፣ ለእውነት መቆም፣ በማንኛውም ሁኔታ ከፍትህ ጎን መቆም

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**መልመጃ ሁለት**

**ሀ. ‘እውነት’ ወይም ‘ሐሰት’ በማለት መልሱ።**

1. ሐሰት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. ሐሰት 5. እውነት 6. እውነት

**ለ. ትክክለኛውን ምላሽ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. ሐ 2. ለ 3. ለ 4. ሐ 5. ሀ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ተግባር አንድ**

ስለታሪኩ ማስታወስ የቻሉትን ያህል፤ በገባቸው ቅደም ተከተል እንዲያቀርቡ ይፈቀድላቸው፤ ሲሳሳቱ ያበረታቷቸው፤ በሌላ ጊዜ ፈርተው እንዳይታቀቡ

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**መልመጃ ሦስት**

**ሀ. የሚከተሉትን ቃላት ከፍቺያቸው ጋር አዛምዱ።**

1. **ሐ** 2. **ረ** 3. **ሀ** 4. **ለ** 5. **መ** 6. **ሠ**

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር ሁለት**

ማንኛውም ታሪክ (ተረት) ተቀባይነት አለው፤ አላማው ተማሪዎቹ እንዲናገሩና እንዲደማመጡ ማድረግ ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ተግባር ሦስት**

**ቃለ መጠይቅ**

**ሀ. ለቀጣዮቹ መልሶች የሚመቹ ጥያቄዎችን አዘጋጁ፡፡**

1. *መልስሽን ተቀብለሻል?*
2. ወዴት እየሄድሽ ነው? የት ልትሄጂ አስበሻል? ወዘተ
3. ምን አይነት ፍራፍሬ ትመርጫለሽ? እስቲ የምትወጃቸውን የፍራፍሬ አይነቶች ንገሪን? ምርጫሽ የምትደርጊያቸው ፍራፍሬዎች? ወዘተ
4. እንዴት ጎበዝ ልትሆኚ ቻልሽ? ጥሩ ውጤት እንዴት ማስመዝገብ ቻልሽ? አንደኛ እንዴት ወጣሽ? ወዘተ
5. ምን አይነት ልብስ መልበስ ትወጃለሽ? ምርጫዎችሽ የትኞቹ አልባሳት ናቸው? ሰው ምን አይነት ልብስ ቢለብስ ደስ ይልሻል? ወዘተ
6. ከማን ጋር ነው የምትኖሪው? ትምህርት ቤት ከማን ጋር ትሄጃለሽ?

**ለ. ከላይ ያሟላችሁትን ጥያቄና መልስ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ጠያቂና መላሽ በመሆን ተለማመዱ፡፡**

ጥያቄና መልሱን አጥንተው በምልልስ መልክ ያቀርባሉ። (ከተማሪ መጽሐፍ ተወግዷል፤ እርስዎ ግን ሊጠቀሙት ይችላሉ)

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ተግባር አራት**

**ምን ብጠየቅ ደስ ይለኛል**

እኔ መጠየቅ የምፈልገው ብለው በመጀመር ማንኛውንም አይነት ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**መልመጃ አራት**

**እውነት/ሐሰት**

1. ሐሰት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሐሰት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ አምስት**

**አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

1. መቃኘት - መመልከት፣ እዚህም እዚያም አካባቢን ማየት
2. በርከት - በዛ፣ በመጠን ጨመር እያሉ፣ እየበዙ
3. አቅሚ - ጉልበቷ፣ ዕናቷ፣ ሀይሏ
4. እስኪበቃት- እስክትረካ፣ እስከምትችለው ድረስ፣ እስክትጠግብ
5. ዘቅዝቃ - ጎንበስ አድርጋ፣ ዝቅ አድርጋ፣ ወደ ታች ደፋ አድርጋ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**መልመጃ ስድስት**

ሰማይ፣ ሀገር፣ ዳቦ፣ ኩራዝ፣ ፈረስ፣ ትህትና፣ ሶርሳ፣ ጠረጴዛ፣ ጦጣ፣ እጅ፣ መሬት፣ ድመት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ተግባር አምስት**

እለታት፣ አንድ፣ ቀን፣ አንዲት፣ ቁራ፣ ውሃ፣ ማሰሮ፣ አንገት፣ አከባቢ፣ ጠጠሮች

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ ሰባት**

2. ጀግና 3. ዩኒቨርሲቲ 4. ተጓዥ 5. አናጢ 6. ትራክተር 7. ሌሲ 8. መምህር

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### ተግባር ስድስት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

### መልመጃ ስምንት

ወንበር፣ ሰሌዳ፣ ማፅጃ፣ ጠረጴዛ፣ ተማሪ፣ መምህር፣ ግድግዳ፣ በር፣ መስኮት፣ ጣሪያ፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ መፅሐፍ...

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

### መልመጃ ዘጠኝ

1. ሶፊያ መፅሐፍ አዋሰችኝ።
2. ዝናብ እየዘነበ ነው፡፡
3. ዛፉ ላይ ወፎች ጎጆ ሰርተዋል።
4. መንገሻ ወደ ቡሌ ሆራ ሄደ።
5. እንቆቅልሽ የሚጠይቀኝ እፈልጋለሁ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

### ተግባር ሰባት

ተማሪ፣ ቀን፣ ሐሙስ፣ መስፍን፣ ሙዝ፣ እህት፣ በር፣ ማር፣ ገጠር፣ ክፍል፣ ጠርሙስ፣ ሰው፣ ድመት…

| ባለ ሁለት ፊደል | ባለ ሦስት ፊደል | ባለ አራት ፊደል |
|---|---|---|
| ምሳ ጠጅ ፍም | መኪና ሀገር | አጠገብ ፊንድቶ |
| ቤት አለ መቶ | አገተ ተጠና | ተቀበለ መጎተት |
| መና ጎን ዳር | ገመና ብርድ | አንኳር አበረደ |
| ቁም … | ዳመና ቁርስ … | መናደድ ፊርቶን … |

# ምዕራፍ አራት

# የጊዜ አጠቃቀም

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው መልሰው እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎቹ ለደረጃው የሚመጥኑ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱና የመሰረቷቸውንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት፡፡

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፣
- የሰዓት አጠያየቅንና አመላለስን አዳምጠው ይወያያሉ፣
- የቀረበ ፅሁፍን አንብበው መልዕክቱን ይመዝናሉ፣
- የሚነበቡላቸውን አረፍተነገሮች አዳምጠው ይፅፋሉ፣
- የተውሶ ቃላትን ለይተው ያመለክታሉ፣
- ግሶችን ለይተው በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።

# 2. የትምህርት ይዘት

## .1. ማዳመጥ

- የመምህር ገለፃን ማዳመጥ
- የሚቀርብ ምንባብን ለመረዳት ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- ተራን እየጠበቁ ለመናገር ማዳመጥ

## .2. መናገር

- ሰዓትና ደቂቃን ለይቶ ጊዜን መናገር
- የተለመዱ የሰዓት መንገሪያ ቃላት መጠቀም
- ቀናትና ወራትን ለይቶ መናገር
- ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ጠቀሜታ ማስረዳት

## .3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ምልልስን ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ማንበብ
- የተውሶ ቃላትን ለይቶ ለማመልከት ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ
- የቃል ክፍልን ለይቶ ለማመልከት ማንበብ

## .4. ቃላት

- የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍቺ መፈለግ

- ለቃላት አገባባዊ ፍቺ መስጠት
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም
- ቃል ክፍልን መለየት (ግስ)

.5. **መፃፍ**

- በአሃዝ የተሰጠ ሰዓትን በፊደል (ቃል) መፃፍ
- አረፍተነገሮችን አዳምጦ መፃፍ
- በቤትና ትምህርት ቤት የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ መፃፍ
- ግሶችን ተጠቅሞ አረፍተነገሮችን መፃፍ፤ ማሟላት
- ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ግሶችን ለይቶ ማመልከት

- **የማስተማሪያ ዘዴ**
  - አሳታፊ ገለፃ
  - ልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ
  - ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
  - ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
  - ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
  - መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
  - ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ።
- **የክፍል አደረጃጀት**
  - ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
  - ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ
- **ምዘና**
  - ጊዜን መጠየቅና መናገር ችለው መተግበራቸውን ማረጋገጥ
  - በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ.መደበኛ ክትትል ማድረግ
  - አዳምጦ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
  - አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
  - ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
  - አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ፤
  - ግሶችን ለይተው ማመልከትና መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ

- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ጊዜ መናገርና መጠየቅን በተመለከተ የሚቀርብ ገለፃን አዳምጠው ይተገብራሉ

እባክዎ መምህር በቅድመማዳመጥ ደረጃ ወቅት የቀረቡትን ሦስት ጥያቄዎች እንደየልምድና ተሞክሯቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፤ ምንኛውም የሚሰጥ መልስ ተቀባይነት ይኖረዋል።

**በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ገለፃ ዝግጅት አድርገው ገለፃ ያቅርቡላቸው**

- ጊዜን በደቂቃ፣ ሰዓት፣ ቀን… ከፋፍለን እንደምንጠቀም
- ጊዜን ከፋፍሎ በአግባቡ መጠቀም ስለሚኖረው ጠቀሜታ
- በአንድ ቀን ውስጥ 24 ሰዓታት ስለመኖራቸው (ቀን/ማታ)
- ሰዓት እንዴት እንደምንጠይቅና እንደምንመልስ
- ሰዓት በመንገርም ሆነ በመጠየቅ ወቅት ትህትና መኖር እንዳለበት
- ከአምስት፣ ከአስር፣ ከሩብ፣ ከሃያ፣ ከሀያ አምስት፣ ተኩል፣ ሃያ አምስት ጉዳይ፣ ሀያ ጉዳይ፣ እሩብ ጉዳይ… ስለሚሉ አገላለፆች (ምሳሌዎችን ሰሌዳ ላይ በመፃፍ)
- በመጨረሻ ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዱ የተለያዩ ጊዜያትን የሚያመለክቱ ሰዓቶችን ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. 12፡30፣ 1፡00፣ 1፡20…
2. 1፡45፣ 2፡00፣ 2፡15…
3. 6፡00፣ 6፡30፣ 7፡00…

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

(ምንባቡ እየተነበበ የሚመለሱ፤ ማንኛውም ከጥያቄዎቹ ጋር የሚዛመድ ምላሽ ተቀባይነት አለው)

**እባክዎ መምህር የተማሪዎችዎን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ምንባቡን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። (*መጀመሪያ ፈጠን፤ ቀጥሎ ዝግ ባለ ፍጥነት*)**

እኔ በጥዋት ከእንቅልፌ ተነስቼ ቁርሴን በልቼ በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ፡፡ ትምህርት ቤቴ ስደርስ ከጓደኞቼ ጋር ሰላምታ እለዋወጣለሁ፡፡ ከዚያም ከሁሉም ተማሪዎች ጋር በመሆን የሕዝብ መዝሙር እዘምራለሁ፡፡ መዝሙሩ ሲጠናቀቅም ሰልፌን እንደጠበቅኩ ወደ ክፍሌ አመራለሁ፡፡

*1. ቀጥሎ ምን የማደርግ ይመስላችኋል?*

መማሪያ ክፍሌ ደርሼም የመጀመሪያው ክፍል ጊዜ እስከሚጀምር በጉጉት እጠብቃለሁ፡፡ ሌሎቹንም ክፍል ጊዜዎች በንቃት እሳተፋለሁ። የእረፍት ሰዓት ሲደርስ ከጓደኞቼ ጋር ወጥቼ እጫወታለሁ፡፡ ከእረፍት በኋላም ወደ ክፍላችን እመለሳለሁ፤ አራተኛው ክፍል ጊዜም ይጀመራል፡፡ ተሳትፎዬን አጠናክሬ እቀጥላለሁ። የክፍል ስራዎቼን እሰራለሁ፤ የቃል ጥያቄዎች እመልሳለሁ።

*2. በጉጉት የምጠብቀው ምኑን ነው? (~~መልስ፡ የክፍለጊዜ መጀመርን~~)*
*3. የእረፍት ሰዓቴ ሲደርስ ምን አደርጋለሁ? (~~መልስ፡ ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ~~)*

የክፍል ተሳትፎዬን በማየት ጓደኞቼ ይወዱኛል፤ መምህሮቼም ያበረታቱኛል። እኔም ጓደኞቼ እንደኔ ትምህርታቸውን በትጋት እንዲከታተሉ እመክራቸዋለሁ። በተለይ ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ሁልጊዜ አስታውሳቸዋለሁ። ብዙዎቹ የክፍል ጓደኞቼም ጥሩ ተፎካካሪ እየሆኑ ነው። ልጆች ከጓደኞቼ ጋር ስለምን እንደተመካከርን ታውቃላችሁ? አዎ ጊዜያችንን በአግባቡ እየተጠቀምን ወደፊት ጎበዝ፣ ጠንካራና ታማኝ በመሆን አገራችንን ማገልገል እንደሚገባን ነው! እናንተስ ስለጊዜ አጠቃቀምና አገርን ስለማገልገል ምን ትላላችሁ? በሚቀጥለው ትረካዬ ከትምህርት ቤት መልስ ጊዜዬን እንዴት እንደምጠቀም እነግራችኋለሁ፤ ጠብቁኝ!

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

መምህር ያለፈውን ክፍለጊዜ ትምህርት ከከለሱና የዕለቱን ካስተዋወቁ በኋላ፣ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን እንዲያነቧቸው ይጠይቋቸው፤

እባክዎ 'ጊዜዬን በአግባቡ እጠቀማለሁ እናንተስ' የሚለውን ምንባብ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው።

በመቀጠል የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን እንዲያሟሉ ይንገሯቸው።

## የድህረማዳመጥ ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የተወሰኑ ተማሪዎችን ምላሾች ይቀበሉ፤ በዚህን ወቅት ሌሎቹ ተማሪዎች የተሰጡት ምላሾች ልክ ስለመሆን አለመሆናቸው እንዲያረጋግጡ ይጋብዟቸው። የተረጋገጠውን በተራ ቁጥሩ ትይዩ ሰሌዳ ላይ ሊፅፉላቸው ይችላሉ።

### መልመጃ ሁለት

### ቃላቱን አዛምዱ።

ምንባቡን መሰረት አድርገው ቃላቱን ፅፈው እንዲያዛምዱ ይንገሯቸው። ቀጥሎም ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲያነፃፅሩ ያበረታቷቸው፤ በአማራጭነትም ደብተራቸውን ሰብስበው እርማት በማድረግ ምጋቤ ምላሽ ሊሰጧቸው ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ሰዓት አጠያየቅና አመላለስ

ይህንን ክፍለጊዜ ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ሰዓት መጠየቅንና መመለስን በአግባቡ ማካሄድ ይችላሉ።

ሰዓት አጠያየቅና አመላለስን በተመለከተ ትህትናን በተላበሰ መልኩ ማከናወን እንደሚገባ ክለሳዊ ገለፃ ይስጧቸው። (በክፍለጊዜ አንድ ቀርቦ ስለነበር)

የተወሰኑ ሰዓቶችን ፅፈውም እንዴት እንደሚነበቡ በድጋሜ እያሳተፉ ገለፃ ያቅርቡላቸው፤

ለመለማመጃም የተወሰነ ጊዜ ይስጧቸው፤ ባሉበት ጥንድ ጥንድ ሆነው ይለማመዱ።

ድጋፍ ለሚሹት ተጨማሪ ገለፃና ምሳሌ እየተዘዋወሩ ይስጧቸው፤ ቀድመው ለሚጨርሱና ማበልፀጊያ ለሚያሻቸውም ከርዕስ ጉዳዩ ሳይወጡ ተጨማሪ ስራ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ተግባር አንድ

ያለፈውን ክፍለጊዜ ይከልሱ።

የዕለቱን ትምህርት አስተዋውቀው ምሳሌ ይስጧቸው። በመቀጠል መፅሐፋቸው ላይ ያለውን ወይም እርስዎ ሰሌዳ ላይ የሚፅፉላቸውን ጊዜያት (ሰዓትና ደቂቃ) እየተመለከቱ ጥንድ ጥንድ

ሆነው ሰዓት መጠየቅንና ለተጠየቁት መመለስን እንዲለማመዱ ያድርጉ። ሁሉም ተማሪ በሂደቱ መሳተፉን ያረጋግጡ።

በመጨረሻም ናሙና ሰዓቶችን ፅፈው የተወሰኑ ተማሪዎችን (ድንገቴ በሆነ መልኩ) ይጠይቁ፤ ልክ መሆን አለመሆኑን ሌሎች ተማሪዎች ያረጋግጡ። ንቁ ተሳትፎ በማድረጋቸው አመስግነው ያበረታቷቸው። በየቤት ስራ መልክ ወላጆችን ወይም ሌላ ሰውን የቀናትና ወራትን ስያሜዎች ጠይቀው ፅፈው እንዲመጡ ይንገሯቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ተግባር ሁለት

ያለፈውን ክፍለጊዜ ያስታውሱ፤ የእለቱን ያስተዋውቁ። ጠይቀው የመጡትን የቀናትና ወራት ስያሜ መጀመሪያ በቡድን በቡድን እየሆኑ እንዲነጋገሩባቸው ያድርጉ፤ በመቀጠል የቡድን ተወካይ ተከማሪ ዘገባ ያቅርብ ቀናቱና ወራቱን አይረሴ እንዳይሆኑ በመዝሙር (ሙዚቃዊ በሆነ) መልኩ እንዲሏቸው ዝግጅት አድርገው ያለማምዷቸው

እሁድ…ሰኞ…ማክሰኞ…እሮብ…ሀሙስ… እያሉ

በተጨማሪም አንደኛው ቀን ማን ነው? (እሁድ)… አራተኛው ቀን ማን ይባላል (እሮብ)? ወዘተ እያላችሁ ተጠያየቁ፤ ወራቱንም በዚሁ መልኩ (አስራ ሦስት ወራት)

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ተግባር ሦስት

ያለፈውን ከልሰው የዕለቱን ትምህርት ካስተዋወቁ በኂላ…

ተማሪዎች ተራ በተራ እየተነሱ የአንድ ቀን ውሏቸውን (ትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት መልስ) በቃል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ገለፃቸውንም በተለያየ መልኩ እንዲያቀርቡ ያትጓቸው። ሙሉ ክፍለጊዜው ለመናገርና ለማዳመጥ ተግባር ይውላል።

አፈፃፀማቸውን እያዩ ነጥብ በመስጠት ማስታወሻዎ ላይ (የነጥብ ወረቀት) ይመዝግቡ፤ ካልተዳረሰልዎት በሌላ የመናገር ክፍለጊዜ ያሟላሉ።

ተግባር አራትን በተመለከተ መረጃ አጠናቅረው እንዲመጡ ይንገሯቸው፤ አፈፃፀሙን ያስረዷቸው

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ተግባር አራት

አባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ አዘጋጅተው የመጡትን መረጃ እንዲያጋሩ ያድርጉ፤ ለሀሳብ ፍሰቱና ተራን ጠብቆ ስለመናገር ትኩረት ይስጡ፤ በጥንድ በቡድን መጨረሻም በጋራ የሚሰራ ተግባር ነው።

በተግባር አምስት ስር ያለውን ምልልስ በየቤት ስራ መልክ አጥንተው እንዲመጡ ያሳስቧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ተግባር አምስት

የወይዘሮ ማንጠግቦሽንና የመንገደኛውን ምልልስ አጥንተው ከቻሉ በቃል ካልሆነ እያነበቡ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። ሲያቀርቡ ያበረታቷቸው። ምዘናም ያካሂዱ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## መልመጃ ሦስት

## የድህረምንባብ ጥያቄዎች

ምልልሱን መሰረት አድርገው ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ፅፈው (መፃፍን በዚያው እንዲለማመዱ) እንዲሰሯቸው ያድርጉ።

ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ምላሾቹ ላይ ይነጋገሩ፤ በመጨረሻም በጋራ ይሰራ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ተማሪዎች ይህንን የቃላት ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡ የተውሶ ቃላትን ከሌሎች ቃላት መለየት ይችላሉ

## መልመጃ አራት

## የተውሶ ቃላት

ውሰትን በተመለከተ አጭር መግለጫ ይስጧቸው

- በማንኛውም ቋንቋ ውስጥ አይቀሬ መሆኑን
- የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሰዎች ንክኪ እስካደረጉ ድረስ ውሰትም ስለማጋጠሙ
- ውሰት ተፈጥሯዊ መሆኑ፤ ውሰትን ማስቀረት እንደማይቻል

- ውሰት ሲበዛ ተገቢ አለመሆኑንና ቋንቋን ሊያቀጭጭ ስለመቻሉ
- ቋንቋው መግለጫ ቃል እያለው ለመዋስ አለመሞከር (ለምሳሌ ፍሬንድ/ጓደኛ፣ እናት/ማዘር..)
- አዳዲስ ቴክኖሎጂና ፈጠራ በየጊዜው መከሰት ከክስተቱ ውጪ ያሉ ቋንቋዎች እንዲዋሱ የሚያደርጋቸው ስለመሆኑ

ቀጥሎ የቀረበውን የአዛምድ መልመጃ (የውሰት ቃላት) ያሰሯቸው። ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው፤ በመጨረሻ ጥያቄዎቹ በጋራ ይሰሩ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች በአሀዝ የተሰጣቸውን ጊዜ (ሰዓትና ደቂቃ) በፊደል(በቃል) ይፅፋሉ፤ የሚነበቡላቸውን አረፍተነገሮች አዳምጠው ይፅፋሉ፤ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮች ይመሰርታሉ።

መምህር እባክዎ ስለግስ ቃላት አጠር ያለ ክለሳ ያቅርቡላቸው፤ ምሳሌዎችም ይስጧቸው፤ ከክለሳው በኋላም የእለቱን ትምህርት ያተዋውቋቸው፤

ምሳሌዎችንም እያሳተፉ ያቅርቡላቸው።

መልመጃውን ፅፈው እነዲሰሩ ያድርጉ፤ የፃፉትን ጥንድ ጥንድ በመሆን እየተጠያየቁ ያቅርቡ።

ጊዜ ካለ ተጨማሪ ተመሳሳይ ተግባራት ይቅረቡላቸው፤ ተማሪዎቹ ከድግግሞሹ ያተርፋሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## ተግባር ስድስት

ክለሳና የዕለቱ ትምህርት እንደተለመደው ይተዋወቅ።

መምህር እባክዎትን ተከታዮቹን አረፍተነገሮች ለተማሪዎችዎ እያነበቡ ያስፅፏቸው።

በመጨረሻም አረፍተነገሮቹ ያለስህተት (ፊደላት ግድፈትና የስርዓተነጥቦች መዛነፍ) መፃፉን ደብተራቸውን ሰብስበው በመመልከት ያረጋግጡ፤ እርማትና ምጋቤ ምላሽ ይሰጣቸው።

**የሚነበቡላቸው አረፍተ ነገሮች፡-**

1. ቁርሴን ሁልጊዜ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ እበላለሁ።
2. አማርኛ፣ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስና እንግሊዝኛ እንማራለን።
3. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው።
4. ቡርቴ ለምን ትምህርት ቤት ቀረች?
5. እህቴ በርትታ ታጠናለች፤ ህልሞቿን ታሳካለች።

6. እኛ በጊዜ ተነስተን በጋሪ ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን።
7. ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል፣ ላምና በሬ የቤት እንስሳት ናቸው።
8. ለምን ወደ ቤተመፅሐፍ አንሄድም?

## መልመጃ አምስት

የውሰት ቃላትን በተመለከተ አጭር ክለሳ ካደረጉ በኋላ፤ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ምሳሌ እየሰጡ አሳታፊ ገለፃ ያቅርቡ

- ተማሪዎቹ ስለግስ የሚያውቁት ነገር ይኖር እንደሆነ ይጠይቋቸው
- ግስ የሚባሉት ቃላት በማሰሪያ አንቀፅነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን
- ግሶች የድርጊት መገለጫዎች መሆናቸውን (በላ - የመብላት፣ ሰበረ - የመስበር)
- ምሳሌ የሚሆኑትን ሰሌዳ ላይ መፃፍ
- ተማሪዎች ግስ የሆኑ ቃላትን እንዲጠሩ መጠየቅ
- ግስ የሆኑትን ግስ ካልሆኑት ማስለየት (ቃላት አቅርቦ እንዲለዩ በመጠየቅ)

በመጨረሻም በተማሪ መፅሐፍ በሳጥኑ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ግስ የሆኑትን ለይተው እንዲፅፉና ምላሻቸውንም ከጓደኛ ጋር እንዲያመሳክሩ ማድረግ፤ በጋራ ማረጋገጥ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ተግባር ሰባት

ሰንጠረዡን ደብተራቸው ላይ ስለው(ፅፈው) እንዲያሟሉ ይጠይቋቸው፤ የፃፉትን በቡድን በቡድን ሆነው እንዲናበቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹ።

ውይይቱ ሲጠናቀቅ ማሳያ የሚሆኑ ተግባራትን ከየቡድኑ አንዳንድ ተወካይ እንዲያቀርብ ያበረታቱ።

መልመጃ ስምንትን በየቤት ስራ መልኩ ሰርተው እንዲመጡ አስቀድመው ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## መልመጃ ስድስት

ስለግስ አጭር ክለሳ ይቅረብ፤ የፃፏቸውን አረፍተ ነገሮች ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲናበቡ ይጋብዟቸው። በመጨረሻ የተወሰኑትን አረፍተነገሮች እያነበቡ ለክፍል ያቅርቡ።

ግስን አስመልክቶ የቀረበውን ማስታወሻ ከመፅሐፋቸው ላይ ይፃፉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ሰባት

ስለግስ አጭር ክለሳ፣

መልመጃውን በቀላሉ እንዲሰሩ ስለሚረዳቸው ሁለት/ሦስት ምሳሌዎች ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው።

መልመጃውን በግላቸው ደብተራቸው ላይ ፅፈው ይስሩ። ደብተራቸውንም እርስዎ ሰብስበው በማረም ምልክት ያድርጉበት (ይፈርሙበት)፣ በመጨረሻም የትኞቹ ቃላት እንደተሰመረባቸው በጋራ ተነጋገሩባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት እና አስራ ስምንት

### መልመጃ ዘጠኝ

እንደተለመደው ያለፈው ትምህርት ይከለስ፣ የእለቱ ተግባር (አረፍተ ነገሮችን ማሟላት) ይተዋወቅ

ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ይፃፏቸው፣ ግሶች የሚሏቸውን ቃላት በየአረፍተነገሮቹ ውስጥ ፈልገው እንዲያሰምሩባቸው ያትጓቸው።

እየተጋገዙ መልሰው እርማት(ማስተካከያ ካስፈለገ) ያድርጉባቸው፣ ለማሳያነት የተወሰኑትን እጅ እያወጡ ለክፍሉ እንዲያነቡ ይሁን።

### መልመጃ አስር

እንደተለመደው ያለፈው ትምህርት ይከለስ፣ የእለቱ ተግባር (አረፍተ ነገሮችን ማሟላት) ይተዋወቅ

ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ይፃፏቸው፣ በተጓደሉት ቦታዎች ግሶችን እያስገቡ አረፍተነገሮቹ የተሟሉ ማሰሪያ አንቀጾች እንዲኖራቸው ያድርጉ፣ ለዚህም ተማሪዎችዎን ያበረታቷቸው።

እየተጋገዙ መልሰው እርማት (ማስተካከያ ካስፈለገ) ያድርጉባቸው፣ ለማሳያነት የተወሰኑትን እጅ እያወጡ ለክፍሉ እንዲያነቡ ይሁን።

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የጊዜ አጠቃቀም**

ገለጻ ከመጀመሩ በፊት ለሚጠየቁት ሦስቱ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ተሞክሯቸውን መሰረት አድርገው ማናቸውንም ተያያዥ ምላሾች ሊሰጡ ይችላሉ። በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ጊዜዎች እያጠኑና እንዴት እንደሚጠሩ ጥንድ ጥንድ በመሆን እየተነጋገሩ የዕለቱን ትምህርት ያከናውናሉ፤ እርስዎም ከገለጻው በተጨማሪ ተገቢውን እገዛ እየተዘዋወሩ ያቅርቡላቸው::

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. 12፡30፣ 1፡00፣ 1፡20…
2. 1፡45፣ 2፡00፣ 2፡15…
3. 6፡00፣ 6፡30፣ 7፡00… ወዘተ እያሉ ሊመልሱ ይችላሉ

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ማናቸውም ተማሪዎቹ የሚሰጧቸው የትንበያ መልሶች
2. የክፍለጊዜ መጀመርን
3. ከጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

1. **በጊዜ** 2. **ከሁሉም ተማሪዎች ጋር** 3. **ወደ ክፍሏ** 4. **ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም**

**መልመጃ ሁለት**

1. **ለ** 2. **መ** 3. **ሠ** 4. **ሀ** 5. **ሐ**

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር አንድ**

የሚቀርቡላቸውን የሰዓት ምስሎች አይተው የመናገር ተግባርን ያከናውናሉ። (ስድስት ከአምስት፣ ለስምንት ሃያ ጉዳይ፤ ለሰባት ሃያ አምስት ጉዳይ)

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሁለት**

1. ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ እሮብ፣ ሐሙስ፣ አርብ፣ ቅዳሜ፣ እሁድ (የመጀመሪያ ቀን በመሆን የሚታወቀው እሁድ መሆኑን ግን ልብ ይሏል!)
2. መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዚያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ ጳጉሜን (አስራ ሁለቱ 30 ቀናት ሲኖራቸው፣ ጳጉሜ 5/6 ቀናት አሏት)

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ተግባር ሦስት**

ውኋቸውን በተመለከተ የሚያቀርቡት ማንኛውም ምላሽ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ተግባር አራት**

ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ያለውን ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ (ቡድናዊ)፣ አካባቢያዊና ሀገራዊ ፋይዳ በተመለከተ የሚቀርቡ ማናቸውም አወንታዊ ምላሾች ተቀባይነት አላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ተግባር አምስት**

ምልልሱን አጥንቶ በቃል ወይም እያነበቡ ማቅረብ

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**መልመጃ ሦስት**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

1. በትህትና 2. ሰዓት 3. ስድስት ተኩል 4. መንገደኛው
5. በጊዜ በአግባቡ የተጠቀሙ ሰዎች ውጤታማ ሲሆኑ፣ ያልተጠቀሙ ደግሞ ተጎጂ ናቸው
6. የየራሳቸውን መልስ ይሰጣሉ፤ ልምዳቸውን መሰረት አድርገው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ አራት**

1. **ሠ** 2. **ሐ** 3. **ሀ** 4. **ለ** 5. **መ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**አሃዝን ወደ ፊደል መቀየር**

3፡25 (ሦስት ከሃያ አምስት)፣ 6፡00 (ስድስት ሰዓት)፣ 7፡30 (ሰባት ተኩል (ከሠላሳ))፣

8፡45 (ለዘጠኝ እሩብ ጉዳይ፤ ስምንት ከአርባ አምስት) 9፡05 (ዘጠኝ ከአምስት)

10፡ 35 (ለአስራ አንድ ሃያ አምስት ጉዳይ፤ አስር ከሠላሳ አምስት)

11፡ 20 (አስራ አንድ ከሃያ) 2፡00 (ሁለት ሰዓት)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ተግባር ስድስት**

**የሚነበቡት አረፍተነገሮች**

1. ቁርሴን ሁልጊዜ አነድ ሰዓት ተኩል ላይ እበላለሁ።
2. አማርኛ፣ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስና እንግሊዝኛ እንማራለን።
3. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው።
4. ቡርቴ ለምን ትምህርት ቤት ቀረች?
5. እህቴ በርትታ ታጠናለች፤ ህልሞቿን ታሳካለች።
6. እኛ በጊዜ ተነስተን በጋሪ ወደ ትምህርት ቤት እንሄዳለን።
7. ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል፣ ላምና በሬ የቤት እንስሳት ናቸው።
8. ለምን ወደ ቤተመፅሐፍ አንሄድም?

**የተውሶ ቃላት**

**መልመጃ አምስት**

1. **ሠ** 2. **ሐ** 3. **ሀ** 4. **ለ** 5. **መ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ተግባር ሰባት**

| ስፍራ | የሚከናወኑ ተግባራት | ማከናወኛ ጊዜ |
|---|---|---|
| በቤት ውስጥ | መመገብ፣ ዜና ማየት፣ ወላጅ ማገዝ፣<br>መተኛት፣ ማብሰል፣ ልብስ ማጠብ | 1፡30<br>2፡00… |
| በትምህርት ቤት | ሰንደቅ አላማ ስነስርዓት<br>ክፍል ውስጥ ማዳመጥ<br>ማስታወሻ መያዝ<br>የክፍል ስራ መስራት… | 2፡00<br>2፡30… |

ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

**መልመጃ ስድስት**

ተፈተነ፣ አጎረሰ፣ አስመጣ፣ ነበር፣ ገመተ፣ ጠጣ፣ ተናገረ፣ ጻፈ

**ትምህርት አራት፡ መፃፍ**

ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

**መልመጃ ሰባት**

ማናቸውም ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ እስከሆኑ ድረስ ተቀባይነት አላቸው።

**ምሳሌ፡**

አስቴር ክፍል ውስጥ ተቀመጠች።

እናንተ ውድድሩን አሸነፋችሁ።

እኔ ለእናቴ ደብዳቤ ፃፍኩ። ወዘተ

ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

**መልመጃ ስምንት**

1. አሚናና ሲፈን ወደ ገበያ <u>ሄዱ</u>፡፡
2. ለእህቱ ደብዳቤ <u>ፃፈና ላከላት</u>፡፡
3. ሌባው በፖሊስ <u>ተያዘ</u>፡፡
4. ጊዜዬን ለአልባሌ ተግባር <u>አላውልም</u>፡፡
5. አዲስ ደብተር ዛሬ <u>ተገዛልኝ</u>፡፡
6. አባቴ ሰባት ሰዓት ላይ ዜና <u>ያዳምጣል</u>፡፡

ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

**መልመጃ ዘጠኝ**

1. ሂድን/አዘገምን 2. ያዝኩ/ፃፍኩ/ያዝን/ወሰድን/ፃፍን 3. እንጠቀም/ ተጠቀምን
4. እንታዘዝ/እንስማ 5. አጠናለሁ/እሰራለሁ/አነባለሁ 6. ይወዳል/ላጠ/ በላ/ አመጣልኝ
7. ሂደች/ ተጓዘች/ በረረች (ለአውሮፕላን) 8. ሞላ/ ሞልቶ ፈሰሰ/ 9. ይሻሉ/ ይገባቸዋል
10. አመነጨ/ አስገኘ

# ምዕራፍ አምስት

## መጓጓዣ

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18 )

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ብልሃትን በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ
- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው ዘገባ እንዲያቀርቡ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ምንባብ አንብበው ከነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያመሳክሩ ያበረታታሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ለቃት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ተማሪዎች ቅፅሎችን ከሌሎች የቃል አይነቶች ለይተው እንዲያውቁ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎቹ የተዘበራረቁ አረፍነገሮችን አስተካክለው እንዲፅፉ ምሪት ይሰጣሉ፤ ከጓደኞቻቸው ጋር በትብብር እንዲሰሩ ያተጋሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ፤ ቴክኖሎጂያዊ ግብዓቶችን ማስተማርን ለማሳለጥ ይጠቀማሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- አዳምጠው የቃል ዘገባ ያቀርባሉ፣
- ምንባብ አንብበው ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ያመሳክራሉ፣
- የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን አስተካክለው ይፅፋሉ፣
- ቅፅሎችን ከሌሎች ቃላት ለይተው ያመለክታሉ፣
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፣
- ቅፅሎችን ለይተው በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- የቃል ዘገባ ለማቅረብ ማዳመጥ
- አዳምጦ ለመረዳት ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- የውይይት ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- የተደመጠ ታሪክን መልሶ በመተረክ መናገር
- ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣን በተመለከተ መናገር
- የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ጠቀሜታና አሉታዊ ጎና አስልክቶ መናገር
- የእረፍት ቀን አጠቃቀምን በተመለከተ መናገር

## 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ የቀረበ ምንባብን ማንበብ
- በዜማዊ ጥያቄና መልስ ለመሳተፍ ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ማንበብ
- የመጓጓዣ አይነቶችንና ጠቀሜታን ለማወቅ ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ
- የቃል ክፍልን(ቅፅልን) ለይቶ ለማመልከት ማንበብ

## 2.4. ቃላት

- ከመጓጓዣ ጋር የተያያዙ ቃላትን ለይቶ መጠቀም

- ለቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ መፈለግ
- ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም
- ቃል ክፍልን መለየት (ቅፅል)

### 2.5. መፃፍ

- ተዘበራርቀው የተሰጡ አረፍተነገሮችን አስተካክሎ መፃፍ
- ቅፅሎችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ
- ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅፅሎችን ለይቶ ማመልከት
- ቅደም ተከተላቸው የተዛቡ አረፍተነገሮችን አስተካክሎ መፃፍ

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴል
- አሳታፊ ገለፃ
- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ (ሞዴል መሆን)፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት።

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- የመተባበር መንፈስን የሚያሰርፅ
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- የመኳኳቸ አይነቶችን ለይተው ማወቃቸውንና ስለነሱም መናገር መቻላቸውን መፈተሽ
- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ-መደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠው የቃል ዘገባ ማቅረብ መቻላቸው ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን ተደራሽ በሆነ ሁኔታ መመዘን
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ፤
- ቅፅሎችን ለይተው ማመልከትና መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ

- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች መጓጓዣንና አይነቶቹን በተመለከተ የሚቀርብ ምንባብን አዳምጠው የተለያዩ ተግባራትን ይከውናሉ

### መጓጓዣ

*መምህር እባክዎ በዛሬው ክፍለ ጊዜ አዲስ ምዕራፍ እንደሚጀመር በማብሰር፤ በዚህ ምዕራፍ ከተማሪዎቹ ምን እንደሚጠበቅ የቃል ጥቆማ ይስጡ*

*ምዕራፉንና ርዕሱን (መጓጓዣን) ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው*

*መጓጓዣ የሚለው ቃል ምንን እንደሚወክልና ተማሪዎቹ ያውቁት እንደሆነ ይጠይቋቸው::*

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ሁለቱን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች አንብበው እንዲመልሱ ይጠይቋቸው፤ ከጥያቄዎቹ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ምላሽ ተቀባይነት አለው (የ4 ወይም 5 ተማሪዎችን ምላሽ ይቀበሉ)

**ቀጥለው የተማሪዎችዎን የማንበብ አቅም ባገናዘበ መልኩ ምንባቡን ያቅርቡላቸው (ቢያንስ ሁለት ጊዜ ይነበብ)፤**

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱም ጥቂት ቆምታ እያደረጉ ያንብቡላቸው:: (ብዙ ጊዜም በነዚህ ጥያቄዎች ላይ እንዳይባክን ይሁን)

*የመጓጓዣ አይነቶችን በሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን፣ እነሱም ዘመናዊና ባህላዊ ናቸው። ዘመናዊ የሚባሉት መጓጓዣዎች መኪና፣ ባቡር፣ መርከብና አውሮፕላን የመሳሰሉት ናቸው። ባህላዊ ወይም ጥንታዊ የሚባሉት ደግሞ ጋሪ፣ ሰረገላ እና እንደግመል ባሉ ሌሎች እንስሳት አማካኝነት የሚከናወን መጓጓዣን ያካትታሉ።*

*ዘመናዊ መጓጓዣዎች ፈጣን፣ ጊዜ ቆጣቢና ምቾት የተላበሱ ሲሆን፣ ባህላዊ መጓጓዣዎቹ ግን ዘገምተኛ፣ ጊዜ የሚፈጁና ምቾት የሌላቸው ናቸው። በሌላ በኩል ዘመናዊዎቹ ውድና እንደልብ ተደራሽ አይደሉም፤ ባህላዊዎቹ ግን ወደ ተፈለገበት ቦታ ያለ ብዙ ወጪ መንቀሳቀስ የሚቻልባቸውና በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚገኙ ናቸው።*

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ማንበብዎን እንደጨረሱ የድህረማዳመጥ ጥያቄዎቹን ተማሪዎችዎን እያሳተፉ በቃል መልሷቸው:: የተወሰኑት ሲመልሱ ሌሎቹ ልክ ስለመሆን አለመሆኑ እንዲያረጋግጡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው::

### ክፍለጊዜ፡ ሁለት

የክፍለጊዜ አንድን የማዳመጥ ምንባብ ይዘት ይከልሱላቸው (ወይም ምንባቡን እንዴ ያንብቡላቸው) ከዚያም ለክፍለጊዜው የቀረቡትን ጥያቄዎች በፅሑፍ እንዲመልሱ ይንገሯቸው።

በግል የመለሱትን ይዘው ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር መልሶቹን ያነፃፅሩ፤ በመቀጠል በአነስተኛ ቡድን ይሁኑና ጥያቄዎቹን አንድ በአንድ እያነበቡ ምላሻቸውን ተራ በተራ ለቡድኑ ያጋሩ:: በመጨረሻም ከየቡድኑ አንዳንድ ተወካይ ለክፍሉ ፅብረቃ ታቅርብ/ያቅርብ

### ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### ተግባር አንድ

ተማሪዎችዎ በአካባቢያቸው ስላሉ መጓጓዣ አይነቶች፣ ምሳሌዎች፣ ጥቅምና ጉዳትና አብዛኛው ሰው የትኞቹን ለምን እንደሚጠቀም ሲወያዩ ይከታተሏቸው፤ በትብብር የመስራት ልምድን ማጎልበቻ ስለሆነም አንዱ ሲናገር ሌላው እንዲያዳምጥ፤ አንድኛው ባነሳው ሀሳብ ላይ ሌላኛው እንዲያክል ያበረታቷቸው:: በመጨረሻም እንደክፍል በየቡድናቸው በተግባሩ ላይ የቃል ዘገባ ያቅርቡ::

### ክፍለጊዜ፡ አራት

### መልመጃ ሁለት

ለቀረቡት ቃላት (**ውድ፣ ዘገምተኛ፣ ዘመናዊ፣ የሚከናወን፣ ባህላዊ፣ ምቾት**) አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ይጠይቋቸው፤ ምላሻቸው ላይ አጠር ያለ ውይይት አድርጉ::

ከዚያም በቃላቱ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱና ደብተር ተቀያይረው እንዲናበቡ ያድርጉ፤ በመጨረሻም የፃፏቸውን አረፍተ ነገሮች ለክፍሉ በንባብ ያቅርቡ።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

መምህር ተማሪዎችዎ ስለባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ አጠር ያለ ዝግጅት በክፍል ውስጥ አድርገው ንግግር እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው (ንግግሩ የክፍል ደረጃውን የሚጠብቅ፤ መቆራረጥ ወይም የሀሳብ መዛነፍ ሊታይበት እንደሚችል ይቀበሉ)፤ ለንግግራቸው መነሻ እንዲሆን መማሪያ መፅሐፉ ላይ ነጥቦች ተጠቁመዋል

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ተግባር ሦስት

መምህር እባክዎ መጀመሪያ ከአንድ ፈቃደኛ ተማሪ ጋር አጠር ያለ ልምምድ አድርገው በምሳሌነት የቀረበውን ምልልስ በዜማ ለክፍሉ ያቅርቡ። በመቀጠል አንድ ጊዜ ሁሉም ተማሪ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ምሳሌውን ይወጡት፤ በመጨረሻ የየራሳቸውን ስም እየተጠቀሙና ልምዳቸውን እያማከሉ ምሳሌውን የመሰለ ምልልስ በዜማ ይለማመዱ (ለምሳሌ ኪያ ግርማ በሚል ፈንታ የራሳቸውን ስም፣ የራሳቸውን መኖሪያ፣ የሚጓጓዙበትን ወዘተ)

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

ሁለቱን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ።

**የበረሃው መርከብ** የተሰኘውን ምንባብ ድምፅ እያሰሙ ተራ በተራ እንዲያነቡ ያድርጉ፤ ፍጥነት፣ ትክክለኛነትንና ተገቢ አገላለፅን (አቀላጥፎ ማንበብን) ይመዝኑበት፤ ሁሉም ተማሪ ተራውን እየጠበቀ ተሳታፊ ይሆናል፤ ካልተዳረሰ (ጊዜ ካበቃ) ሌሎቹ በሌላ ምንባብ ይመዘናሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

እባክዎ መምህር የበረሃው መርከብ ምንባብን አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፤ ከዚያም ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን (ከ1-4) ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ያድርጉ፤ ከዚያም ራሳቸው ወደ ምንባቡ ተመልሰው ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። ለመለሱት መልስም ከምንባቡ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ይጠይቋቸው (ስንተኛው አንቀፅ፣ ስንተኛው መስመር)፤ በመጨረሻ እንደክፍል በጋራ ይሰራ። ደብተራቸውን ሰብስበው ሊያርሙላቸው ይችላሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

### መልመጃ አራት

ከላይ በክፍለጊዜ ስምንት በተከናወነው ቅደም ተከተል መሰረት ይሰራ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## የእረፍት ቀን ጉብኝቴ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

- የቃላቱን ፍቺ (**ተፈናጠጥኩ፣ ስንጓዝ፣ እያወዛወዙ፣ ይማርካል**) እንዲገምቱ ይጋብዟቸው።
- የቅድመንባብ ጥያቄዎቹንም ልምዳቸውን እያጋሩ እንደሚመልሷቸው ይጠይቋቸው።
- ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አምስት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ስድስት

የተሰጡትን ቃላት በአገባባቸው መሰረት ፍቺ እንዲሰጧቸው ምንባቡን (**የእረፍት ቀን ጉብኝቴ**) መልሰው እንዲመለከቱት ይንገሯቸው። ለቃላቱም አውዳዊ ፍቺ ይስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| ለመጎብኘት | እንደሚፈጅ | ቀልብን |
| ተፈናጠጥኩ | መዳረሻ | እየለቀቀኝ |

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

### መልመጃ ሰባት

መልመጃውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው ይስሩ፤ ምስሎቹንም በመሳል ደብተራቸው ላይ መጠናቸውን አነስ አድርገው እንዲያኖሯቸው ያበረታቷቸው:: ጥንድ ጥንድ ሆነውም ይተራረሙ::

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

### መልመጃ ስምንት

ያለፈውን ክፊለ ጊዜ ምን እንዳከናወኑ፣ ለሁሉም ክፍለጊዜዎች እንደሚደረገው፣ በማስታወስ ያስጀምሩ፤ የዛሬውን ትምህርት ይዘት (አረፍተ ነገሮችን ማሟላት ያስተዋውቁ):: መልመጃው ደብተር ላይ ተፅፎ የሚሰራ ነው:: ሲጨርሱ እንደተለመደው ደብተራቸውን ሰብስበው እርማት ይስጧቸው::

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ዘጠኝ

እባክዎ መምህር ከክለሳና ትውውቅ በኋላ በዚህ መልመጃ ስር ተጓድለው የቀረቡትን ቃላት ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ይዘዟቸው፤ ከዚያም በየግላቸው ቃላቱን ለማሟላት ይሞክሩ፣ ያቃታቸውን ከጓናቸው ካለ ጓደኛ ጋር ሆነው ይሞክሩ፤ በመጨረሻም በአነስተኛ ቡድን ሆነው ሁሉንም ቃላት ያስተያዩ፤ እስካሁን ያልተመለሱ ካሉ ይጠይቁና ድጋፍ ያድርጉላቸው:: ሲጠናቀቅ ወደ ቀጣዩ መልመጃ ይሸጋገሩ::

### መልመጃ አስር

ከላይ አሟልተው ያዘጋጇቸውን የመጓጓዣ አይነት ምሳሌዎች የየብስ(የምድር)፣ የውሃ እና የአየር ብለው እንዲመድቧቸው ያበረታቷቸው::

በመጨረሻም ሰንጠረዡን ሰሌዳ ላይ ይፃፉትና በጋራ አሟሉት::

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ አስራ አንድ

ሀ. ጥያቄዎቹን አንዳንድ መስመር ባዶ ቦታ እየተው እንደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ይንገሯቸው:: ሲጨርሱ በባዶው ቦታ ላይ እነዚህኑ የተዛቡ አረፍ ነገሮች አስተካክለው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው

ለ. በዚህኛው ክፍል ቅደምተከተላቸው የተዛቡ አረፍተ ነገሮች ተሰጥተዋል፤ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በመነጋገር እንዲያስተካክሏቸው ይንገሯቸው በመጨረሻም ትክክለኛውን ቅደም ተከተል በጋራ ከተማሪዎቹ ጋር እየተነጋገራችሁ አስቀምጡ:: የቁጥር ቅደም ተከተሉ ሰሌዳ ላይ ይፃፍ::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## መልመጃ አስራ ሁለት

ቅፅሎችን ተጠቅመው በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን እንዲገልፁ የሚያስችል ተግባር ስለቀረበ ይህንኑ እንዲተገብሩ ያበረታቷቸው። በተማሪዎቹ መፅሐፍ ላይ ያለውን ማስታወሻ በመንተራስም ስለቅፅሎች ገለፃ ይስጧቸው። ማስታወሻውንም ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጓቸው።

በመቀጠል በምሳሌው መሰረት ጥቂት አረፍ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያትጓቸው:: ውሏችሁ አድካሚ ግን ደግሞ አስደሳችና ውጤታማ እንደነበር በመንገር ለነበራቸው ተሳትፎ አስጨብጭቡላቸው (ሁሉም ለራሱ)::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

## መልመጃ አስራ ሦስት

በተሰጡት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ቅፅሎችን ለይተው እንዲያመለክቱ ይጠበቃል:: በመሆኑም እርስዎ አስቀድመው በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተሰጠውን ምሳሌ ወይም ተጨማሪ ከራስዎ በማቅረብ መልመጃውን እዲሰሩ ምሪት ይስጧቸው:: ሰርተው ሲጨርሱም ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲተራረሙ ወይም እርስዎ እንዲያርሙላቸው ይሁን::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

## መልመጃ አስራ አራት

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ ዘመናዊና ባህላዊ መጓጓዣዎችን በተመለከተ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ይጠበቅባቸዋል:: ለዚህም ይረዷቸው ዘንድ ሁለት ምሳሌዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ተሰጥተዋል፤ እነዚህን ምሳሌዎችና ሌሎችን በማሳየነት በማቅረብ ተማሪዎችዎ የየራሳቸውን አረፍተነገሮች እዲመሰርቱ ያበረታቷቸው:: ተገቢውን ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው:: በክፍልዎ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር በርከት ያለ ከሆነ ደብተሮቻቸውን እይተለዋወጡ እንዲተራረሙም ማድረግ ይችላሉ::

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

1. በእግር፣ በጋሪ፣ በባጃጅ፣ በታክሲ፣ በባስ ወዘተ ሊሉ ይችላሉ
2. በእግር፣ በጋሪ፣ በባጃጅ፣ በታክሲ፣ በባስ ወዘተ ሊሉ ይችላሉ

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. ባዳመጡት መሰረት**

1. ስለመጓጓዣ አይነቶች
2. ሁለት፤ ባህላዊና ዘመናዊ
3. **ባህላዊ**፣ ጋሪ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ሰረገላ፣ ታንኳ፤ **ዘመናዊ** አውሮፕላን፣ መኪና፣ ባቡር፣
4. ፈጣን፣ አስተማማኝና ጊዜ ቆጣቢ በመሆናቸው ወዘተ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

1. ወደ ተፈለገበት ቦታ ያለ ብዙ ወጪ መንቀሳቀስ የሚቻልባቸውና በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚገኙ መሆኑ
2. ፈጣን፣ አስተማማኝና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ውድ መሆናቸው ወዘተ
3. ተማሪዎቹ የሚሰጡት ማንኛውም ምክንያተዊ ሀሳብ መልስ ይሆናል
4. ትራንስፖርት፤ (የተውሶ ቃል ነው)

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**ተግባር አንድ**

ተማሪዎቹ ተሞክሯቸውን መሰረት አድርገው የሚያቀርቧቸው ማብራሪያዎች ተቀባይነት አላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**መልመጃ ሁለት**

**ውድ** - ብዙ ወጪ የሚያስወጣ/ከፍ ያለ ገንዘብ የሚያስከፍል/

**ዘገምተኛ** - የማይፈጥን፣ ቀርፋፋ፣ በቀስታ የሚጓዝ

**የሚከናወን**- የሚሰራ፣ የሚፈፀም፣ የሚተገበር

**ባህላዊ** - ጥንታዊ፣ የድሮ፣ እንደነበር ያለ

**ዘመናዊ** - አዲስ፣ የቅርብ፣ ፈጠራ የታከለበት

**ምቾት** - ድሎት፣ የማይጎረብጥ፣ ደስ የሚል፣ የሚደላ

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር ሁለት**

ለመነሻነት የተሰጡትን ሀሳቦች መሰረት አድርገው ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው (በምዘና ወቅትም ለሀሳብ ፍሰትና ተጨባጭነት ቅድሚያ ይስጡ)

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሦስት**

የቀረበውን ምሳሌ መሰረት አድርገው በዜማ እንዲያቀርቡ ይበረታቱ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ምንባብ አንድ**

**የቅድመንባብ ጥያቄዎች**

1. አህያ፣ በቅሎ፣ ፈረስ፣ ግመል ወዘተ ሊሉ ይችላሉ
2. እንደየአካባቢያቸው (አዎ ወይም አይ)

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ ሦስት**

1. ሐሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሐሰት

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**መልመጃ አራት**

1. ግመል
2. ውሃ አንዴ ጠጥቶ ለረጅም ጊዜያት መቆየት ስለሚችል
3. በሳር በል/ አጥቢ/ለማዳ
4. ለምግብነት (ስጋ፣ ወተት)፤ ቆዳውን ለተለያየ አገልግሎት

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ምንባብ ሁለት**

**የእረፍት ቀን ጉብኝቴ**

**የቅድመንባብ ጥያቄዎች**

**ተፈናጠጥኩ** - ጋለብኩ/ተሰቀልኩ/...ላይ ወጣሁ

**እያወዛወዙ** - ወዲህ ወዲያ እያደረጉ

**ስንጓዝ** - ስንሄድ

**ይማርካል** - ይስባል/ ያጓጓል

ከቃላቱ ቀጥሎ ያሉት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቀደመ ልምድ መሰረት በማድረግ ይመለሳሉ፡፡ ሲያነቡ አቀላጥፎ ማንበባቸውን መመዘን

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አምስት**

1. ፈረስ 2. አራት 3. ዘመድ ለመጎብኘት
4. ከእናቱ ጋር 5. ፈረስ ላይ በመውጣቱ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ ስድስት**

**ለመጎብኘት** - ለማየት፣ ለመጠየቅ **እንደሚፈጅ**- እንደሚወስድ፣ እንደሚጨርስ

**ተፈናጠጥኩ**- ተደርቤ ወጣሁ፣ ጋለብኩ **ቀልብን**- ስሜትን፣ ሀሳብን፣ ትኩረትን

**መዳረሻ** - ማረፊያ፣ ማብቂያ፣ ማጠናቀቂያ **እየለቀቀኝ** - እየተወኝ፣ እየጠፋ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**መልመጃ ሰባት**

ከምስሎቹ ጋር ይዛመድ

1. ሠ 2. መ 3. ረ 4. ሰ 5. ሸ 6. ሀ 7. ሐ 8. ለ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**መልመጃ ስምንት**

1. ልምድ 2. ፎቆች 3. እንድከላከል 4. ዘመድ 5. ተሽከርካሪዎች 6. ጨዋታ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ ዘጠኝ**

**ሀ.** አውሮፕላን **መ.** ጋሪ **ሰ.** አውቶቢስ

**ለ.** ፈረስ **ሠ.** መርከብ **ሸ.** ጀልባ

**ሐ.** ባቡር **ረ.** ብስኪሌት **ቀ.** ሠረገላ

**መልመጃ አስር**

| **የየብስ** | **የውሃ** | **የአየር** |
|---|---|---|
| መኪና፣ ጋሪ፣ ሠረገላ፣ አውቶቡስ፣ ባቡር፣ ፈረስ | ጀልባ፣ መርከብ | አውሮፕላን |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ትምህርት አምስት፡ መጻፍ**

**መልመጃ አስራ አንድ**

**ሀ. አረፍተነገር ማስተካከል**

1. ቀይ ሹራብ ተገዛልኝ።
2. እህቴ የቤት ስራዋን በግዜ ትሰራለች።
3. አይሮፕላን የአየር ትራንስፖርት አይነት ነው።
4. እናቴ በባጃጅ ወደ ገበያ ሄደች።
5. ፍራፍሬ የሚበላ ልጅ ጤናማ ነው።

**ለ. ቅደምተከተል ማስተካከል**

ትክክለኛው ቅደም ተከተል፡ 1፣ 3፣ 8፣ 4፣ 7፣ 6፣ 5፣ 2

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ቅጽሎች**

ማንኛውም ተማሪዎቹ ቅጽሎችን በመጠቀም የሚመሰርቷቸው ተቀባይነት ያላቸው (ትርጉም አዘል መሆንናሰዋስውን መጠበቅ) አረፍተነገሮች

ሀ. ማንኛውም አካባቢያቸውን የሚገልፅ ቅፅል

**ለምሳሌ፡** ትልቅ ዛፍ፣ ትንሽ ወፍ፣ ሰፊ ሜዳ ...

ለ. ሰዋስው ህግን የተከተለና ቅፅል ያለበት ማንኛውም አረፍተነገር

**ለምሳሌ**፡ ትምህርት ቤታችን ውስጥ ትልቅ ዛፍ አለ።
ትንሽ ወፍ ስትበር አየሁ።
ልጆች የሚጫወቱበት ሰፊ ሜዳ አለ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**መልመጃ አስራ ሦስት**

1. ሰብስቤ **አሮጌ** መኪና ገዛ።
2. ቦንቱ **ነጭ** ቀሚስ ለብሳለች።
3. **ጎበዝ** ተማሪዎች ሁልጊዜ ይሸለማሉ።
4. **ዘመናዊ** መጓጓዣዎች ጊዜ ቆጣቢ ናቸው።
5. አበበች **ሰማያዊ** ቦርሳ አንጠልጥላለች።
6. መምህራችን **ትልቅ** መፅሐፍ ይዘዋል።
7. **ረጅሙ** ድልድይ ተገንብቶ አለቀ።
8. ሙስጠፋ **አዲስ** ቤት እያሰራ ነው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

ዘመናዊና ባህላዊ መጓጓዣዎችን በተመለከተ የሚመሰርቷቸው በሰዋስውና ፍቺ ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተነገሮች

# ምዕራፍ ስድስት

# ስነምግባር

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ብልሃትን በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ
- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው አስፈላጊ ነጥቦችን መልሰው እንዲናገሩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ምንባብ አንብበው ጥሩ እና መጥፎ ስነምግባርን ለይተው እንዲያመለክቱ ያነቃቃሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ለቃት ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ተማሪዎች ተገቢ ስርዓተነጥቦችን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያተጋሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በትብብር እንዲሰሩ ያስተባብራሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ፤ ቴክኖሎጂያዊ ግብዓቶችን ማስተማርን ለማሳለጥ ይጠቀማሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይጠቅማል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- አዳምጠው አስፈላጊ ነጥቦችን መልሰው ይናገራሉ፣
- ምንባብ አንብበው ጥሩና መጥፎ ስነምግባርን ይለያሉ፣
- ስርዓተነጥቦችን በአግባቡ ተጠቅመው አረፍተነገሮችን ይፅፋሉ፣
- ለቃላት መዝገበቃላዊና አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፣

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- ዋና ዋና ነጥቦችን መልሶ ለመናገር ማዳመጥ
- መጥፎና ጥሩ ስነምግባርን ለይቶ ለማወቅ ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- የቃላት ፍቺን ለማግኘት ማዳመጥ
- ግጥምን በመዝሙር መልክ መልሶ ለማቅረብ ማዳመጥ
- የውይይት ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- መጥፎና ሰናይ ስነምግባርን ለማስረዳት መናገር
- ስዕሎችን ለመግለፅ መናገር
- ጥሩ ስነምግባር የተላበሰን ሰው ባህሪያትን አስልክቶ መናገር
- ስለጥሩና መጥፎ ስነምግባር ሰዎች ባህሪያት በንፅፅር መናገር

## 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ የቀረበ ምንባብን ማንበብ
- ግጥምን በዜማ እየዘመሩ ለማቅረብ ማንበብ
- ዋና ዋና ሀሳብን ለማግኘት ማንበብ
- የጥሩና መጥፎ ስነምግባርን ልዩነት ለማወቅ ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ
- የቃል ፍቺን ለመረዳት ማንበብ

## 2.4. ቃላት

- ጥሩና መጥፎ ስነምግባር ጋር የተያያዙ ቃላትን ለይቶ መጠቀም

- ለቃላት ፍቺ መስጠት
- የተጓደሉ አረፍተነገሮችን በቃላት ማሟላት
- ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም

## 2.5. መፃፍ

- የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ማሟላት
- አጫጭር አረፍተነገሮችን መፃፍ
- ተገቢ ስርዓተነጥቦችን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮችን መፃፍ

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴል
- አሳታፊ ገለፃ
- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ (ሞዴል መሆን)፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች ለቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት።

# 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- የመተባበር መንፈስን የሚያሰርፅ
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

# 5. ምዘና

- ስለጥሩና መጥፎ ስነምግባር መለያዎች ለይተው ማወቃቸውንና ስለነሱም መናገር መቻላቸውን መፈተሽ
- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠው ዋና ዋና ሀሳቦችን ለይተው ማመልከት መቻላቸው ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን በየጊዜው ከሚታይ ለውጥ አንፃር መፈተሽ
- ለቃላት ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ተገቢ ስርዓተነጥቦችን እየተጠቀሙ መፃፍ መቻላቸውን መመርመር
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፣ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህንን የትምህርት ንዑስ ክፍል ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች አዳምጠው ዋና ዋና ነጥቦችን መልሰው መናገር ይችላሉ፤ ተራቸውን እየጠበቁ ማዳመጥና መናገር ይችላሉ መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ ከአዲስ ምዕራፍ፣ ከአዲስ ርዕሰጉዳይ (ይዘት ጋር) እየተዋወቁ መሆኑን ይንገሯቸው፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በምዕራፍ 5 ስለምን እንደተማሩ በመጠየቅ አስታውሰው ይከልሱላቸው::

**ቲቶ**

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ተማሪዎች ከምንባቡ ጋር በከፊል እንዲተዋወቁና ወደማዳመጡ ተግባር ትኩረት ሰጥተው እንዲገቡ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ::

**አሁን ምንባቡን ለተማሪዎችዎ ደረጃ በሚመጥን ፍጥነት እያነበቡ ያቅርቡላቸው::**

ቲቶ የሚባል አንድ ልጅ ነበር:: ሁልጊዜ ቤተሰቦቹን የሚያስቸግርና በሌሎች ጓደኞቹ ላይም ተንኮል የሚሰራ ነበር:: ቤተሰቦቹ ወይም ጎረቤቶች ሲልኩት እሺ ብሎ አይታዘዝም:: መጫወቻቸውን እየደበቀ ጓደኞቹን ያስለቅሳቸዋል:: ትምርት ቤት ሲሄድም በጣም ያረፍድ ነበር:: አንድ ቀን እንደለመደው በክፍል ውስጥ አለልቱ የተባለች ልጅን እርሳስ ተውሶ አልመልስም አለ:: የክፍል መምህርታቸውም ይህንን ነገር ሰማች::

**እዚህ ጋር ምንባቡን ገታ ያድርጉና ተማሪዎችዎን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎቹን ያሰሯቸው::**

1. *ቲቶ ምን ማድረግ ነበረበት?*
2. *መምህርቷ ቲቶ ላይ ምን እርምጃ የምትወስድበት ይመስላችኋል?*

መምህርቷም ቲቶ ወላጆቹን እንዲጠራ አደረገችው:: ከወላጆቹ ጋርም ቲቶ በሚያሳየው ባህሪ ዙሪያ ተወያዩ:: ቲቶም ለምን እነዚህን መጥፎ ተግባራት እንደሚፈፅም ተጠየቀ:: እሱም ያጠፋው ሁሉ ልክ እንዳልሆነ አመነ:: ቤተሰቡንና ጓደኞቹን ስላሳዘነም ይቅርታ ጠየቀ፤ አለልቱንም በክፍል ጓደኞቹ ፊት ይቅርታ አድርጊልኝ ብሎ እርሳሷን መለሰላት:: ከዚህ ጊዜ በኋላ ቲቶ ተወዳጅ፣ ለወላጆቹ ታዛዥ፣ ሰው አክባሪና ከጓደኞቹ ጋር በፍቅር የሚጫወት ሆነ:: በትምህርቱም ጎበዝ እየሆነ መጣ፤ በጥሩ ስነምግባሩም አርዓያ መሆን ጀመረ::

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

ሀ. ስለቲቶ ያዳመጡትን ምንባብ ዋናዋና ነጥቦች በቃል መልሰው እንዲናገ ያበረታቷቸው። ለዚህም አስቀድመው ታሪኩን እያስታወሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ጥቂት ደቂቃዎችን ይስጧቸው። ከዚያም እጅ እያወጡ እንዲመልሱ ያትጓቸው።

ለ. ቀጥሎ የተሰጡትን ባዶ ቦታዎች አሁንም ባዳመጡት ምንባብ ታሪክ መሰረት እንዲያሟሉ ይንገሯቸው፤ ለዚህም እባክዎ አንድ ጊዜ ምንባቡን ደግመው ያንብቡላቸው። በመጨረሻም ምላሻቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲያነፃፅሩ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## መልመጃ ሁለት

እባክዎ መምህር ተማሪዎች በክፍለጊዜ አንድ ስለአዳመጡት ምንባብ ጥቂት ነገሮችን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። በመቀጠል በዚህ መልመጃ ስር ያሉ ጥያቄዎችን ደብተራቸው ላይ ፅፈው በፅሑፍ ምላሽ እንዲሰጧቸው ያድርጉ፤ አዳምጦ የመረዳት አቅመማቸው በጣም ዝቅ ያለ ሆኖ ከተገኘ ምንባቡን ደግመው ያንብቡላቸው። በመቀጠል የሰሩትን ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲጋሩ ይጠይቋቸው። በመጨረሻም መልሶቹን እንደክፍል ተነጋገሩባቸው (በጋራ)።

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## መልመጃ ሦስት

ቃላትን የተመለከተውን አዛምድ ጥያቄ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ያድርጉ፤ በመቀጠል ባለፈው ስለቲቶ ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ቃላቱን ከፍቺያቸው ጋር ያዛምዱ። በመቀጠል በአነስተኛ ቡድን ሆነው ምላሾቹን መልሰው ይወያዩባቸው። የቡድን አባላቱ ሁሉ የቃላቱን ፍቺ ከተረዱ በኋላ በየቃላቱ እየተጋገዙ በቃል አረፍነገሮችን እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፤ አፈፃፀሙንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ። ጊዜ ካለ የቃላቱን ፍቺና የተወሰኑ አረፍተነገሮችን በቃል ለክፍሉ እንዲያቀርቡ መጋበዝ ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**መናገር** የተሰኘውን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ጥሩ ስነምግባርንና መጥፎ ስነምግባርን በተመለከተ ራሳቸውን ችለው ገለፃ መስጠት ይችላሉ

## ተግባር አንድ

መፅሐፋቸው ላይ የተሰጣቸውን ስዕል እያዩ ስለጥሩና መጥፎ ስነምግባር እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው (ለምሳሌ ክብ ሰርተው በቡድን እንዲቀመጡ ማድረግ)፤ በመጨረሻ በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ስዕሎቹን እየጠቆሙ ማብራሪያ ያቅርቡ።

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ተግባር ሁለት

በተግባር አንድ እዳከናወኑት በቡድን ቡድን በመሆን የተቧቸውን የመወያያ ነጥቦች መሰረት አድርገው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ይወያዩ። (በእኔ አመለካከት፣ ለእኔ እንደሚመስለኝ…እያሉ)ከውይይታቸው በኋላም የየቡድኑ አባላት በተናጠል ነጥቦቹን ተከፋፍለው (ዘጠኙን) ጥሩ ስነምግባር የተላበሰ ሰው ምን እንደሚያደርግ ለክፍል ተማሪዎች ይናገሩ። ስለተሳትፏቸው እያመሰገኑ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ተግባር ሦስት

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎን ስድስት ስድስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲያዋቅሩ ያድርጉ፤ ከዚያም እዚያው ቡድን ውስጥ ሦስት ሦስት ሆነው ይከፈሉና አንደኛው ንዑስ ቡድን የጥሩ ስነምግባር ሰው ባህሪ የሚላቸውን ዘርዝሮ ይፃፍ፣ ሁለተኛው ንዑስ ቡድን ደግሞ የመጥፎ ስነምግባር መገለጫ የሚላቸውን ይፃፍ፣ ከዚያም የዘረዘሯቸውን ተቀያይረው ያንብቡ፤ በመጨረሻም የቡድኑን ድምዳሜ በተወካይ በኩል ለክፍሉ ያጋሩ።

ክፍለጊዜ 8 ላይ የሚቀርበውን መዝሙር በየቤት ስራ መልክ አንብበው እንዲመጡ ያሳስቧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

### መዝሙር

እባክዎ መምህር በራስዎ ወይም ከሙዚቃ መምህር ወይም ሌላ ተሰጥኦ ካለው ባልደረባ ጋር በመሆን ግጥሙን ዜማ ሰርተውለት ክፍል ከመቅረቡ በፊት አስቀድመው ይለማመዱት። በክፍል ውስጥ የተማሪ መፅሐፍ ገልጣችሁ እያነበባችሁ በጋራ ተወጡት። በመጨረሻ ተማሪዎቹ እራሳቸውን ችለው እንዲዘምሩት ያበረታቷቸው። ግጥሙን በቃል ከያዙት

ማንበብ አያስፈልጋቸውም፤ አካላዊ እንቅስቃሴው አብሮ እየተቀናጀ እንደሚቀርብ ልብ ይሏል። (በሚቀጥለው ክፍለጊዜም ሊደግሙት ይችላሉ፤ ጠቃሚ ስነምግባራዊ ጉዳዮችን ስለያዘ)

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ የቀረበን ምንባብ አቀላጥፈው ማንበብ ይችላሉ፤ ካነበቡት ምንባብም ዋና ዋና ነጥቦችን ነቅሰው ማውጣት ይችላሉ

### ውሸታሟ ጦጣ

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

የቅድመንባብ ጥያቄዎቹን እንዲመልሷቸው ያድርጉ፣ የቃላቱን ፍቺም እንዲገምቱ ያበረታቷቸው፤ በመቀጠል ምንባቡበ መዝምታ እንዲያነቡ ይጠይቋቸው። እያነበቡም የንባብ ጊዜ ጥያቄዎቹን ይመልሱ። አፈፃፀማቸውን እያዩ ምንባቡን አንዴ በአርዓያነት ሊያነቡላቸው ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎቹን በተገቢው ሁኔታ ይመልሱ ዘንድ ምንባቡን አንዴ ደግመው በፍጥነት እንዲያነቡት ያነቃቋቸው፤ ወይም እርስዎ ያንብቡላቸው። ግልፅ ያልሆነ ነገር ሲገጥማቸውም ወደምንባቡ እየተመለሱ እንዲመለከቱ ያሳስቧቸው። በመጨረሻም ጥያቄዎቹን በጋራ ስሯቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

### መልመጃ አምስት

እንደተለመደው ያለፈው ክፍለጊዜ ይከለስ፣ የእለቱ የትኩረት ነጥብ ይነገር፤ ቃላቱን ደብተራቸው ላይ ይፃፏቸው፤ መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ በጥንድ በመጨረሻም በቡድን ስለመልሶቹ ትክክለኝነት ሀሳብ ይለዋወጡ፤ ከዚያም እንደክፍል ተነጋገሩባቸው። ቀላቱን እየተጠቀሙ አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ማድረግም ፍቺያቸውን ተማሪዎች በአግባቡ ተረድተው እንደሆን ለማረጋገጥ ይጠቅማል።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ተግባር አራት

የቀረበውን ምንባብ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ አቀላጥፎ ማንበብ አቅማቸውን ይመዝኑ (ፍጥነት፣ ትክክለኛነትና አገላለፅን)። የማንበብ ችግር ያለባቸው ሲያጋጥምዎት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት አይርሱ (ለምሳሌ ተጨማሪ የንባብ ተግባር መስጠት)። ማንበቡን ከጨረሱ በኋላም ይዘቱን በተመለከተ የቀረበውን መልመጃ በጋራ ስሩ።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ከንዑስ ትምህርቱ በኋላ ተማሪዎች ለቃላት ፍቺ መስጠት ይችላሉ፤ ጥሩና መጥፎ ስነምግባር የሚገለፅባቸውን ቃላት ለይተው በማወቅ ይጠቀማሉ።

## መልመጃ ስድስት

በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በቡድን በቡድን እየሆኑ በመተጋገዝ ጥሩ ወይም መጥፎ ባህሪን ለመግለጫነት ይውሉ እንደሆነ ይለያሉ፤ የለዩትንም በየምድባቸው በደብተራቸው ላይ ይፅፋሉ፤ ፅፈውም ያነባሉ(መፅሐፋቸው ላይ ያለውን ሰንጠረዥ እንዲጠቀሙት ይንገሯቸው)።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## መልመጃ ሰባት

ለተሰጡት ቃላት ተቃራኒ በምሳሌው መሰረት እንዲፈልጉ የበረታቷቸው። መልመጃው የሚሰራው በፅሑፍ ሲሆን መጀመሪያ በግል ይሞክሩት፣ ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በመነጋገር ይስሩ፤ በመጨረሻም በቡድን ውይይት ካደረጉባቸው በኋላ ለክፍሉ ያጋሩ፤ ጊዜ ከፈቀደም በቃል አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱባቸው ያበረታቷቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

## መልመጃ ስምንት

የቀረቡትን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ ፅፈው ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ሁለት ሦስት አረፍተነገሮችን በምሳሌነት ሰሌዳ ላይ ይስሩላቸው። በመጨረሻም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

## ተግባር አምስት

መምህር ዛሬ ተማሪችዎ የየራሳቸውን አረፍተነገሮች መስረትን ይለማመዳሉ። ስለሆነም ያለፈውን ክፍለጊዜ ትምህርት ከከለሱላቸውና የእለቱን ካስተዋወቋቸው በኋላ ምሳሌዎችን በመስጠት ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ የተመለከቷቸውን ወይም ያከናወኗቸውን ድርጊቶች በተመለከተ አረፍተነገሮችን እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ እየተዘዋወሩም አፈጻጸማቸውን ይመልከቱ። ሲጨርሱም እርማት በማድረግና ምጋቤ ምላሾችን በመስጠት ያትጓቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

## መልመጃ አስር (የመልመጃ 9 አካሄድን ይከተሉ)

የቀረቡትን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ ፅፈው ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ሁለት ሦስት አረፍተነገሮችን በምሳሌነት ሰሌዳ ላይ ይስሩላቸው። በመጨረሻም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

| ? | ። | ፤ |
|---|---|---|

እነዚህን ስርዓተነጥቦች ተጠቅመው ሁለት ሁለት አረፍተ ነገሮች ፅፈው መጀመሪያ በጥንድ፣ ቀጥሎ በቡድን እየተናበቡ ስለትክክለኛነታቸው እንዲወያዩ ያድርጉ

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ማንኛውም የተማሪዎቹን ልምድ የሚያንፀባርቅ መልስ
2. 'አይ ወይም አዎ' ብለው መቼና እንዴት የሚለውን ያስረዳሉ

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. *አለመዋሸት/ አለማታለል*
2. *ታስፈርመዋለች፤ ትመክረዋለች፤ ከትምህርት በቤት ታስባርረዋለች ወዘተ*

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

1. ወላጆቹን 2. ተወያዩ/ተነጋገሩ 3. ይቅርታ 4. ታዛዥ፣ በፍቅር

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**መልመጃ ሁለት**

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በፅሑፍ መልሱ።**

1. የአለልቱን
2. ያልተገባ ባህሪ/ስነምግባር የጎደለው ልጅ/ ወላጅን፣ ጎረቤትን፣ ጓደኛንና መምህርን ያሳዝናል፤ ስለዚህ **መልካም ስነምግባር የተላበስን እንሁን፤እንታረም፤ ስናጠፋ ይቅርታ እንጠይቅ**
3. ጓደኞቹን ተንኮል ይሰራባቸዋል፣ መጫወቻቸውን ይደብቅባቸዋል፣ ለወላጆቹም ሆነ ጎረቤቶቹ አይታዘዝም፣ የአለልቱን እርሳስ ተውሶ አልመልስም አለ
4. የቲቶ ወላጆች እንዲጠሩ አደረገች፤ በቲቶ ያልተገባ ባህሪ ዙሪያ ተወያየች
5. ቲቶ ጥፋቱን አውቆ ይቅርታ ጠየቀ
6. ተወዳጅ፣ ለወላጆቹ ታዛዥ፣ ሰው አክባሪና ከጓደኞቹ ጋር በፍቅር የሚጫወት፣ በትምህርቱም ጎበዝ፣ በጥሩ ስነምግባሩም አርዓያ የሆነ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**መልመጃ ሦስት**

አዛምድ/ቃላት 1. **ሰ** 2. **ሽ** 3. **ሠ** 4. **ሐ** 5. **ሀ** 6. **መ** 7. **ለ** 8. **ረ**

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ስዕሎቹን እያዩ ተገቢ ያልሆኑትን ስነምግባር የጎደላቸው፤ ተገቢ የሆኑትን ደግሞ የጥሩ ስነምግባር መገለጫዎች እያሉ ምላሽ ይሰጣሉ። ምክንያታቸውንም ያስረዳሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሁለት**

ተግባሩን ተከትሎ የተሰጡትን ነጥቦች (ንፅህና፣ አለባበስ፣ ሰው ማክበር፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ የሌሎች ሀሳብ ማክበር፣ ጓደኛን መውደድ፣ መታዘዝ፣ አካባቢን መንከባከብ እና ለሀገር ፍቅር መኖርን ወዘተ) በተመለከተ ከጥሩ ስነምግባር የተላበሰ ሰው የሚጠበቀውን ማንኛውንም

ሀሳባቸውን ያቀርባሉ (ተቀባይነት ያለው ሀሳብ)፤ እንደሚመስለኝ…በእኔ አመለካከት…እያሉ ይጀምሩ!

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ተግባር ሦስት**

እስካሁን ያነሷቸውን (በሌሎች ክፍለጊዜዎች) ነጥባች ሰብሰብ አድርገው ስለጥሩ ስነምግባር የተላበሰና ስለመጥፎ ስነምግባር የተላበሰ ሰው መገለጫዎች(ባህሪያት) እያነሱ ይወያያሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

***መዝሙር***

*መዝሙሩን አንብበው በዜማ ያቅርቡት፤ ማንኛውም አይረሴ የሆነ ዜማና አካላዊ እንቅስቃሴ (የጣት ጥቆማና ራስ ማወዛወዝ ያለበት)*

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ምንባብ አንድ**

***ውሸታሟ ጦጣ***

**የቅድመንባብ ጥያቄዎች**

1. አዎ/አይ፤ አዎ ካሉ የሚያውቅትን ይጠቁማሉ
2. ማንኛውም ግመታ /**ወጥመድ** - ሽምቀቆ፣ **ባህላዊ** -የተለመደ/ጥንታዊ፣ **መቆራመት**- ኩርምት ማለት/ በሚያሳዝን አቀማመጥ መቀመጥ/

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. *ጦጣዋ ቤተሰቦቿን አሯሯጠቻቸው።*
2. *የጦጣዋ ወላጆች ሮጠው ዛፍ ላይ ወጡ።*
3. *ጦጣዋን የያዛት ወጥመድ ነው።*
4. *ልጆች ጦጣዋ ምን የምትሆን ይመስላችኋል? **ማንኛውም ትንበያ***

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

***መልመጃ አራት***

1. *ታሪኩን መልሰው በቃል ይናገራሉ (ስለውሸታሚጦጣ)*
2. *ውሸት ጠቃሚ እንዳልሆነ፣ መታመንን እንደሚያጓድል*
3. *ልጃቸው ውሸታም በመሆኗ*
4. *መጥፎ ነገር፤ በሌሎች ዘንድ አለመታመን፤ መጠላት፣ መገለል*

***እውነት/ሐሰት*** *1. ሐሰት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሐሰት*

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**መልመጃ አምስት**

***አዛምድ/ቃላት*** *1.መ 2.ሠ 3.በ 4.ሸ 5.ቀ 6.ለ 7.ሐ 8.ሀ 9.ሰ 10.ረ*

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ተግባር አራት**

*ምሳሌውን መሰረት አድርገው እዚያው ምንባቡ ውስጥ ያሉትን የጥሩ ስነምግባር መገለጫዎች ይዘረዝራሉ። (እባክዎ ምንባቡን ይዩት!)*

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ ስድስት**

| ጥሩ (ሰናይ) ባህሪያት | | | መጥፎ (እኩይ) ባህሪያት | |
|---|---|---|---|---|
| ትሁት | ታዛዥ | ሰው አክባሪ | አታላይ | አኩራፊ |
| ትጉህ | ተወዳጅ | ጠንካራ | ውሽታም | አጭበርባሪ |
| ተጫዋች | ታማኝ | ጎበዝ | ተሳዳቢ | ሰነፍ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ ሰባት**

| | | |
|---|---|---|
| ጤናማ -ህመምተኛ/በሽተኛ | ጠቃሚ - ጎጂ/የማይረባ | ቁምነገር - ቀልድ/ቧልት |
| መጥላት- መውደድ/ማፍቀር | ያልተማረ- የተማረ | አለመታዘዝ - መታዘዝ |
| ልጅነት- አዋቂነት/ጎልማሳነት | ቅሬታ - ድጋፍ/ስምምነት | |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ትምህርት አምስት፡ መፃፍ**

**መልመጃ ስምንት**

1. ጌጤ ሰው አክባሪ ልጅ ናት። **(አራት ነጥብ)**
2. ሂርኮ፣ ፀዳለ፣ አሳንቴና ቴዎድሮስ ጓደኛሞች ናቸው። **(ነጠላ ሰረዝ፤ አራት ነጥብ)**
3. ሶፊያ በትምህርቷ አንደኛ ወጣች። **(አራት ነጥብ)**
4. ወደ ቤተ መፅሐፍ ለምን አንሄድም? **(ጥያቄ ምልክት)**
5. ወረቀት፣ እርሳስና ማስመሪያ ያስፈልጉኛል። **(ነጠላ ሰረዝ፤ አራት ነጥብ)**
6. መሳደብ የጥሩ ልጅ ባህሪ አይደለም። **(አራት ነጥብ)**
7. ዛሬ ክፍል ያልመጣው ማነው? **(ጥያቄ ምልክት)**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስደስት**

**ተግባር አምስት**

ተማሪዎቹ ወደትምህርት ቤት ሲመጡ ያዩትን ነገር በተመለከተ የሚጽፏቸው ማናቸውም ተቀባይነት ያላቸው አረፍተነገሮች መልስ ይሆናሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**መልመጃ ዘጠኝ**

1. በርትቼ አጠናለሁ፤ አንደኛ እወጣለሁ።
2. እንዴት የምታምር አበባ አየሁ መሰለሽ!
3. “መቼ ትመጣለህ?” አለችኝ።
4. ጤፍ፣ በቆሎ፣ ስንዴ እና ገብስ የእህል ዘር ናቸው።
5. ለምን ጠራሺኝ?
6. ገበያ እንሄዳለን፤ እህል እንሸምታለን።
7. ልዩነታችንን በውይይት መፍታት ይገባናል።
8. ተረት፣ እንቆቅልሽና አፈ ታሪክ ስነቃል ናቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

ስርዓተነጥቦቹን (? ። ፣) ተጠቅመው የሚፅፏቸው ማናቸውም አረፍተነገሮች ተቀባይነት ይኖራቸዋል፤ ሰዋስውን እስካላፋለሱ ድረስ!

# ምዕራፍ ሰባት

# ግብርና

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህሩን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው ሚና ጨዋታ እንዲጫወቱ ያበረታታሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ የቀረቡ ዋና ዋና ሀሳቦችን እንዲለዩ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች አጭር አንቀጽን አንብበው ዋናውን ሀሳብ እንዲፅፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎቹ ለቃላት ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያሟላሉ
- ተማሪዎች ተውሳከ ግሶችን ለይተው እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ ምሳሌዎች ይሰጣሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎቹ ለደረጃው የሚመጥኑ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱና የመሰረቷቸውንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተለዋወጡ እንዲተራረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት፡፡

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ምንባብ አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፣
- የቀረበ ምንባብን አንብበው ሚና ጨዋታ ይጫወታሉ፣
- አጭር አንቀፅ አንብበው ዋናውን ሀሳብ ይፅፋሉ፣
- በምንባብ ውስጥ የቀረቡ ዋና ዋና ሀሳቦችን ይለያሉ
- ከምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፣
- ተውሳከ ግሶችን ለይተው ይጠቀማሉ
- አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ምንባቡን ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- የቃላትን ፍቺ ከአውድ ለመረዳት ማዳመጥ
- ተራን እየጠበቁ ለመናገር ማዳመጥ፤ በውይይት ተሳታፊ ለመሆን

### 2.2. መናገር

- ነጋዴ ወይም ገበሬ ሆኖ ሚና ጨዋታ መጫወት
- የሚና ጨዋታውን መሰርት አድርጎ የቃል ዘገባ ማቅረብ
- መረጃ አደራጅቶ መናገር
- በውይይት መሳተፍ
- መዝሙር በጋራ መዘመር (ግብርንናን የተመለከተ)

### 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ

### 2.4. ቃላት

- የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍቺ መፈለግ
- የቃላትን አገባባዊ ፍቺ መፈለግ
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም
- ተውሳከ ግሶችን ከሌሎች ቃላት መለየት

### 2.5. መፃፍ

- አንቀፅ አንብቦ ዋናውን ሀሳብ መፃፍ
- ቃላት እያዛመዱ (እያስተካከሉ) አረፍተነገር መፃፍ
- ቃላት መርጠው አረፍተነገሮችን በማሟላት መፃፍ

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ።
- አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በመስጠት ማለማመድ

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ.መደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አንቀፅ አንበብበው ዋና ሀሳብ ማውጣት ስለመቻላቸው መፈተሽ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- ተውሳከግሶችን ከሌሎች ቃላት መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ

- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፣ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች አዳምጠውና ያዳመጡትንም መሰረት አድርገው የተለያዩ ጥያቄዎችን መመለስ ይጠበቅባቸዋል

### ክፍለጊዜ አንድ

### አንበሳና ዝሆን

መምህር እንደተለመደው የዕለቱ ትምህርት ከአዲስ ምዕራፍ እንደሚጀምር  አሳውቀውና ምዕራፉንና ርዕሱን ሰሌዳ ላይ በመፃፍ፣ ያለፈውን ምዕራፍ ዋና ዋና ነጥቦች በመከለስ ይጀምሩ።

**አንበሳና ዝሆን የተሰኘውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት የቅድመንባብ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፣ የቀረቡትን አራት ቃላት ፍቺም እንዲገምቱ ያድርጉ። ከዚያም የተማሪዎችዎን የንባብ ክሂል ደረጃ ባገናዘበ መልኩ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው (አንዴ ፈጠን አንዴ ዝግ አድርገው)።**

*አንበሳና ዝሆን በዱር ተጎራብተው የሚኖሩ እንስሳት ናቸው። አንበሳ እርሻ በማረስ፣ ዝሆን ደግሞ በከብት እርባታ ስራ ተሰማርተው ይኖራሉ። በዚህም ከሌሎች የዱር እንስሳት በተለየ ሀብታሞች ለመሆን በቅተዋል። አንበሳው ብዙ ጎተራ እህል ሲኖረው፣ ዝሆኑ ደግሞ በርካታ በረት ከብቶች አሉት። ብዙ ጊዜም ሌሎቹ እንስሳት ለልመናና ለብድር ወደእነሱ ይመጡ ነበር። ነገር ግን አንበሳም ሆነ ዝሆን ለብድርም ሆነ ለልመና የመጡትን ለአንድ ቀን ብቻ የሚሆን ይሰጧቸዋል። ከዚያም ከዛሬ በኋላ ለልመናና ለብድር እዚህ ድርሽ እንዳትሉ፣ ጠንክራችሁ ስሩና ራሳችሁን በምግብ ቻሉ ብለው ያስጠነቅቋቸዋል።*

*አንበሳና ዝሆኑ ምግብ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ እርስበርስ ካላቸው በመቀያየር ይመገቡ ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ዝሆን ሳር በል፣ አንበሳ ደግሞ ስጋ በል በመሆናቸው ነበር። ከእለታት አንዱ ቀን ዝሆን ለአያ አንበሳ አንድ ሀሳብ አቀረበለት። "እኔና አንተ እስከመቼ ምግባችንን እየተለዋወጥን እንመገባለን? አንተ የኔን ስራ ብትሰራ እኔ ደግሞ ያንተን ስራ ብንሰራ እኮ በጣም ውጤታማ እንሆናለን" አለው። አንበሳም በሀሳቡ በመስማማት "ስራና ሰሪ ተገናኙ ማለት ይሄ አይደል!" አለ። ከዚያን ግዜ ጀምሮም አንበሳ በከብት እርባታ፣ ዝሆኑም*

*በእርሻ ስራ ተሰማርተው መኖር ጀመሩ። አንበሳ ከብቶቹን ለማደለብና የተሻለ ምርት እንዲሰጡ ለማስቻል አዳዲስ አሰራሮችን ስራ ላይ አዋለ። ዝሆንም ዘመናዊ የአስተራረስ መንገዶችን በማጥናት ግብርናውን አቀለጣጠፈ። ብዙ እንስሳትንም በሰራተኝነት ቀጥረው ማሰራት ቻሉ። ለልመናና ለብድር የሚመጣ እንስሳም ጠፋ። ሁለቱም የናጠጡ ሀብታሞች በመሆን የጠንክሮ መስራት አርዓያነታቸው ለሌሎች እንስሳት ተረፈ።*

### ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

አጠቃላይ ታሪኩን (ዝሆንና አንበሳ) በቃል እንዲናገሩ ይጋብዟቸው፤ ምንባቡንም አንድ ጊዜ ፈጠን ባለ አነባበብ ያቅርቡላቸው:: በመቀጠል መልመጃውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲመልሱት ያበረታቷቸው:: እየተዘዋወሩም አፈፃፀማቸውን ይመልከቱ:: ሲጨርሱም መልሶቻቸውን ከጎናቸው ካሉ ጓደኞቻቸው ጋር እንዲያነፃፅሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው:: በመጨረሻም ጥያቄዎቹን በጋራ ስሯቸው::

### ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### ተግባር አንድ

የዛሬው ክፍለጊዜ አስደሳችና ተማሪዎች ቀደም ሲል ያዳመጡትን የአንበሳና ዝሆን ታሪክ እያስታወሱ መልሰው በቃል የሚናገሩበት ነው! ታሪክን መልሶ መናገር ህፃናቱ ሁነትን በቅደም ተከተል ማደራጀት የሚያስችል አቅምን እንዲጎናፀፉ ከማስቻሉም በላይ አንጎላቸው መረጃን የማብላላትና ይዞ የማቆየት ልምምድንም ያካሂዳል:: ስለዚህ እባክዎ መምህር ክፍለጊዜው አዝናኝና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን እያመቻቹ ተማሪዎች ታሪኩን ተራቸውን እየጠበቁ እንዲናገሩና እንዲያዳምጡ ያበረታቷቸው::

### ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ምልልስን አጥንተው የሚና ጨዋታ ይጫወታሉ (ገበሬ ወይም ነጋዴ በመሆን)፤ የቡድን ውይይት አድርገው የቃል ዘገባ ያቀርባሉ::

## ተግባር ሁለት

### ገበሬና ነጋዴ

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ አንድዱን ሚና (ገበሬ ወይም ነጋዴ) መርጠው ምልልሱን እንዲያጠኑት አስቀድመው ይገሯቸው፤ ሚናውን በዕጣ ማስያዝም ይችላሉ። ከዚያም ጥንድ ጥንድ ሆነው ይለማመዱት፣ አራት ወይም ስድስት አባላት ያሉት ቡድን እንዲመሰርቱ ያድርጉና ተራ በተራ አስቀድመው በያዙት ጥምረት (ጥንድ) ያቅርቡ (በቃል ወይም እያነበቡ)። አፈፃፀሙን ይከታተሉ፤ ተሳትፏቸውንም ያድንቁ።

### ክፍለጊዜ፡ አምስት

## መልመጃ ሁለት

መምህር በዛሬው ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ ቀደም ሲል በምልልስ ያዩትን ምንባብ መሰረት አድርገው የቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት የቃል ዘገባ ያቀርባሉ። ስለሆነም ቢበዛ አምስት አባላት ያሉት ቡድን ለዚህ ተግባር ያዋቅሩ፤ በመቀጠል አንድ የቡድኑ አባል ጥያቄውን እያነበበ ያቅርብ፤ ሌሎቻቸው አዳምጠው ምላሽ የሚሉትን በምልልሱ መሰረት ይስጡ። በዚህ መልኩ ሁሉንም ጥያቄዎች ያዳርሱ። ከዚያም አንድ ወይም ሁለት የቡድን ተወካይ ጥያቄዎቹን እያነበበ ምላሹን ለክፍሉ ያቅርብ።

ለተግባር ሶስት መስሪያ መረጃ አሰባስበውና አደራጅተው እንዲያመጡ በየቤት ስራ መልክ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ተግባር ሦስት

እባክዎ መምህር ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚሰራውን የግብርና ስራ አይነትና አሰራር ጠይቀው ያጠናቀሩትን መረጃ መሰረት በማድረግ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። በአቅርቦት ወቅትም መረጃውን ለማግኘት የተደረገን ጥረት፣ የሀሳብ ፍሰትንና የመረጃውን ተጨባጭነት እንዲሁም የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ ምዘና ያካሂዱ። ተሳትፏቸውንም ያድንቁላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ተግባር አራት

### ግብርናዬ ግብርናዬ

መምህር የተማሪዎችዎ የዛሬ ውሎ አስደሳች እንደሚሆን ከወዲሁ መገመት ይቻላል:: ምክንያቱም ተማሪዎችዎ እየዘመሩና እየተጫወቱ የግብርናን ሙያ ወሳኝነት የሚያደንቁበት ይዘት ቀርቦላቸዋል:: ለሞያው አወንታዊ አመለካከት ከወዲሁ መያዛቸውም ለወደፊት ውጤታማነታቸው መሰረት ይጥላል ተብሎ ይታሰባል::

እባክዎ መምህር እርስዎም በንቃት ግጥሙን በማጥናትና አብሮ ከተማሪዎች ጋር በመዘመር ብርታት ይሁኗቸው:: የመዝሙር ግጥሙን እያነበቡና ዜማ እያወጡበት ይለማመዱ፣ በመቀጠል ጮክ ብለው በጋራ ክፍል ውስጥ ይዘምሩ፣ ይህ ተግባር ድግግሞሽ ይፈልጋል:: በመጨረሻም ግጥሞቹን በቃላቸው ሸምድደው በመያዝ እንዲዘምሩ ይሁን:: ክፍለጊዜው ካለፈ በኋላም ቢሆን እንዲዘምሩት ያበረታቷቸው::

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## መልመጃ ሦስት

መምህር ግብርናዬ የሚለውን የመዝሙር ግጥም ከተማሪዎችዎ ጋር በዜማ ደግመው ይበሉት:: በቀጠል ተማሪዎችዎን ያቧድኗቸውና በዚህ መልመጃ ስር ያሉ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው (ለምሳሌ አቀማመጥ፣ መፅሐፍ)፣ እነሱ በቡድን ከተነጋገሩ በኋላም ጥያቄዎቹን በጋራ ከእርስዎ ጋር ሆነው ይስሯቸው ወይም የቃል ዘገባ ያስቀርቡ፣ ምዘና ያካሂዱ::

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የአቀላጥፎ ማንበብ አቅማቸው እንዲዳብር የቀረበ ምንባብን ድምፃቸውን እያሰሙ ያነባሉ፣ በተጨማሪም በጥልቀት አንብበው የተረድዖት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ::

### ዘመናዊና ባህላዊ ግብርና

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

እባክዎ መምህር ከእለቱ ትምህርት ትውውቅ በኋላ ሦስቱን የቅድመንበብ ጥያቄዎች ተማሪዎችን ይጠይቋቸውና ልምዳቸውን ከሚነበበው ምንባብ ጋር ያዛምዱላቸው::

ለጥያቄዎቹ የሚሰጡት መልሶች ከጉዳዮቹ ጋር እስከተዛመዱ ድረስ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። *ጎተደራሽ፣ ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አሰራር* የሚሉትንም ቃላት ፍቺ እንዲገምቱ ይጠይቋቸው፤ በመቀጠል ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡት ይጋብዟቸው። በንባባቸው ወቅትም የቀረቡትን የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች እየመለሱ እንዲሄዱ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

በክፍለጊዜ ዘጠኝ የተነበበውን ምንባብ ይዘት እንዲያታውሱ በማነቃቃት የአንብቦ መረዳት መልመጃ ጥያቄዎቹን እንዲሰሯቸው ያድርጉ። ለዚህም እባክዎ መምህር ተማሪዎቹን ጥያቄዎቹን መጀመሪያ ደብተሮቻቸው ላይ እንዲፅፏቸው ይዘዟቸው። ከዚያም ወደ ምንባቡ እየተመለሱ በማሰስ የተጓደሉትን እንዲያሟሉ ይጠይቋቸው። ይህንን ሲያከናውኑም እየተዘዋወሩ ቅኝት ያድርጉ እገዛ ለሚሹ ድጋፍ ያድርጉላቸው። በመጨረሻም በጋራ ተወያይታችሁ መልስ ስጡባቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

### መልመጃ አምስት

መምህር በዚህኛው መልመጃ ስርም አንብቦ መረዳት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ተማሪዎቹ በቡድን ሆነው እንዲወያዩባቸውና በትብብር ሰርተው የቃል ዘገባ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው። የጋራ ምላሽም ስጡባቸው።

በመቀጠል ለቀረቡት እምስት ቃላት (በቅድመ ምንባብ ፍቻቸውን የገመቷቸው) ፍቺ እንዲሱ ይጠየቁ፤ ፍቻቸውንም በጋራ ተነጋገሩባቸው፤ ሰሌዳ ላይ ምላሾቹን ይፃፉላቸው። በመጨረሻም እነዚሁኑ ቃላት እየተጠቀሙ የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች ፅፈው ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያትጓቸው፤ የቃላቱን ፍቺዎች በአግባቡ መረዳታቸውን ግን እርግጠኛ ይሁኑ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ይህንን ንዑስ ትምህርት ተማሪዎች ከተከታተሉ በኋላ ለቃላት ፍቺ መስጠት ይችላሉ፤ ተውሳከ ግሶችን ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ለይተው እንዲያመለክቱም ይጠበቅባቸዋል።

### መልመጃ ስድስት

መምህር እባክዎትን እነዚህን ከሁለቱ ምንባቦች የተወሰዱትን ቃላት ተማሪዎች ደብተራቸው ላይ እንዲፅፏቸው ይዘዟቸው። ከዚያም ምንባቦቹ ውስጥ ይዘውት በነበረው ፍቺ መሰረት

(በአውዳቸው) ከፍቺያቸው ጋ እንዲያዛምዷቸው ያበረታቷቸው:: ሲያጠናቅቁም ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው፤ ትክክለኛ ምላሹንም ሰሌዳ ላይ ያስፍሩላቸው::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## ተግባር አምስት

ተግባር አምስት ሁለት ክንውኖችን በውስጡ የያዘ ሲሆን፣ ተማሪዎች የእንስሳትን ልጆች ስያሜዎች እንዲማሯቸውና ከግብርና ስራ ጋር ተያይዘው ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላትን እንዲያውቁ የሚያስችሉ ናቸው:: በመሆኑም ጠይቀው የመጡትን መረጃና ከጓደኞቻቸው ያገኙትን ምላሽ መሰረት በማድረግ በትክክል መረዳታቸውን እንዲናገሩ በመጠየቅ ይለዩ:: ይህንን ተግባር ተማሪዎች ደብተራቸውን ተለዋውጠው እንዲተራረሙ በማድረግም አንዱ የሌላውን ስራ እንዲመዝን ማድረግ ይቻላል::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ክፍለጊዜ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራው የቃል ክፍላቸው ተውሳከ ግስ ለሆኑ ቃላት ይሆናል:: በመሆኑም መምህር እባክዎትን አስቀድመው ተማሪዎቹ የቀረቡትን አረፍተነገሮች እንዲያነቧው ያድርጉ፤ ትኩረትም ለተሰመረባቸው ቃላት በመስጠት ለምን ተግባር እንደዋሉ እንዲገምቱ ያነቃቋቸው:: ከዚያም ቃላቱ ተውሳከ ግስ እንደሚባሉና በግስ ላይ እየተጨመሩ በግሱ የተገለፀውን ድርጊት ወይም ሁነት ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከድግግሞሽና ከሁኔታ አንፃር የሚገልፁ መሆናቸውን ያሳውቋቸው:: ሌሎች ምሳሌ የሚሆኑም ተማሪዎቹ ራሳቸው እንዲነግሩዎት ያበረታቷቸው::

ማስታወሻውንም ከመፅሐፋቸው ላይ እንዲፅፉ ወይም እርስዎ ሰሌዳ ላይ ፅፈውላቸው እንዲገለብጡት ያድርጉ፤ ይህንንም መሰረት አድርገው የቀረበውን መልመጃ ደብተራቸው ላይ በመፃፍና ተውሳከ ግሶቹን ለይተው በማመልከት እንዲሰሩ ያንቋቸው:: በትክክል ስለመሰራቱም እየተዘዋወሩ ያረጋግጡ:: ጊዜ ከፈቀደም የሰሩትን ያርሙላቸው::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

### መልመጃ ስምንት

መልመጃ ዘጠኝ ተማሪዎች ተውሳከ ግሶችን በትክክል ለይተው አውቀው በየአረፍተነገሮቹ ውስጥ ለምን አገልግሎት እንደዋሉ ማወቅ መቻላቸውን በተግባር ለመፈተሽ በሚያስችል መልኩ የተዋቀረ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት አረፍተነገሮቹን

ደብተራቸው ላይ በመፃፍ ምላሻቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ለዚህም በቅድሚያ ከየአረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉ ግሶችን(ማሰሪያ አንቀፆችን) እንዲለዩ፣ በግሶቹ አማካኝነት የቀረበው ድርጊት/ሁነት ስለምን እንደሆነና ከዚህም ተነስተው የተውሳከ ግሶቹን ሚና እንዲለዩ ያበረታቷቸው፤ ተጨማሪ ምሳሌዎችንም ይስጧቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ዘጠኝ

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ክፍል ተውሳከ ግሶችን እየተገለገሉ ተማሪዎች አረፍነገሮችን እንዲፅፉ ይጠበቃል፤ ከዚህም በተጨማሪ የቀረቡላቸውን ቃላት እያገጣጠሙ የተሟላ አረፍ ነገረርን ይመሰርታሉ፡፡

ስለሆነም በመጀመሪያው ክፍል በክብ ሳጥኑ ውስጥ የተሰጧውን ተውሳከ ግሶች ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ይጋብዟቸው፡፡ በመቀጠልም የተጠቀሟቸው ተውሳከ ግሶች በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ምንን እንደሚገልፁ ከማሰሪያ አንቀፆቹ (ግሶቹ) አንፃር እየተመለከቱ በመናገር እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስር

በዚህ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ እንዲያነቡት አንድ አንቀፅ ቀርቦላቸዋል፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ አንቀፁን ሁለት ጊዜ እንዲያነቡት ይጠይቋቸው፡፡ አንብበው ሲጨርሱም ስላነበቡት አንቀፅ መልሰው እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡ የሚፅፉትም ዋናውን ሀሳብ ብቻ ነው፤ ወደ ዝርዝሩ አይገቡም፡፡ በመቀጠል በአነስተኛ ቡድን ሆነው የፃፉትን እየተጋሩ ይነጋገሩ፡፡ በመጨረሻም የተሻለ ነው የሚሉትን ሀሳብ ለክፍሉ በተወካይ በኩል እንዲያጋሩ ያበረታቷቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ አንድ

ቀጥለው በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት እያሰካኩ የተሟሉ አረፍነገሮች እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡ ምላሻቸውንም ያርሙላቸው፡፡ (ጊዜው ካልበቃ በየቤት ስራ መልክም ሊያሰሯቸው ይችላሉ፡፡)

**አጠቃላይ በምዕራፉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት በቃል ይከለሱ።**

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

የቃላት ፍቺ፡ **ሀብታም** - ባለፀጋ፣

**ስጋ በል** - የሚመገበው የእንስሳት ስጋን ብቻ የሆነ

**አሰራር** - አካሄድ/አተገባበር

**አርዓያነት** - ምሳሌነት/ሞዴልነት

**አንበሳና ዝሆን**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

ለሁለቱ ጥያቄዎች ዳራቸውን መሠረት አድርገው ይመልሱ፤ ማንኛውም ከጥያቄዎቹ ይዘት ያልወጣ ምላሽ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

1. በዱር ተጎራብቶ መኖር
2. በእርሻ ስራ በኋላ ላይ ወደ ከብት እርባታ
3. ቀድሞ ከብት እርባታ በኋላ ላይ በእርሻ ስራ
4. ተገቢ ስራ ተገኘ ወይም ፍላጎታችን የሆነውን ስራ ልንሰራ ነው ማለቱ ነው
5. አንበሳና ዝሆን በፈጠሩት የስራ እድል ተጠቅመው ሌሎችም ስራ ስላገኙ
6. ሰው የሚፈልገውን ወይም የሚመቸውን ስራ ቢሰራ ውጤታማ ይሆናል፤ ልመና ከተለመደ አመል ይሆንና ስራ እንዳይሰራ ምክንያት ይሆናል፤ ስለዚህ ሰውን በስራ እንዲሰማራ እድል መፍጠር ጠቃሚ ነው

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**ተግባር አንድ**

ታሪኩን በቃላቸው መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር ሁለት**

ሚና ጨዋታ መጫወት

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**መልመጃ ሁለት**

1. ሰላምታ ተለዋወጡ
2. ለገበሬው
3. አላግባብ ዋጋ አትጨምሩባቸው። ታልሆነ እኛው ደጃቸው ድረስ እናቀርብላቸዋለን።
4. ከተሜ ሸማቹ
5. በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱን ለሸማቹ ለማቅረብ
6. ገበሬው

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሦስት**

ማንኛውም ተማሪዎቹ የሚያቀርቡት ከልምዶቻቸው ጋር የተያያዙና ከተግባሩ ይዘት ያልወጣ ምላሽ ተቀባይነት አለው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ተግባር አራት**

መዝሙሩን ግጥሙን በማጥናት በዜማ ተለማምዶ ማቅረብ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**መልመጃ ሦስት**

1. የሌሎች ስራዎች ሁሉ መሰረት፤ የበላይ፤ ጠቃሚ
2. ሁሉ የሚመች
3. ግብርና ለሰው ልጆች ምግብ ፍጆታ የሚውሉትን ስለሚያቀርብ
4. አወንታዊ፤ ምክንያቱም ግብርና ምን ምን ተግባራት እንደሚከናወኑበትና የስራዎች ሁሉም አውራ መሆኑን ስለተገለፀበት
5. ሰብል(እህል) ይመረትበታል፣ ዶሮ እርባታ፣ ከብት እርባታ፣ ንብ ማነብ ወዘተ ይካሄድበታል

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ዘመናዊና ባህላዊ ግብርና**

**የቅድመንባብ ጥያቄዎች**

ከተራ ቁጥር 1- 3 ላሉት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ማንኛውንም ከጥያቄዎቹ ይዘት ያልወጡና ልምዳቸውን መሰረት ያደረጉ ምላሾችን ሊሰጡ ይችላሉ።

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ባህላዊና ዘመናዊ
2. ስለዘመናዊ ግብርና

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አራት**

1. ባህላዊ እና ዘመናዊ 2. ባህላዊ ግብርና 3. መመገብ 4. ባህላዊ ግብርና
5. ይጠይቃል፤ ዝቅተኛ ነው 6. ዘመናዊ ግብርና 7. አመርቂ 8. አመቺ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**መልመጃ አምስት**

1. ስለግብርና አይነቶች እና ስለባህላዊ ግብርና አዋጭ አለመሆን
2. በዘመናዊ ግርና፡- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የፈጠራ ስራዎችን ይጠቀማል፣ ምርት ከፍ ይላል፤ ጊዜ አይባክንም፣ የሰው ጉልበት ይቆጠባል፣ ሁልጊዜ ማሻሻያዎች ይደረግበታል፣ በጥቂት ቦታዎችና በውስን ሀብቶች አመርቂ ውጤት፣ በወቅቶች ላይ ብቻ ጥገኛ አይሆንም፣ በራሱ አመቺ ሁኔታዎችን
3. ባህላዊ ግብርና
4. ዘመናዊ ግብርና
5. 'ዘመናዊውን' እንዲሉ ይጠበቃል ከምክንያታቸውም ውስጥ በተራ ቁጥር 2 ስር ከተጠቀሱት መካከል ሊሆን ይችላል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ ስድስት**

**ሀ.** 1. **ሠ** 2. **መ** 3. **ረ** 4. **ለ** 5. **ሀ** 6. **ሐ**

**ለ.** 1. **ለ** 2. **መ** 3. **ሠ** 4. **ሐ** 5. **ሀ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ተግባር አምስት**

ሀ. 1. ግልገል/ውርንጭላ 2. ቡችላ 3. ውርንጭላ 4. ደቦል 5. ሙጭሊት
6. ጫጩት 7. ግልገል *(የፈረስ ልጅ ስያሜ ምናልባት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያለ መጠሪያን ቢያቀርቡ ተቀባይነት አለው)*

ለ. 1. ማረስ ፤ ማቆር 2. ማርባት፣ ማምረት 3. መትከል፣ መዝራት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ ሰባት**

1. አባቴ **ውጪ** ተቀመጠ።
2. እናቴ **ቅድም** ሄደች።
3. ፈረሰኛው **ወዲህ** መጣ።
4. ዶክተሯ **ክፉኛ** አዘነች።
5. አምቡላንሱ **በፍጥነት** ደረሰ።
6. ፍራፍሬው **በደንብ** በስሏል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ ስምንት**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ቦታን | 2. ሁኔታን | 3. መጠንን/ሁኔታን | 4. ጊዜን | 5. ቦታን |
| 6. ጊዜን | 7. ሁኔታን/መጠንን | 8. ሁኔታን | 9. ቦታን | 10. ጊዜን |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ትምህርት አምስት፡ መፃፍ**

**መልመጃ ዘጠኝ**

ማንኛውም ተውሳከ ግሶችን የተጠቀመና ሰዋስዋዊ የሆነ አረፍተነገር ተቀባይነት ይኖረዋል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**መልመጃ አስር**

ለትራፊክ አደጋ መከሰት ዋነኛ ምክንያቶች ሹፌሮች ናቸው፤ በዚህም በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መልመጃ አስራ አንድ**

*1. የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ ይገባል።*
*2. አናጢው ቤቱን አስውቦ ገነባው።*
*3. ሰረገላ ባህላዊ መጓጓዣ ነው።*
*4. ቀጭኔ የዱር እንስሳ ነው።*
*5. ጎበዝ ተማሪ ሁልጊዜ ያጠናል።*
*6. አውሮፕላን ዘመናዊ መጓጓዣ ነው።*

# ምዕራፍ ስምንት

# ስራ

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው የተነሱትን ነገሮች እንዲተገብሩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ምንባብን አንብበው አንድምታዊ ፍቺ እንዲሰጡ ምሪት ይሰጣሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ የቀረቡ ዋና ዋና ሀሳቦችን እንዲለዩ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች ምንባብ አንብበው አቀላጥፎ የማንበብ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ያነሳሳሉ
- ተማሪዎቹ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎች ተዛማጅ አረፍተነገሮችን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በማቅረብ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች የወደፊት እቅዳቸውን ምን መሆን እንደሚፈልጉ በማንሳት እንዲፅፉ ድጋፍ ይሰጣሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ምንባብ አዳምጠው የተነሱትን ጉዳዮች ይተገብራሉ፣
- የቀረበ ምንባብን አንብበው አንድምታዊ ፍቺ ይሰጣሉ፣
- ምን መሆን እንደሚፈልጉ በማንሳት የወደፊት እቅዳቸውን ይፅፋሉ፣
- በምንባብ ውስጥ የቀረቡ ዋና ዋና ሀሳቦችን ይለያሉ
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፣
- አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።
- ተዛማጅ አረፍተነገሮችን በአረፍተነገር ምስረታ ወቅት ይጠቀማሉ

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ለማዳመጥ ተግባር የቀረበ ምንባብን ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- የቃላትን ፍቺ ከአውድ ለመረዳት ማዳመጥ
- ተራን እየጠበቁ ለመናገር ማዳመጥ፤ በውይይት ተሳታፊ ለመሆን
- አንድምታዊ ፍቺ ለመስጠት ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- በትርፍ ጊዜያቸው ምን እንደሚያከናውኑ በተመለከተ መናገር
- ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልጉና ይህንን ለማሳካት ምን ማድረግ እንዳለባቸው አስመልክቶ መናገር
- አማራጭ እቅድን ማቅረብን በተመለከተ መናገር
- በውይይት መሳተፍ

### 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ ማንበብ
- የፅሑፍን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ማንበብ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ
- የቃላት አውዳዊ ፍቺን ለመረዳት ማንበብ

### 2.4. ቃላት

- የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ መፈለግ

- በቃላት ውስጥ ያሉ ቅጥያዎችን መፈለግ
- የተለያዩ ቃላትን በተለያዩ አወዶች መጠቀም
- ለአያያገሮች ትኩረት መስጠት

### 2.5. መፃፍ

- አንድምታን ለይቶ መፃፍ
- አያያገሮችን ተጠቅሞ አረፍተነገሮችን ማሟላት
- አያያገሮችን እየተጠቀሙ የተሟሉ አረፍተነገሮች መመስረት
- በተናጠል ያሉ አረፍተነገሮችን እያያያዙ አንድ አረፍተነገር መመስረት

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- የአንድምታዊ ፍቺ ማውጣት ብልሃትን መጠቀም
- ተማሪዎች አዳምጠው በቃል እንዲገልፁ ማትጋት፣
- ተራ በተራ የማስነበብ ስልትን መተግበር
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ።
- አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ምሳሌዎችን በመስጠት ማለማመድ

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድ፣ በቡድንና በጋራ እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢ-መደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጦ ፍሬ ነገሮችን መረዳታቸውን ማረጋገጥ
- አንቀፅ አንብበው ዋና ሀሳብ ማውጣት ስለመቻላቸው መፈተሽ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን መመዘን
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን መመዘን
- የተለያዩ አያያገሮችን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮች ማሟላታቸውንና መመስረታቸውን ማረጋገጥ
- አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀራቸውን፣ አጫጭር አረፍተ ነገሮች መፃፍ መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች አዳምጠውና ያዳመጡትንም መሰረት አድርገው ወደ ትግበራ ይሸጋገራሉ፤ ከማዳመጥ በኋላም የተለያዩ የተረድዖት ጥያቄዎችን መመለስ ይጠበቅባቸዋል

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ 8ኛው ምዕራፍ የሚጀመርበት ነው:: ስለሆነም ተማሪዎችዎ ለዚህ ዝግጁ እንዲሆኑ ምዕራፉንና ርዕሱን ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ይጀምሩ:: የቅድመንባብ ጥያቄውንም በመጠየቅ ከምንባቡ ጋር ያዛምዷቸው::

ለቅድመንባብ ጥያቄዎቹ የሚሰጧቸው ማናቸውም ይዘቱን የተመለከቱና ልምዳቸውን ያማከሉ ምላሾች ተቀባይነት አላቸው::

የቀረቡትንም ቃላት ፍቺ *(አብዝቶ፣ ማሰስ፣ ደን፣ ስንቅ)* እንዲገምቱ ያድርጉ:: በመቀጠል ምንባቡን ተገቢውን ፍጥነት ጠብቀው ያንብቡላቸው ወይም ታሪኩን አጥንተው በቃል ይተርኩላቸው::

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችንም ሰሌዳ ላይ ሊፅፉላቸው ይችላሉ::

### ሰነፉ ፌንጣና ጉንዳን

ከብዙ አመታት በፊት በአንድ ደን በበዛበት አካባቢ የሚኖር አንድ ፌንጣ ነበር። ፌንጣው መዝናናትን አብዝቶ የሚወድ ነበር። እንደ ሌሎቹ ፌንጣዎች ሁሉ እሱም የበጋውን ወቅት በጣም ይወደዋል። በተቃራኒው ስራ መስራት የማይወድና ሰነፍ ነበር። ፀሐይ ደመቅ ብላ ሙቀቷን ስትሰጥ እሱ ማሲንቆውን ይይዝና ቀኑን ሙሉ ሲዘፍንና ሲዘል ይውላል።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. *ፌንጣው የሚኖረው በ_________ አካባቢ ነው።*
2. *ሌሎች ፌንጣዎች የሚወዱት የ_______ ወቅትን ነው።*

ከጎረቤቱ ትኖር የነበረች ጉንዳን ግን ከፌንጣው በጣም ትለያለች። ቀኑን ሙሉ ስትዘልና ስትጨፍር ትውላለች? ፈፅሞ አታደርገውም። እሷ ትኩረቷ በሙሉ ስራዋ ላይ ነበር። መቼ

መዝናናት እንዳለባት ታውቃለች። ቀኑን ሙሉ ምግብ **ስታሰስና** ወደ ጉንዳን ተራራ **ስታጓጉዝ** ትውላለች። በዚህም ፌንጣ ሁልጊዜ **ያንጓጥጣትና** ይሳለቅባት ነበር። "እንደኔ ለምን እየዘፈንሽ፣ እየጨፈርሽ አትዝናኚም? ፀሐዩአ ደማቅ፣ ሰማዩ ጥርት ያለ፣ ወቅቱ በጋ ነው!" ይላታል። "በጋ በጋ ሆኖ አይቀርም፤ ክረምቱም ይመጣል፤ ይልቅስ በጊዜ **ስንቅህን** ሰብሰብ እያደረክ ብታዘጋጅ ጥሩ ነው" ትለዋለች። እርሱ ግን ፈፅሞ አይሰማትም። መልሶ ወደ ዝላዩ ይሄዳል።

3. መቼ መዝናናት እንዳለባት የምታውቀው ማን ናት?
4. ፌንጣ ምን የሚደርስበት ይመስላችኋል?

ከጊዜ በኋላ ግን የተፈራው ክረምት ደረሰ። ጉንዳኔ በጥሩ ጊዜ ያሰባሰበችውን ምግቧን እየተመገበች ከጉንዳን ተራራዋ ውስጥ ከመሰሎቿ ጋር ትኖር ጀመር። አያ ፌንጣ ግን መድረሻ አጣ፤ ረሀቡ **ሞረሞረው**። ከላይ ዝናቡ ከስር ጎርፉ **መድረሻ** አሳጡት። በዚህን ጊዜም ጎረቤቱ ጉንዳኔ ትዝ አለችው። ወደ ተራራማ ቤቷም ሄዶ ደጇን አንኳኳ። ጉንዳኔም ማን መጣ ብላ በሯን ከፍታ አየች። ከደጃፏም ያ ሰነፍ ፌንጣ በረሃብ **ተጎሳቁሎ** በክረምቱ ቅዝቃዜ ሲንቀጠቀጥ አየችው፤ አዘነችለትም። "እባክሺን እሜት ፌንጣ በረሃብ ልሞትብሽ ነው፤ የሆነ የሚበላ ነገር ፈሊጊልኝ፤ ካንቺ ዘንድም ለጥቂት ጊዜ ልቆይ" አላት። እርሷም "ያኔኮ ነግሬህ ነበር? እንደኔ ጠንክረህ መስራት ነበረብህ!" ብላው በሯን ዘግታ ወደ ውስጥ ገባች።

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በዚህ ክፍለጊዜ የተደመጠውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎችዎ ሁለቱንም (ሀ እና ለ) ደብተራቸው ላይ ፅፈው በምንባቡ መሰረት እንዲሰሯው ይንገሯቸው፡፡ እየተዘዋወሩም ምልከታ ያድርጉ፡፡ እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ታሪኩን መልሶ ማስታወስ ላይ ክፍተት ካሳዩ አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው፡፡

በመጨረሻም ከተማሪዎችዎ በጋራ መልሶቹን እየተወያያችሁ አሚሉ፡፡

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### መልመጃ ሁለት

መልመጃ ሁለት ከተነበበው ምንባብ ሀሳብ በተጨማሪ የራሳቸውንም ሀሳብ እየጨመሩና ምክንያታዊ እየሆኑ እንዲመልሱ እድል የሚፈጥርላቸው ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የተነሳውንም የአንድምታ ፍቺ ጉዳይ ልምምድ ያደርጉበታል፡፡ ስለሆነም በጥያቄዎቹ ላይ መጀመሪያ

በግል ምላሽ ይስጡባቸው፣ ቀጥሎ ሀሳባቸውን ለብጤያቸው እንዲያጋሩ ያበረታቷቸው። በመጨረሻም ሃሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያጋሩ ለተወሰኑ ተማሪዎች እድል ይሰጣቸው። ሲጨርሱ ወደ ቀጣዩ መልመጃ ያሸጋግሯቸው።

### መልመጃ ሦስት

***መልመጃ ሦስት ከተነበበው ምንባብ ውስጥ ለተገኙ ቃላት ተመሳሳይ ቃላት በመፈለግ ከጓደኛ ጋር መጋራትን የሚጠይቅ መልመጃ ነው። በመሆኑም በዚሁ መሰረት ተማሪዎች እንዲሰሩ ያትጓቸው።***

| | | | |
|---|---|---|---|
| መሞርመር | መድረሻ | መነሳቆል | ስንቅ |
| ማንጓጠጥ | ማሰስ | ማጓጓዝ | ሰነፍ |

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

መምህር ዛሬ ተማሪዎችዎ ስዕሎችን እያጠኑ እርስበርስ ሀሳብ የሚለዋወጡበት ክፍለጊዜ ነው። ስለሆነም እርስዎ አስቀድመው ምስሎቹን በማየትና ክፍል ውስጥ ሲመጡም ተማሪዎችዎን በአነስተኛ ቡድን (4 ወይም 5) ወይም በጥንድ በማጣመር ሀሳብ እንዲያንሸራሽሩና በየትኛውስ ሞያ መሰማራት እንደሚፈልጉ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤ ለምርጫቸው ምክንያቶቻቸውንም ይጠይቋቸው፤ በውይይት ወቅትም እየተዘዋወሩ ይቃኟቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሁለት

መምህር ዛሬ ተማሪዎችዎ በትርፍ ጊዜያቸው ምን ምን እንደሚያከናውኑ ልምዳቸውን ለጓደኞቻቸው የሚያጋሩበት አስደሳች ክፍለጊዜ ነው።

በመሆኑም በትርፍ ጊዜያቸው (ከትምህርት ቤት መልስ) ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ መጀመሪያ ለይ በደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩና በመቀጠል ለቡድን አባላቶቻቸው የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያነቃቋቸው፤ ለዚህም አስቀድመው በአነስተኛ ቡድን አቧድኗቸው። አፈፃፀማቸውንም እየተዘዋወሩ በመቃኘት ይመዝኑ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ተግባር ሦስት

ማንኛውም ተማሪ በህይወቱ ወደፊት ባሳካ ብሎ የሚመኘው፣ እንደእከሌ ብሆን ብሎ የሚያልመው ህልም አለው:: ብዙዎቹ ህልሞችም ከአከባቢያዊ ሁኔታዎችና ልምዶች በመነሳት የሚፈጠሩ ናቸው:: ስለሆነም ህልማቸውን ለሌሎች እንዲያጋሩ እድል ይፈጠርላቸው ዘንድ ይህ ተግባር ተዘጋጅቷል:: እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ወደፊት ምንመሆን እንደሚፈልጉ በግልፅ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤ ለዚህም ክብ ሰርተው በቡድን እንዲቀመጡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው::

የምናቅደው እቅድ በተለያዩ ምክንያቶች ሊስተጓል እንደሚችል ጥቆማ በመስጠትም የመጀመሪያው ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ ወይም አብሮ አናደኛው ባይሳካ እንደሁለተኛ የሚይዙትን እቅድ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው:: ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን ነገር ለምን መሆን እንደፈለጉም ማክንያታቸውንም አብረው እንዲገልፁ ይንገሯቸው:: ምሳሌውን አብራችሁ እዩ::

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ተግባር አራት

ይህ ተግባር ተማሪዎች በጨዋታ መልክ በቃል አረፍተ ነገር መመስረትን (ያውም በፍጥነት!) እንዲለማመዱ እድል የሚፈጥርላቸው ነው:: በመሆኑም መምህር በመጀመሪያ እርስዎ የጨዋታው አካል በመሆን ከአንድ ተማሪ ጋር ከሰሩ በኋላ ተማሪዎችዎ ያንን ተከትለው እንዲሰሩ ያበረታቷቸው (ልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ!):: ተማሪው ቃል ይጥራ እርስዎ ደግሞ በተጠራው ቃል አረፍተነገር ይመስርቱ! ሁሉም ቃል የመጥራትና በተራቸው ደግሞ አረፍተነገር የመመስረት እድል ያግኙ::

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ምንባብ አንድ

### ትጉኋ መምህርት

### የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ መሰረታዊውን አንብቦ የመረዳት ክህሎት ለመለማመድ እድል ለተማሪዎችዎ የሚፈጠርበት ነው:: ስለሆንም ተማሪዎችዎ ተነሳስያት ኑሯቸው የማንበብ

ተግባሩን እንዲከውኑ ያበረታቷቸው፤ ለዚህም የቅድመንባብ ጥያቄዎቹን ተማሪዎችዎን ከምንባቡ ለማወዳጀነት ይጠቀሙባቸው:: የተመረጡትን ቃላት ፍቺም እንዲገምቱ ይጋብዟቸው (*ሞያ፣ ባግባቡ፣ ትጉህ፣ መገሰፅ*)::

አሁን ምንባቡን በዝምታ እንዲያነቡ ምሪት ይስጧቸው:: እያነበቡም የምንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ይስሩ:: ክፍል ውስጥ በመዘዋወር ያትጓቸው::

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

ባለፈው ክፍለጊዜ ያነበቡትን 'የትጉህዋ መምህርት'ን ታሪክ አንድ ጊዜ መልሰው እንዲያነቡት ያድርጉ፤ እርስዎም ሞዴል ሆነው ቢያነቡላቸው ተማሪዎችዎ ተጠቃሚ ይሆናሉ::

የንባብ ተግባሩን ሲጨርሱም ጥያቄዎቹን መጀመሪያ በግላቸው ቀጥሎ ደግሞ በቡድን እየተወያዩ ይመልሷቸው:: በመጨረሻም የየቡድኑ ተወካይ የሆኑት ጥያቄዎቹን እያነበቡ ፅብረቃ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው::

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

### መልመጃ አምስት

በዚህ መልመጃ ከነበበው ምንባብ የተወሰዱ ቃላት ቀርበዋል:: በመሆኑም ተማሪዎችዎ ጥንድ ጥንድ በመሆን ወደ ኋላ ተመልሰው ምንባቡ ውስጥ ቃላቱ የት የት እንደሚገኙና በያዙት አውድ ምን አይነት ፍቺ እንዳላቸው እንዲገምቱ ያበረታቷቸው::

ለእያንዳንዱ ቃል የሰጡትን ፍቺም ለቡድን አባላቶቻቸው እንዲያስረዱ ይድርጉ፤ በመጨረሻም በቃላቱ ደብተራቸው ላይ አረፍተነገር እንዲፅፉ ይንገሯቸው (በወቅቱ ክፍለጊዜው ካለቀ በየቤት ስራ መልክ መስጠት ይቻላል)::

በቀጣዩ ክፍለጊዜም በተግባር አምስት ስር የተሰጡ ቃላትን ፍቺ ሰዎች (ወላጆች) ጠይቀው እንዲመጡ ያሳስቧቸው::

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### ተግባር አምስት

መምህር ተማሪዎችዎ የእነዚህን ቃላት ፍቺ ቤተሰቦቻቸውን፣ የአካባቢያቸውን ሰዎች ወይም መዝገበቃላት በመጎብኘት ፍቺ ሰጥተው እንዲመጡ አስቀድመው በየቤት ስራ መልክ

ያሰሯቸው። ሰርተው የመጡትንም ክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲጋሩ ያትጓቸው። ቀጥሎም በቃላቱ ፍቺ ላይ እንደ ክፍል ውይይት ይደረግ። በመጨረሻም ጊዜ ከፈቀደ በቃላቱ አረፍተነገሮች ይመስረትባቸው፤ ሰሌዳ ላይም ይፃፉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## መልመጃ ስድስት

*ቃላት ካላቸው መዝገበቃላዊ ፍቺ በተጨማሪ አገባባዊ ፍቺም አላቸው። አገባባዊ ፍቺንም ለማወቅ አውድን ከግምት ማስገባት ይገባል። **አውድ** ከቃል በፊት ወይም በኋላ መጥቶ የተተኳሪ ቃሉን ፍቺ እንድናውቅ ፍንጭ የሚሰጠን ነው(ለምሳሌ ከቃሉ ጋር የመጡ ሌሎች ቃላት)።*

ሀ. በአረፍተነገሮቹ ውስጥ (ከ1-5) የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ/አገባባዊ ፍቺ እንዲፈልጉ ይንገሯቸው፤ አስቀድመው ግን ደብተራቸው ላይ አረፍነገሮቹን ይፃፏቸው።

ለ. በመቀጠል በነዚሁ ቀላት እየተገለገሉ የየራሳቸውን አረፍተነገሮች እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፤ ደብተራቸውን ሰብስበውም እርማት ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## መልመጃ ሰባት

## መልመጃ ስምንት

ቅጥያዎች ለተለያየ አላማ ቃላት ላይ እየተቀጠሉ አገልግሎት ይሰጣሉ። ለጀማሪ አንባቢዎች ቃላትን እያጣመሩና እየነጠሉ መጥራትና መፃፍ የቃላት ዕውቀታቸውንና የአቀላጥፎ ማንበብና መፃፍ ችሎታቸውንም ያጎለብታል።
በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ቅጥያዎችን ከዋና ቃላት መለየትን ይለማመዳሉ። ቅጥያዎቹ በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ ላይ ይገኛሉ።

እባክዎ መምህር መልጃዎቹን መነሻ በማድረግ ለተማሪዎቹ መጀመሪያ ሰርተው ያሳዩአቸው፤ ቀጥሎ አብራችሁ ስሩ፤ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ (ቅጥያዎቹን እንዲለዩ) ያድርጉ። በነገራችን ላይ ቅጥያዎቹ ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ በዚህ ደረጃ እንዲነሳ ስለማይበረታታ ማብራሪያ አይቀርብባቸውም፤ አሁን መነጠልና ማጣመር ብቻ!
ተማሪዎቹ መልመጃውን ሰርተው ሲጨርሱ እርማት ይስጡ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ስምንት "ለ"

*መምህር እንደሁልጊዜው ትምህርቱን ያለፈውን በመከለስ የእለቱን በማስተዋወቅ ይጀምሩ፤ ሲጨርሱም የክለሳ ገለጻ ያቅርቡ።*

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎቹ የቀረቡትን አረፍተነገሮች ደብተሮቻቸው ላይ በመጻፍ ከአረፍተነገሮቹ ውስጥ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመለየት የማመመልከት ስራን ይሰራሉ። እባክዎ መምህር በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው። ተገቢ ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው። ተማሪዎችዎ ፈጥነው የሚጨርሱ ከሆነም የለዩአቸውን ቃላት የሚመስሉ ሌሎች ቃላትን ቅጥያዎቹን በመጨመር እንዲመሰርቱ ማድረግ ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

ይህ ተማሪዎች ቃላት ላይ ቅጠያዎችን በመጨመር ሌሎች አዳዲስ ቃላት መመስረትን የሚለማመዱበት ክፍለጊዜ ነው። በመሆኑም መምህር በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች ወይም ተጨማሪ ከእርስዎ በማቅርብ ለተማሪዎቹ ያስተዋውቋቸው። ምሳሌዎቹን መሰረት በማድረግም ሌሎች ቃላትን ቅጥያዎችን በመጨመር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው። እየተዘዋወሩም አፈጻጸማቸውን ይመልከቱ፤ እርማትም ይስጡበት። ተጫማሪ ቃላትን በመስጠትም በየቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡ ማድረግ ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### አያያዥ ቃላት

### መልመጃ ዘጠኝ

ይህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከአያያዦች ጋር እንዲተዋወቁና በአረፍተነገር ምስረታ ወቅትም እነዲጠቀሙባቸው እድል ይፈጥራል። በመሆኑም መልመጃዎቹን በትኩረት እንዲሰሩ ተማሪዎችዎን ያበረታቷቸው። ለዚህም ቅድመዝግጅት አድርገው ይምጡ።
በዚህ ትምህርት ስር የቀረቡትን የተጓደሉ አረፍተነገሮች ዕፊው በአያያዦች እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው። አያያዦቹን ለምን እንደመረጡም ጥንድ ጥንድ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት እንዲያስረዱ ይጠየቁ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

## መልመጃ አስር

መምህር ተማሪዎችዎ ቀደም ሲል በተማሩት ክፍለጊዜ የተጠቀሟቸውንና ሌሎች አያያገሮችን በመገልገል **መልመጃ አስርን** ይሰራሉ:: ለዚህም ይረዳቸው ዘንድ እርስዎ አስቀድመው ምሳሌዎችን ሰሌዳ ላይ ፅፈው ይስሩላቸው:: በመቀጠልም ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ደብተራቸው ላይ ፅፈው ይስሯቸው:: ሰብስበውም እርማት ይስጧቸው::

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## መልመጃ አስራ አንድ

ሌላ አያያገሮችን ተጠቅሞ አረፍተነገሮችን የመመስረት አጋጣሚ!

መምህር ዛሬም ተማሪዎችዎ አያያገሮችን በተመለከተ ልምምድ እንዲያደርጉ የሚፈቅድላቸው መልመጃ ተዘጋጅቶላቸዋል:: በነገራችን ላይ ይህ የፅሑፍ ልምምድ ተማሪዎች ወደ ሌሎች ክሂሎችም እያሸጋገሩት ሀሳብ ለመቀበያነትና ለመስጫነት ሊገለገሉበት ይቻላሉ:: ስለሆነም አያያገሮችን ለተመለከተው መለማመጃ መጋለጣቸው ጠቀሜታ አለው::

አሁን መልመጃውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ይስሩ፤ በመጨረሻም በቡድን ሆነው እየተወያዩ ማስተካከያ ያድርጉ:: በአማራጭነትም ክፍሉ በጋራ ሊሰራው ይችላል(ሁሉም ተማሪዎች)::

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. በንክሻው፣ ጠንክሮ በመስራቱ፣ ጉድጓድ ውስጥ በመኖሩ ወዘተ
2. አንበጣ ወይም ሌላ በየአካባቢው ያለ መጠሪያ
3. **አብዝቶ** - በጣም፤ **ማሰስ**- መፈለግ፤ **ደን** -ጫካ **ስንቅ-** የጉዞ ምግብ

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ደን በበዛበት 2. የበጋ 3. ጉንዳን 4. የተማሪዎቹ ማንኛውም ትንበያ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የድህረማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

ሀ. 1. ሐሰት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. ሐሰት

ለ. 1. ጎረቤታሞች 2. ስትሰራ 3. መዝናናት 4. እህል/ምግብ 5. እህል/የሚበላ/ምግብ

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**መልመጃ ሁለት**

1. አዎ የሚል መልስ ይጠበቃል፤ ነገር ግን ተማሪዎቹ የቱንም አቋም መያዝ ይችላሉ:: የልዩነት ሀሳብ ማንሳታቸውም ይበረታታል (ይከራከሩ)::
2. ሌሎች ጉንዳኖች
3. ምክንያቱም ወቅቶች ይፈራረቃሉ
4. ክረምት እንደሚመጣና ፌንጣ በክረምት የሚበላ ሊያጣ እንደሚችል

**መልመጃ ሦስት**

**መሞርሞር**- የረሃብ ስሜት መቀስቀስ

**መሳሳቆል**- መቸገር/መራቆት/አለመመቸት

**መድረሻ** - መሄጃ

**ማጓጓዝ** - ከቦታ ቦታ ማድረስ/ማስኬድ

**ማንጓጠጥ** - ማሾፍ/ማላገጥ

**ስንቅ**- ለሌላ ጊዜ የሚሆን ምግብ/በተለይ ለጉዞ/

**ሰነፍ** - መስራት እየቻለ የማይሰራ፤ ሀሞተ ቢስ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ተማሪዎቹ የሚመልሱት መልስ አሳማኝ እስከሆነ ድረስ ተቀባይነት አለው (ስዕል 1 - ገበሬ፣ ስዕል 2 (ወደ ቀኝ)- መሀንዲስ፣ ስዕል 3- ፓይሌት፣ ስዕል 4- መምህርት ስዕል 5- ሀኪም (ዶክትር)፣ ስዕል 6 - ስራ ፈጣሪ (የቢዝነስ ሴት ወይም ነጋዴ፣ ሂሳብ አዋቂ፣ ጠበቃ...)

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር ሁለት**

ማንኛውም ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የተመለከተ ምላሽ መልስ ይሆናል::

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሦስት**

ማናቸውም ተማሪዎቹ ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልጉ በተመለከተ የሚሰጧቸው ሀሳቦች ምላሽ ይሆናሉ::

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ተግባር አራት**

ማናቸውም ተማሪዎቹ የሚመሰርቷቸው አረፍተነገሮች ምላሽ ይሆናሉ። የቋንቋው ስርዓት (ሰዋስው) እስከተጠበቀ ድረስ!

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ምንባብ አንድ**

**ትጉህዋ መምህርት**

**የቅድመማንበብ ጥያቄዎች**

1. ማንኛውም የተማሪዎቹ ምላሽ፤ ከጥያቄው ይዘት እስካላፈነገጠ ድርስ
2. **ሙያ** - ስራ/ዘርፍ ፤ **ባግባቡ** - በስርዓት፤ **ትጉህ** - ጠንካራ/ብርቱ፤ **መገሰፅ** - መምከር

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. በአስተማሪነት/መምህርነት 2. እንዴት መስራትና ማጥናት እንዳለባቸው

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**የድህረማዳመጥ ጥያቄዎች**

**መልመጃ አራት**

1. የቤት ስራ አለመስራትና ማርፈድ 2. በመገሰፅ 3. በአክብሮት
4. በተግባሯ (ሰዓት ስለምታከብር፤ ተማሪዎችን በአግባቡ ስለምታስተናግድ፣ አዳዲስ መምህራን ሲመጡ በአክብሮት ስለምትቀበል ወዘተ)

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**መልመጃ አምስት**

**ሀ.** **ትገስፃቸዋለች** - ትመክራቸዋለች **መጓጓዣ** - መሄጃ/ትራንስፖርት/
**ባግባቡ** - በስርዓት/በወጉ **ትጉህ** - ብርቱ/ታታሪ/ጠንካራ
**ሞያ** - ስራ/ዘርፍ **ባልደረቦቿ**- የስራ አጋሮቿ
**የተካነች** - ችሎታው/እውቀቱ ያላት **ታከናውናለች** -ትሰራለች/ትፈፅማለች

**ለ.** የቃላቱን ፍቺ በተገቢው መንገድ ተጠቅሞ የተመሰረተ ማንኛውም ትክክለኛ መልስ (አረፍነገር) ተቀባይነት አለው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ተግባር አምስት**

**መተግበር** - መፈጸም፣ ማከናወን፤

**ዕቅድ** - ትልም፣ ራዕይ፣ ቅድመ ዝግጅት፤

**አፈፃፀም** - አተገባበር፣ አከዋወን

**መስተጓጎል** - መደነቃቀፍ፣ መሰናከል፤

**አመርቂ** - ውጤታማ፣ ፍሬያማ፣ ስኬታማ፤

**ስኬት** - ግብ፣ መድረሻ

**ትርፋማ** - ውጤታማ፣ አስደሳች፤

**ተግዳሮት** - እንቅፋት፣ አጣብቂኝ፣ ችግር

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**መልመጃ ሰባት**

**ሀ.** 1. ያለውን/የተገኘውን 3. አዘጋጃለሁ 4. አስደሳች/አጓጊ 5. አብሮ አደጎቼ/ እኩዮቼ

**ለ.** ማንኛውም ከላይ የተሰጡትን ቃላት መሰረት በማድረግ የተመሰረተ አረፍተነገር (ተቀባይነት ያለው፤ ፍቺ ያለው፤ ሰዋስውን የተከተለ)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ ስምንት**

**ሀ.** **ስለሰው** (ስለ- ሰው)፣ **አክባሪነት** (አክባሪ -ነት)፣ **አልጠጣም** (አል- ጠጣ - ም)፣ **አልዋሽም** ( አል - ዋሽ -ም)፣ **ሞኝነት** (ሞኝ - ነት)፣ **ለመሄድ** (ለ- መሄድ)፣ **ስለቀረ** (ስለ- ቀረ)፣ **ለመስራት** (ለ- መስራት)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መልመጃ ስምንት**

**ለ.** 1. ለ-ፈተና፣ እየ-ተዘጋጀ-ሁ 2. ከ-ገበያ፣ ስት-መጣ፣ እ-መንገድ፣ አስ-ቆመ- ች- ኣት
3 የ- ትራፊክ፣ ባለ-መጠንቀቅ፣ ይከሰት-ኣል (ለተማሪዎቹ አይቅረብ)
4 አል- ተናገር-ኡ-ም 5. ሰው-ነት-ኣችን-ን፣ አለ-ብን 6. አካል-ኣዊ፣ ይሰጥ- ኣል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ ስምንት**

**ሐ.** ምሳሌዎቹን መሰረት ያደረጉ ማናቸውም ቃላት (ቅጥያ ያላቸው፤ ትርጉም የሚሰጡ ምላሽ ይሆናሉ)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ትምህርት አምስት፡ መፃፍ**

**አያያዥ ቃላት**

**መልመጃ አስር**

1. ወይም 2. እና 3. ሆኖም 4. ሆኖም/ይሁን እንጂ 5. እንጂ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

1. ሰብለ ወደ ሀገሯ ለመመለስ ወስናለች ስለዚህ ጓዟን አሰናድታለች።
2. ታሲሳ ወደ ኢሉባቦር ወይም ወደ ወለጋ ይሄዳል።
3. ኬሪያ እና መገርቱ ሽቀጣሽቀጥ ይሸጣሉ።
4. ብሩህ እና ፀሐያማ ቀን ደስ ይለኛል።
5. እናቴ ናፍቃኛለች ስለዚህ ስልክ እደውልላታለሁ።
6. ዛፍ መትከል አለብን ያለበለዚያ በአየር ሙቀት መጨመር የተነሳ እንጠፋለን።
7. ጠንክሮ መስራት ያስከብራል፤ ሌብነት ግን ያሳፍራል።

**(በመልስነት ሌሎች አማራጮችም ሊኖሩ ይችላሉ፤ ሰዋሰውን የጠበቁና ከዋናዎቹ አረፍተነገሮች ሀሳብ እስካልወጡ ድረስ)**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መልመጃ አስራ አንድ**

ማንኛውም ሰዋስውን የጠበቀና የተሰጡትን አያያገሮች ተጠቅሞ የተፃፈ ተቀባይነት ያለው አረፍተነገር ምላሽ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ባህል

## (የክፍለ ጊዜ ብዛት 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ብልሃትን በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ
- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ (ቴክስት) አዳምጠው ያዳመጧቸውን ጉዳዮች እንዲተገብሩ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ምንባብ አንብበው ከነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያመሳክሩ ያበረታታሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ቃላትን አንብበው አንድምታዊ ፍቺ እንዲሰጡ ምሳሌዎችን በማሳየት ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ተወስነው የሚሰጧቸውን ቃላት ተጠቅመው አረፍነገሮችን እንዲመሰርቱ ያተጋሉ
- ተማሪዎች በደረጃው ለሚገጥሟቸው አዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች መስተዋድዶችን ከሌሎች የቃል አይነቶች ለይተው እንዲያውቁ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎች እንቆቅልሾችን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ እዲጠያየቁ ተግባዊ ድጋፍ ያደርጋሉ
- ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር በትብብር እንዲሰሩ ምሪት ይሰጣሉ፤ ያነቃቃሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ፤ ቴክኖሎጂያዊ ግብዓቶችን ማስተማርን ለማሳለጥ ይጠቀማሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- በምንባብ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮችን አዳምጠው ይተገብራሉ፣
- ምንባብ አንብበው ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ያመሳክራሉ፣
- ምንባብ አንብበው ለቃላት አንድምታዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- መስተዋድዶችን ከሌሎች ቃላት ለይተው ያሳያሉ፣
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፣
- ቅደም ተከተላቸው የተዛቡ አረፍተነገሮችን አስተካክለው ይፅፋሉ
- መስተዋድዶችን ለይተው በአረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- ምንባብን አዳምጠው በውስጡ ያሉ ጉዳዮችን ለመተግበር ማዳመጥ
- በእንቆቅልሽ ጨዋታ ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ
- ለቃላት አንድምታዊ ፍቺ ለመስጠት ማዳመጥ
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመስጠት ማዳመጥ
- የጭውውትና ውይይት ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- በጭውውት ተሳታፊ ለመሆን መናገር
- እንቆቅልሽ በመጠየቅ ሂደት እየተሳተፉ መናገር
- የባህልን ጠቀሜታ በተመለከተ ራስን ችሎ መናገር

- ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚደረግ የቡድን ውይይት ወቅት መናገር

## 2.3. ማንበብ

- አቀላጥፎ ማንበብን ለመለማመድ የቀረበ ምንባብን ማንበብ
- እንቆቅልሾችን አንብቦ መጠየቅ
- አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ማንበብ
- የቃላት አንድምታዊ ፍቺን ለመስጠት ማንበብ
- አንድምታዊ ተረድኦት ላይ ለመድረስ ማንበብ
- የቃል ክፍልን(መስተዋድድን) ለይቶ ለማመልከት ማንበብ

## 2.4. ቃላት

- ተወስነው የሚሰጡ ቃላትን በመጠቀም አረፍተነገሮችን መመስረት
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት
- ቃላትን በተለያዩ አውዶች መጠቀም
- ቃል ክፍልን መለየት (መስተዋድድን)

## 2.5. መፃፍ

- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን እየፃፉ እንቆቅልሽ መጠየቅ
- መስተዋድዶችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ
- ከአረፍተ ነገሮች ውስጥ መስተዋድዶችን ለይቶ ማመልከት
- ቅደም ተከተላቸው የተዛቡ አረፍተነገሮችን አስተካክሎ መፃፍ

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴል
- አሳታፊ ገለፃ
- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ (ሞዴል መሆን)፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት።

# 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- የመተባበር መንፈስን የሚያሰርፅ

- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- እንቆቅልሾችን በመጠየቅና በመመለስ ሂደት በንቃት መሳተፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ያዳመጡትን መተግበር መቻላቸውን መፈተሽ
- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠው አንድምታዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን ተደራሽ በሆነ ሁኔታ መመዘን
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- የተዘበራረቁ አረፍተነገሮችን መልሰው ማወቀር መቻላቸውን
- መስተዋድዶችን ለይተው ማመልከትና መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፤ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ከተሳተፉ በኋላ ተማሪዎች እንቆቅልሽ አዳምጦ መመልስና መጠየቅ ይችላሉ፤ ተራቸውን ጠብቀው ማዳመጥን ይተገብራሉ

### እንቆቅልሽ

## ተግባር አንድ

እንቆቅልሽንና እንቆቅልሽን በተመለከተ ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎቹ መምህር ለሚሰጡት ገለፃ ማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ማበረታታት፤ መምህር እባክዎ ለቅድመ ማዳመጥ ተግባር የተዘጋጁ ጥያቄዎቹን ተማሪዎችዎን ይጠይቋቸው:: የቀረበውን ስዕል እንዲያጠኑት ማድረግም ይቻላል::

መምህር እባክዎን እንቆቅልሽን በተመለከተ ለተማሪዎች ገለፃ ያቅርቡ:: ገለፃው እንቆቅልሽ ምን እነደሆነ፣ እንቆቅልሽ እንዴት እንደሚተገበር፤ ምን ተብሎ እንደሚጀመርና ምንተብሎ እንደሚጠናቀቅ (ተማሪዎች ስለዚሁ ተሞክሯቸውን እንዲናገሩ መጠየቅ)፣ እንቆቅልሽ

በመጠየቅና በመመለስ ተግባር መሳተፍ ምን ጠቀሜታ እንዳለው (ወዳጅነትን ያጠናክራል፤ አዕምሮን ያሰላል፤ መንፈስን ያድሳል)፤ በመጨረሻም ምሳሌ የሚሆኑ እንቆቅልሾችን በመጠየቅ ተግባራዊ ማድረግ፤ በጨዋታው ሂደትም ትክክለኛውን አጠያየቅና አመላለስ መከተል (ጠያቂና መላሽ ምን ያደርጋሉ፤ መላሽ ሲሳሳት ምን ይሆናል ወዘተ)።
በመጨረሻም እንቆቅልሽ መጠየቅና መመለስን ተማሪዎቹ እንዲተገብሩት (የስሩ ደረጃ ያድርጉ)

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## ንቁው ልጅ

### *ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች*

*መምህር ተማሪዎችዎ ወደ ማዳመጡ ተግባር እንዲገቡ ስለሚያስችላቸው የቀረቡትን* ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። የቀረቡትን ቃላት ፍቺ እንዲገምቱም ይጋብዟቸው (ኩንታል፣ አሸለበ፣ መቀጣት፣ የተጋጠ)።
በመቀጠል ምንባቡን ቢያንስ ሁለት ጊዜ የተማሪዎችዎን ደረጃ በጠበቀ መልኩ ያንብቡላቸው፤ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችንም ያሰሯቸው።

***ንቁው ልጅ***

*1. ርዕሱን አይታችሁ ምንባቡ ስለምን የሚነግረን ይመስላችኋል?*

***የነዚህን ቃላት ፍቺ ገምቱ።***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ***ኩንታል*** | ***አሸለበ*** | ***መቀጣት*** | ***የተጋጠ*** |

*ከእለታት አንድ ቀን አንድ መንገደኛ አህያውን አንድ ኩንታል ስንዴ ጭኖ ወደ ገበያ ሊሄድ ተነሳ፡፡ በጉዟቸው ላይም መንገደኛው ስለደከመው አረፍ ልበል በማለት ዛፍ ስር ቁጭ አለ፤ ጥቂትም አሸለበ፡፡ ከቆይታ በኋላ ከእንቅልፍ ሲነቃም አህያውን ከነበረበት ሊያገኘው አልቻለም።*

*1. የመንገደኛው የዕለቱ ተግባር ወደ __________ መሄድ ነበር።*

*ዞር ዞር እያለም መፈለግ ጀመረ። በአጋጣሚም አንድ ልጅ ሲመጣ ተመለከተና፣ "እባክህን አንድ አህያ በዚህ ሲያልፍ አይተሃል?" በማለት ጠየቀው። ልጁም፣ "ግራ አይኑ የማያይ፣ ቀኝ እግሩ የሚያነክስ፣ ስንዴ የተሸከመ ነው?" በማለት መልሶ ጠየቀው። ሰውዬውም አህያው እንደተገኘለት በማመን በጣም ደስ ብሎት፣ "በትክክል፣ እሱ ነው! የት ነው ያየኸው?!" አለው፡፡ ልጁም፣ "አይ ማየትስ አላየሁትም፣" በማለት መለሰለት።*

*2. ልጁ አህያውን ሳያየው እንዴት ሊያውቀው ቻለ?*

*3. የልጁን የመጨረሻ መልስ ሲሰማ ሰውየው ምን ይል ይሆን?*

*በዚህ ጊዜም ሰውዬው በጣም ተናደደ፤ ልጁ እንዲቀጣለትም በአካባቢው ወዳለችው ንግስት ይዞት ሄደ። ንግስቲቱም፣ "አህያውን ሳታየው እንዴት ልትገልፀው ቻልክ?" በማለት ጠየቀችው። ልጁም፣ "አህያው ሲራመድ የረገጠውን መሬት አየሁ የግራውና የቀኙ እግር የተለያየ ነበር፤ በዚህም አህያው እንደሚያነክስ ተረዳሁ። በተጨማሪም በመንገዱ በስተቀኝ ሳሩ የተጋጠ፣ የበስተግራው ደግሞ ያልተነካ ነበር። ከዚህም አህያው የግራ አይኑ እንደማያይ ተገነዘብኩ። በመንገዱ ላይም ስንዴ አልፎ አልፎ ተንጠባጥቦ ይታያል፤ በዚህም አህያው የተጫነው ስንዴ መሆኑን ላውቅ ቻልኩ፣" በማለት አስረዳ።*

*4. እስቲ ግራና ቀኝ እጃችሁን አሳዩኝ። የቱ ነው ግራ የቱ ነው ቀኙ?*

*ንግስቲቷም በልጁ ጉብዝና እየተገረመች ያለቅጣት አሰናበተችው፡፡ ሰውዬውም አህያውን ወደመፈለጉ ተመለሰ።*

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

በዚህ መልመጃ ስር የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እባክዎ መምህር እንደተለመደው ያለፈውን ክፍለጊዜ ትምህርት ከከለሱና የእለቱን ካስተዋወቁ በኋላ ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በትኩረት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ እየተዘዋወሩም ይቃኟቸው፡፡

መምህር ተማሪዎችዎ የተረድኦት ጥያቄዎቹን ሲሰሩ የሚቸገሩበት ሁኔታ ካለ እባክዎ ምንባቡን ትንሽ ፈጠን ባለ ሁኔታ አንድ ጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው (ንቁው ልጅ)፡፡ በመጨረሻም መልሶቻቸውን ጥንድ ጥንድ ሆነው ያነፃፅሩ፡፡ በክፍሉ የጋራ ውይይት ወቅትም እየተሳተፉ ይመልሱ፡፡

ተግባር ሁለትን በተመለከተ ጥቆማ ይስጧቸው፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ የሚቀርውን የቃል ዘገባ ተማሪዎቹ ዝግጅት አድርገው እንዲያቀርቡት ስለጉዳዩ (ባህላዊ መድሃኒት) አስቀድመው መረጃ እንዲያሰብስቡ ይንገሯቸው፡፡

ዝግጅት አድርገው የመጡበትን የቃል ዘገባ መጀመሪያ በአነስተኛ ቡድን ሆነው ይለማመዱ፣ በማስከተል በቡድን ተወካዮቻቸው አማካኝነት ተራ በተራ ያቅርቡ:: እርስዎም የባህላዊ መድሐኒትን ጠቀሜታ ይንገሯቸው፣ ልምድዎትንም ያጋሯቸው:: አጠቃቀሙ ላይ ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባም ይከልሱላቸው::

## ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ተግባር ሦስት

መምህር ባህላዊ እሴቶች እየተጠበቁ እንዲሄዱ ከማድረጊያ መንገዶች አንዱ የየእለቱ ህይወት አካል እያደረጉ መሄድ ነው:: ባህላዊ እሴቶቹ ተቀባይነት እያገኙ እንዲቀጥሉ ከማድረጊያ መንገዶች አንዱም የመደበኛው ትምህርት አካል በማድረግ ተማሪዎቹ ተጋልጠ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው:: በዚህም የኔነት ስሜት እንዲያድርባቸውና የህይወታቸው አካል መሆናቸውን እንዲቀበሉ ያስችላቸዋል::

ስለሆነም በጥቆማ መልክ በመማሪያ መፅሐፋቸው ላይ ከተመለከቱት መርጠው ወይም ከማህበረሰቡ የሚያገኟቸውን ባህላዊ ጉዳዮች በተመለከተ መጠይቅ አካሂደውና መረጃ አደራጅተው በክፍል ውስጥ ለደረጃቸው የሚመጥን የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል::

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ አደራጅተው የመጡትን መረጃ ለክፍል አጋሮቻቸው በቡድን በቡድን እየሆኑ ተራ በተራ እንዲያጋሩ ያበረታቷቸው:: በመጨረሻም የተሻለ ወይም በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ የሆነን ሁለት ወይም ሦስት ባህላዊ ጉዳይን በተመለከተ ለክፍል ፅብረቃ እንዲቀርብ ለየቡድኖቹ እድል ይስጡ፣ አፈጻጸሙንም ይመዝኑ::

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ተግባር አራት

ለተማሪዎችዎ ሌላ አዝናኝ አጋጣሚ!

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች እንቆቅልሽ በመጠየቅና በመመለስ ሂደት በንቃት ተሳትፎ ያደርጋሉ:: እባክዎ መምህር ሚናቸውን በመንገርና አካሄዱን በማሳየት ተማሪዎችዎ በንቃት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው:: ነባርና የራሳቸውን አዳዲስ እንቆቅልሾች እንዲጠቀሙም ያነሳሷቸው:: አንድ ሁለቱንም ምሳሌ በመሆን አብረዋቸው ይስሩ፣ እርስዎም የተዝናንቶቱ ተሳታፊ ይሆኑ!

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አቀላጥፎ ማንበብን በተግባር ይለማማዳሉ፤ የቀረበን ምንባብ አንብበው የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ይከውናሉ

## ተግባር አምስት

### ባህል

*እባክዎ መምህር ይህንን ለተማሪዎቹ አቀላጥፎ ማንበብ ልምምድ እድል የሚፈጥር ምንባብ ተማሪዎችዎ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማንበብ እንዲቋደሱት ያነቃቋቸው:: እንደሁኔታው ሁለቱንም አንቀፅ ወይም ተከፋፍለው አንድ አንድ በመያዝ ያንብቡ:: በማንበብ ወቅትም እንደተለመደው ምዘናዎትን ያቀለጣጥፉ (ትክክለኛነትን፣ ፍጥነትንና አገላለፅን ይመዝኑ)::*

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

### ቹቹና ጓደኛዋ

*ይህ ክፍለጊዜ አንብቦ የመረዳት ተግባር የሚከናወንበት ነው:: ለዚህም ይመጥናቸዋል የተባለ ምንባብ ቀርቧል:: ተማሪዎችዎ በንቃት ምንባቡን ለማንበብ እንዲዘጋጁ ያበረታቷቸው:: ምባቡ በለሆሳስ የሚነበብ መሆኑን ይጠቁሟቸው:: ወደ ምንባቡ ከመግባታቸው በፊትም ርዕሱን አይተው ስለምን ሊያነቡ እንደሆነ እንዲገምቱ ይጠይቋቸው:: እየተነበበም የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች እንደሚሰሩም ያስታውሷቸው:: ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩም አፈፃፀሙን ይቃኙ፤ ምዘናዎትን በምልከታ ይጀምሩ::*

ቹቹና ጓደኛዋ…!

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት

*ሀ. መምህር በዚህ ክፍለጊዜ የቹቹና ጓደኛዋ ምንባብ በድጋሚ ይነሳል በሆኑም ተማሪዎችዎ ታሪኩን ባጭሩ በቃል ለክፍሉ እንዲናገሩ በማድረግ መጀመር ይችላሉ (ሁለት ወይም ሶስት ተማሪ)::*

*በመቀጥል እርስዎ ራስዎ ወይም ተማሪዎቹ መለስ ብለው ታሪኩን አንዴ እንዲያነቡ ማድረግ (እርስዎ ከሆኑ ድምፅዎን ከፍ አድርገው አንብቡላቸው):: ይህንንም መሰረት አድርገው ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ይስሩ:: መመሪያዎቹ ይነበቡ::*

## ክፍለጊዜ፡ አስር

**ለ. የተደመጠን ታሪክ በአጭር በአጭሩ ማስቀመጥ**

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ያነበቡትን ታሪክ በማስታወስ መልሰው ዋና ዋና ክስተቶችን በቅደም ተከተል ያቀርባሉ፤ ለዚህም እርስዎ በአርኣያነት የቀረቡ ምሳሌዎችን በመንተራስ እንዲያስጀምሯቸው ይጠበቃል። ከዚያም ጥንድ ጥንድ እያደረጉ ወይም በአነስተኛ ቡድን እያደራጁ እንዲሰሩ ያድርጉ፤ አፈጻጸማቸውንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ። ለተሳትፏቸውም ዋጋ ይስጡ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፤ መስተዋድዶችን ይጠቀማሉ፤ አንድምታዊ ፍቺ ላይ ይደርሳሉ

## መልመጃ ሦስት

ሀ. መልመጃውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲሰሩ ያድርጉ የማዛመዱን

ለ. በማዛመዱ ተግባር ስር ያሉትን ቃላት ተጠቅመውም የየራሳቸውን አረፍተ ነገሮች ይፃፉ።

በመጨረሻም ደብተሮቻቸውን ሰብስበውና የሰሩትን መሰረት አድርገው እንደተለመደው እርማትና ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## መልመጃ አራት

መስተዋድዶች!

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ መስተዋድድ ከሚባሉ የቃል ክፍሎች ጋር ትውውቅ ያደርጋሉ። ከትውውቁ በፊት ግን መፅሐፋቸው ላይ ያሉትን ሶስት አረፍተነገሮች እንዲያነቧቸውና ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ።

መምህር ተማሪዎችዎ ከዚህ ቀደም ስም፣ ቅፅል፣ ግስና ተውሳከ ግሶች መማራቸውን ያስታውሷቸው። ምሳሌዎችን እንዲሰጡም ይጠይቋቸው። ከዚያ ወደ ገለፃው ይግቡ፤ መፅሐፋቸው ላይ ያለውን ማስታወሻ ያፅፏቸው። ሀረጋቱን እንዲያነቡ ይጋብዟቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

## መልመጃ አምስት

እባክዎ መምህር ስለመስተዋድድ አጭር ክለሳ ያቅርቡላቸው፤ ወደ ኋላ ተመልሰውም ባለፈው ክፍለጊዜ ያነበቧቸውን ሀረጋት እንዲመለከቷቸው ያድርጉ:: የራሳቸውን ተመሳሳይ ሀረጋት እየመሰረቱን ለክፍል ጓደኞቻቸው መንገር ይችሉ ዘንድም በቡድን ያዋቅሯው::

የቡድን ውይይቱ ሲጣናቀቅ መልመጃውን ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲያሚሉ ያድርጉ፤ ትክክለኛነቱንም ደብተራቸውን እንደአጨራረሳቸው ቅደም ተከተል በመሰብሰብ እርማት ይስጡ:: በጋራ ጥያቄዎቹ ይሰሩ::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች ባህላዊ ፅንሰሀሳቦችን አካተው የተመሰረቱ አረፍተነገሮችን ይለያሉ፤ መስተዋድዶችን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፤ የተዛቡ አረፍተነገሮችን አስተካክለው ይፅፋሉ

## መልመጃ ስድስት

መምህር እባክዎን ተማሪዎችዎ አረፍተነገሮቹን ደብተራቸው ላይ እንዲፅፏቸው ይንገሯቸው። በምሳሌው መሰረትም መጀመሪያ በግላቸው ባህል ቀመስ የሚሏቸው ቃላት ስር እንዲያሰምሩ ያበረታቷቸው። በመቀጠል ጥንድ ጥንድ ሆነው የሰሩትን ያነፃፅሩ። በመጨረሻም በቡድን ሆነው ባህል ነክ ያሏቸው ቃላት ላይ ይወያዩ፤ ለምን እደመረጧቸውም ያስረዱ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## መልመጃ ሰባት

መስተዋድዶች!

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ የቀረቡላቸውን መስተዋድዶች በመጠቀም የየራሳቸውን አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ:: በዚህ ትልቅ ተግባር ውጤታማ ይሆኑ ዘንድም እባክዎ አስቀድመው ምሳሌዎች ይስጧቸው::

መልመጃውን በቅድሚያ በግል፣ ቀጥሎ በጥንድ በመጨረሻም በቡድን ሆነው እዲሰሩት ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው:: በትግግዝ መማራቸውን ያበረታቱለላቸው:: እርስዎም እርማት ሊያደርጉባቸው ይችላሉ::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

የባህላዊ ምግብ አሰራሩን በተመለከተ (ጨጨብሳ) ተዘበራርቀው የተሰጡትን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ለይ እንዲፅፉ ያበረቷቸው (የመፃፍ ልምምድ በዚያው ያደርጋሉ)። ከዚያም ቅደምተከተሉን እያነበቡ እንዲያስተካክሉ ይንገሯው፤ በግል የሞከሩትን ይዘው በቡድን እንዲነጋገሩበትና አጠቃለይ አባላቱ የተስማሙበት ለክፍሉ እንዲዘገብ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

መምህር ዛሬ ተማሪዎችዎ ሌላ የራሳቸውን አረፍተነገሮች የሚመሰርቱበት እድል የሚያገኙበት ተግባር ቀርበላቸዋል። ምሳሌ የሚሆኑ አንድ ሁለት አረፍተ ነገሮችን ካሰሯቸው በኋላ፣ ደብተሮቻቸው ላይ የየራሳቸውን አረፍነገሮች እንዲፅፉ ያበረታቷቸው። ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው፤ ደብተሮቻቸው እንደአፈፃፀማቸው ቅደም ተከተል እየተሰበሰበ ይታረም። ቀድመው የጨረሱ ሦስት ተማሪዎችም ከፃፏቸው አረፍተነገሮች መካከል ሦስት ሦስት ያንብቡ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### ተግባር ስድስት

ባለፈው ክፍለጊዜ ስለባህላዊ እሴቶች መረጃ አሰባስበው የቃል ዘገባ ተማሪዎችዎ ማቅረባቸው ይታወሳል። በዛሬው ክፍለጊዜ ደግሞ በአከባቢያቸው የሚዘወተርን አንድ ባህላዊ ምግብ መርጠው እንዴት እንደሚዘጋጅ ቅደም ተከተሉን በፅሑፍ የሚተርኩበት ነው።

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ይህንኑ እንዲተገብሩ ያበረታቷቸው፤ እየተዘዋወሩም ይቃኟቸው። ሲጨርሱም ሀሳብ እንዲለዋወጡ ወደ ቡድን ውይይት እንዲገቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**ተግባር አንድ**

**እንቆቅልሽ በመጠየቅና በመመለስ መሳተፍ**

ገፃውን መሰረት አድርገው እንቆቅልሽ ይጠይቃሉ፤ ይመልሳሉ

**ክፍለጊዜ፣ ሁለት**

**ንቁው ልጅ**

***ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች***

1. ስዕሎቹን ያጠናሉ 2. ይተነብያሉ/ ታሪኩ ስለምን እንደሆነ መገመት

3. **ኩንታል** - መስፈሪያ/መያዣ፤ **አሸለበ** - ጋደም አለ/ተኛ/ እንቅልፍ ወሰደው

**መቀጣት**- መታረም/የጥፋት ዋጋ መቀበል፤ **የተጋጠ** - የተበላ

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ገበያ 2. በማሰላሰል/አእምሮውን በማሰራት/ አመክንዮን በመጠቀም

3. የግምት መልስ (ይናደዳል፣ ይበሳጫል፣ ያኮርፋል…) 4. ግራ እና ቀኝ እጅን ማሳየት

**ክፍለጊዜ፣ ሦስት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

1. መንገደኛው 2. አላየውም 3. አህያው የተገኘለት ስለመሰለው
4. - ማንከሱን የሄደበትን መሬት በማየት(ጎድጎድ ያለውን፤ የተለያየ ስለነበር)
   - አንድ አይኑ እንደማያይ ባንድ በኩል ብቻ ሳሩ ስለተጋጠ
   - ስንዴ እንደተጫነ መሬት ላይ የተንጠባጠበውን በማየት
5. አዎ እንዲሉ ይጠበቃል፤ ምክንያቱም ልጁ ያጠፋው ነገር ስለሌለ
   **እናንተ ብትሆኑ ምንታደርጋላችሁ?** ለሚለው ጥያቄ የየራሳቸውን መልስ ይሰጣሉ
6. የየራሳቸውን መልስ እንደተረዱት ይመልሳሉ

**ክፍለጊዜ፣ አራት**

**ትምህርት ሁለት፣ መናገር**

**ተግባር ሁለት**

ስለባህላዊ ህክምና መረጃ አሰባስበው ያቀረቡት ማንኛውም ዘገባ ተቀባይነት አለው፡፡

**ክፍለጊዜ፣ አምስት**

**ተግባር ሦስት**

ሰለአከባቢያቸው አንድ ባህላዊ ተግበር መረጃ አሰባስበው ዘገባ ያቀርባሉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር አራት**

በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት እየመረጡ ባህሪ፣ መልክ፣ ቅርፅ ወይም ጥቅማቸውን በተመለከተ እንቆቅልሽ ይጠያየቃሉ፤ ማናኛውም ተዘጋጅቶ የሚጠየቅ እንቆቅልሽ ተቀባይነት አለው፤ እስካመራመረ ድረስ! የአጠያየቅ ቅደም ተከተሉ ግን ይተግበር!

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

**ተግባር አምስት**

ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያነበቡ ይተግብሩ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ቱቱና ጓደኛዋ**

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ማንኛውም ከጥያቄው ጋር የተዛመደ መልስ ተቀባይነት አለው
2. ማንኛውም ከጥያቄው ጋር የተዛመደ መልስ ተቀባይነት አለው
3. የሰውን ዕቃ ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ለራስ ማድረግ

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ ሁለት**

1. የሰውን ዕቃ ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ለራስ ማድረግ
2. የሌላን ሰው ንብረት ለመውሰድ መሞከር
3. ምን ይሻለኛል፤ እንዴት አደርጋለሁ፤ ተጨንቂያለሁ፤ ጉዳዩ በጣም አሳስቦኛል ወዘተ
4. ቦርሳውን መልሼ አላገኝም ነበር፤ እናንተ ባታገኙት ኖሮ የሰው ገንዘብ ጥዬ ነበር ወዘተ
5. ወድቆ የተገኘን ነገር ለባለቤቱ መመለስ፤ የራስ ያልሆነን ነገር ለመውሰድ አለመመኘት
6. "እደጉ፣ ያሰባችሁት ይሳካ፤ ክፉ አይንካችሁ፤ የራሳችሁን እንጂ የሰው የማትፈልጉ ሁኑ፣" ብለው
7. አሜን

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ለ. ታሪኩን ባጭር ባጭሩ ከፋፍለው ያቀርባሉ፡ መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ ከዚያ...**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ ሦስት**

**ሀ.** 1. ሐ 2. ረ 3. መ 4. ሀ 5. ለ 6. ሠ

**ለ.** አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ (ማንኛውም ተቀባይነት ያለውና ሰዋስውን የጠበቀ አረፍተ ነገር ምላሽ ይሆናል)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**መልመጃ አራት**

ምሳሌዎቹን ያያሉ፤ ማስታወሻ ይይዛሉ፤ ሀረጋቱን ያነባሉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**መልመጃ አምስት**

1. ወደ 2. ላይ 3. ላይ 4. ውስጥ 5. ውስጥ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ትምህርት አራት፡ መፃፍ**

**መልመጃ ስድስት**

1. በብዙ አካባቢዎች በስራ ላይ **ዘፈን** አለ።
2. ልጃገረዷቱ ፀጉሯን **ሹሩባ** ተሰርታለች።
3. **ጨሌና የሀበሻ ቀሚስ** ተገዛልኝ።
4. **ሲቄ ሀደ ሲቄ** የሚይዙት ቀጭን **ዘንግ** ነው።
5. እኛ **በገዳ ስርዓት** እንተዳደራለን።
6. ቁርሳቸውን **ገንፎ** ወይም **ቅንጬ** ይበላሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ ሰባት**

ማንኛውም ተቀባይነት ያለውና ሰዋስውን የጠበቀ አረፍተ ነገር ምላሽ ይሆናል፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**መልመጃ ስምንት**

መ፣ በ፣ ሐ፣ ሀ፣ ለ፣ ሠ፣ ቀ (በውይይት ወቅት ከዚህ የተሻለ ቅደም ተከተል ሊኖር ይችላል)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**መልመጃ ዘጠኝ**

ማንኛውም ተቀባይነት ያለውና ሰዋስውን የጠበቀ አረፍተ ነገር ምላሽ ይሆናል፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ተግባር ስድስት**

ተገቢ ቅደም ተከተልን ተከትለው ይተርካሉ፡፡

# ምዕራፍ አስር

## ገበያ

### (የክፍል ጊዜ ብዛት 18)

ተማሪዎቹ ይህንን ምዕራፍ በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ መምህራን የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ የማስተማር ብልሃትን በተደጋጋሚ ይጠቀማሉ
- ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው ስለምንባቡ የተሰማቸውን እንዲገልፁ ያበረታታሉ
- ተማሪዎች ምንባብ አንብበው ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲያስረዱ ያነቃቃሉ
- የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማጎልበት የተዘጋጀውን ምንባብ ተማሪዎቹ አቀላጥፈው እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፣ አርዓያ ሁነው ያነባሉ
- በየደረጃው የተዘጋጁ ድህረ ማዳመጥና ድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ ተረድተዋቸው እንዲመልሱ እገዛ ያደርጋሉ
- ተማሪዎቹ ከምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ምሳሌዎችን በማሳየት ያበረታታሉ
- ተማሪዎች በደረጃው ለሚገጥሟቸው አዳዲስ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ
- ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩና ያልተቆጠበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያተጋሉ
- ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር በትብብር እንዲሰሩ ምሪት ይሰጣሉ፤ ያነቃቃሉ
- ተማሪዎች ጥገኛ መስተፃምሮችን ተጠቅመው አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ያበረታታሉ
- የየክፍላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የይዘት ግብዓቶችንና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ያቀርባሉ፤ ቴክኖሎጂያዊ ግብዓቶችን ማስተማርን ለማሳለጥ ይጠቀማሉ

**ማሳሰቢያ፡** ትምህርቱን ተጨባጭና ለተማሪዎቹ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዙ የመርጃና የትምህርት መሳሪያዎችን በአግባቡና በጥራት፣ በተፈላጊው ጊዜና የትምህርት ክፍል ማቅረብ ይገባል፤ ለዚህም አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግን የየእለት ተግባር ማድረግ ይኖርብናል።

ከዚህም ሌላ የየክፍለጊዜው የትምህርት አቀራረብ ያለፈው የሚከለስበት፣ አዲሱ የሚተዋወቅበት፣ ይዘት የሚቀርብበት (አቅርቦት)፣ የሚመዘንበትና የሚጠቃለልበት(የሚከለስበት) አካሄድን የሚከተል መሆን አለበት።

# 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ምንባብን አዳምጠው ስለምንባቡ የተሰማቸውን ይገልፃሉ
- ምንባብ አንብበው ዋና ዋና ነጥቦችን ይገልፃሉ፣
- ምንባብ አንብበው ከምባቡ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ
- ጥገኛ መስተፃምሮችን በመጠቀም አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፣
- ሻጭና ገዢ በመሆን ሚና ይጫወታሉ
- የየራሳቸውን አረፍተነገሮች ይመሰርታሉ
- በትብብር መስራትን ይለማመዳሉ

# 2. የትምህርት ይዘት

## 2.1. ማዳመጥ

- ምንባብን አዳምጠው ምንባቡን በተመለከተ ስሜትን ለመግለፅ ማዳመጥ
- በምልልስ ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ
- ለቃላት አንድምታዊ ፍቺ ለመስጠት ማዳመጥ
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመስጠት ማዳመጥ
- ምልልስ (ገዢና ሻጭ) ላይ ተሳታፊ ለመሆን ማዳመጥ
- ከማዳመጥ በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ከማዳመጥ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ

## 2.2. መናገር

- በምልልስ እየተሳተፉ መናገር (ሻጭና ገዢ)
- ስዕልን በተረዱት መጠን ለመግለፅ መናገር
- ከምንባብ የተረዱትን መነሻ በማድረግ ስሜትን ለማጋራት መናገር
- የሚና ጨዋታ በመጫወት ወቅት መናገር
- ተግባራትን በማከናወን ሂደት በሚደረግ የቡድን ውይይት ወቅት መናገር

### 2.3. ማንበብ

- ገበያን የተመለከተ ምንባብ በማንበብ አቀላጥፎ ማንበብን መለማመድ
- በምንባብ ውስጥ የተገለፀ ሀሳብን በተመለከተ ስሜትን ለማንፀባረው ማንበብ
- ምንባብን አንብቦ ዋናውን ሀሳብ ለመግለፅ ማንበብ
- ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ለመስጠት ማንበብ
- አንድምታዊ ፍቺ ለመስጠት ማንበብ
- ጥገኛ መስተፃምሮችን ለይቶ ለማመልከት ማንበብ

### 2.4. ቃላት

- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት
- ለቃላት አንድምታዊ ፍቺ መስጠት
- ቃላትን በተለያዩ አውዶች መጠቀም
- የቃላት ፍቺን ከአውድ መረዳት

### 2.5. መፃፍ

- ከአረፍተነገሮች ውስጥ መስተፃምሮችን መለየት
- ጥገኛ መስተፃምሮችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ
- ሀረጋትን አዛምዶ አረፍተነገሮችን መመስረት
- ተገቢ አያያዦችን በመጠቀም አረፍተነገሮች መመስረት

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የልስራ፣ እንስራ፣ ስሩ ሞዴል
- አሳታፊ ገለፃ
- ምንባብን ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፣
- ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ማትጋት፣
- ተማሪዎችን ድምጻቸውን ከፍ አስደርጎ ተራ በተራ ማስነበብ (ሞዴል መሆን)፣
- መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፣
- ተማሪዎች ለቃላት አንድምታዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት።

## 4. የክፍል አደረጃጀት

- ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን እንዲሰሩ የሚያስችል መሆን
- የመተባበር መንፈስን የሚያሰርፅ

- ተማሪ መራሽና መምህር ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚፈቅድ

## 5. ምዘና

- ምንባብን አዳምጠው ስለምንባቡ የተሰማቸውን መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ምንባብን አንብበው ዋናውን ነጥብ መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- በየክፍለጊዜዎቹ መደበኛና ኢመደበኛ ክትትል ማድረግ
- አዳምጠው አንድምታዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- በሚና ጨዋታ ወቅት ንቁ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ
- አቀላጥፎ ማንበብንና አንብቦ መረዳትን ተደራሽ በሆነ ሁኔታ መመዘን
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ጥገኛ መስተፃምሮችን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን መመስረት መቻላቸውን መፈተሽ
- በሁሉም ትግበራዎችና ልምምዶች ወቅት ወቅታዊና ተገቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት፣ ውጤታማነታቸውን መከታተል

## ዝርዝር አቀራረብ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ምንባብ አዳምጠው ስለምንባቡ የተሰማቸውን ይገልፃሉ፣ ምልልስን አዳምጠው በተራቸው ይናገራሉ፣ አዳምጠው በውውይይትና ሚና ጨዋታ ይሳተፋሉ::

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ገበያ! አዲስ ርዕስ አዲስ ምዕራፍ! አስደሳች ቀን!

እባክዎ መምህር ወደ ቅድመ ማዳመጥ ተግባሩ ከመሸጋገርዎ በፊት ተማሪዎች የቀረበውን ስዕል እያዩ ምን እንደተገነዘቡ እንዲገልፁ ይጠይቋቸው:: በመቀጠል የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን (ከ1 እና 2) ጥቂት ደቂቃ ወስደው እንዲሰሩ ይጋብዟቸው:: የቀረቡትንም ቃላት ፍቺ እንዲገምቱ ይጠይቋቸው::

**አሁን ምንባቡን ያንብቡላቸው (የተማሪዎቹ ደረጃ ከግምት ይግባ!)** ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ይነበብላቸው:: በአንደኛው የምንባብ ወቅትም (መጀመሪያው) የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች ይሰሩ::

# ገበያ

*ገበያ ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ለመግዛትና ለመሸጥ የሚገናኙበት ስፍራ ነው። በገበያ ለምግብነት የሚያገለግሉ ምርቶች ለምሳሌ የእህል አይነቶች፣ ጥራጥሬዎች፣ ቅመማቅመሞች አትክልትና ፍራፍሬዎች እንዲሁም እንስሳትና ውጤቶቻቸው ወዘተ ይቀርቡበታል። ከዚህም በተጨማሪ የመገልገያ ቁሳቁሶች፣ አልባሳትና ሌሎች ሸቀጣሸቀጦች ለግብይት ተሰናድተው ይመጡበታል።*

*በጥንቱ ጊዜ ሰዎች ግብይት ያካሂዱ የነበረው ለሽያጭ የሚቀርቡትን ነገሮች በመለዋወጥ ነበረ። ከሱ ቀጥሎ ደግሞ የተመረጡ መገበያያዎች በቋሚነት (ለምሳሌ ወርቅ፣ አሞሌ ጨው ወዘተ) ጥቅም ላይ ሲውሉ እንደነበር ይነገራል። በአሁኑ ወቅት ግን ሰዎች ለመገበያያነት ገንዘብን (ብርን) ይጠቀማሉ።*

*በብዙ የአገራችን አካባቢዎች ሻጭና ገዢ ተገናኝተው ግብይት የሚፈፅሙት በውሱን ቀናት ውስጥ ነው፤ በሳምንት አንድ ወይም ሁለት ቀናት። ለመገናኛቸውም ትልቅ ዛፍ ስር፣ ወይም ሰፊ ሜዳን ይመርጣሉ። ከተማ ቀመስ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ በርከት ያሉ የሳምንቱ ቀናት ለመገበያየነት ይውላሉ፤ ከዝናብና ፀሀይ የሚከላከሉ መጠለያዎችም ይቀለሳሉ። ከነዚህ በተጨማሪም መጠናቸው የተለያዩ ሱፐርማርኬቶች በከተሞች የመገበያያ ስፍራ እየሆኑ መጥተዋል። ዘመናዊዎቹን የቴክኖሎጂ መገልገያዎች ተከትሎም አንዳንድ ግብይቶች በድረገፅ መተግበሪያዎች አማካኝነት ሲከናወኑ ይታያል። ለዚህም የእጅ ስልኮች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ይህም ገበያ በቀናትና ቦታዎች ተወስኖ እንዳይቀር እያደረጉት ነው።*

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ (ሀ እና ለ)

በተደመጠው ምንባብ መሰረት ተማሪዎቹ የድህረ ማበብ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያትጓቸው። ጥያቄዎቹን ዕፊው በግላቸው አስቀድመው ይሰሩና በክፍል የጋራ ውይይት የሚቋጯቸው ይሆናል። መምህር እባክዎን ምንባቡን አንዴ ደግመው ያንብቡላቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

## መልመጃ ሁለት

ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ቃላቱን ዕፊው ከፍቺያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያበረታቷቸው፡፡ የሰሩትን ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ሀሳብ ይሰጣጡበት፡፡ በመልሶቹ ላይ ልዩነት ካለ ለክፍሉ ያቅርቡ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

**ሌላ አሳታፊ ተግባር፤ ስዕል አንብቦ መግለፅ!**

መምህር ዛሬ ተማሪዎች የቀረበ ስዕልን እያዩ ስለስዕሎቹ የተረዱትን በተመለከተ ንግግር ያደርጋሉ፡፡ በትገባሩም ሁሉም ተማሪ የማናገር እድሉን ያገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ጊዜውን አመጣጥነው በግል፤ በጥንድ ወይም በቡድን ያሳትፏቸው፡፡

ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን ሲሰጡ ቀጥታ ስዕሉን የተመለከተ ወይም ስዕሉን ተከትሉ የሚመጣን ተግባር (ድርጊት) መሰረት አድርጎ ሊሆን እንደሚችልም ጥቆማ ይስጧቸው፡፡ በመናገር ሂደቱ ወቅትም ምዘናዎን ያከናውኑ (ማን ምን ሰራ፣ ተሳትፎ እንዴት ነበር፤ ምን መሻሻል ያስፈልገዋል፤ ማን ልዩ ድጋፍ ይሻል…?)

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ተግባር ሁለት

መምህር ዛሬ ተማሪዎችዎ በምልልስ ለመሳተፍ የተሻለ እድል የሚያገኙበት ነው! ስለሆነም የቀረበውን ምልልስ ተማሪዎችዎ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያጠኑት በማድረግ ሻጭ ወይም ገዢ በመሆን ክፍል ውስጥ እዲተገብሩት ያበረታቷቸው፤ ሁኔታዎችንም ያመቻቹላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ተግባር ሦስት

መምህር የነገ ተስፋዎቹ ወደፊት ገዥ ወይም ሻጭ ሆነው ህይወታቸውን እንዲገፉ የሚያስችል ጥቆማ የሚሰጥበት ተግባር ቀርቦላቸዋል፡፡ በተግባር ሁለት ስር የተለማመዱትን እንደመነሻ በመጠቀም የሚና ጨዋታም ይጫወታሉ፡፡ ስለሆነም እባክዎ መምህር በዚህ ተግባር በንቃት እንዲሳተፉ ተነሳስያት ይፍጠሩባቸውና ይሳትፏቸው፡፡ ለዚህም ሁለት ሁለት እየሆኑ (በጥንድ) ዝግጅት ያድርጉ፤ አጋር ያጣ ተማሪ ካለ ለሶስት ሆኖ መስራትም ይቻላል፡፡

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### መንገደኞቹና ዛፉ

ተማሪዎች ምንባቡን በጥሞና (በዝምታ) አንብበው ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይሰራሉ:: መምህር ተማሪዎቹ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊትም ስዕሎቹን ሲያዩ ምን እንደተሰማቸው እንዲገልፁ ሊጠይቋቸው ይችላሉ:: በተጨማሪ ምንባቡን ተራበተራ በአንቀጽ ተከፋፍለው እንዲያነቡት በማድረግ አቀላጥፎ ማንበባቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግም ይቻላል::

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

የእውነት ሐሰት ጥያቄዎቹን በጋራ ያስሯቸው:: ደብተሮቻቸውን ሰብስበው እርማት ይስጧቸው፤ ጥያቄዎቹን በጋራ ተነጋገሩባቸው:: አስፈላጊ ከሆነ ምንባቡን ደግመው እንዲያነቡም መጋበዝ ይቻላል::

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

መምህር እነዚህን ጥያቄዎች (ለ. ከ1-5) ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ ፅፈው መልሱን በመምረጥ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም ከሌላ ተማሪ ጋር ተጣምረው መልሶቻቸውን እንዲያስተያዩ ያድርጉ። በመጨረሻም መልሶቹን ጥያቄዎቹን እያነበባችሁ (ተማሪዎች ያንብቡ) በጋራ ስሯቸው።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ አምስት

ሀ. ምንባቡን ወደ ኋላ ተመልሰው እያነበቡት ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያነቃቋቸው:: ደብተራቸው ላይ መልሱን ሰርተው ሲጨርሱም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ እንዲያነፃፅሩ፤ በመጨረሻም ቡድን በቡድን ሆነው እንዲወያዩባቸው፤ ከቻሉም አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱባቸው ያትጓቸው::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

ለ. በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ቃላትን ከተቃራኒዎቻቸው የሚያዛምዱበት መልመጃ ቀርቧል።

ተማሪዎችዎ ደብተራቸው ላይ ፅፈው እንዲሰሯቸው ያበረታቷቸው። ሰርተው ሲጨርሱም መልሶቻቸውን ከጓደኛ ጋር ያነፃፅሩ። ከዚህ ቀጥሎም በ 'ሀ' እና 'ለ' ስር የተዘረዘሩትን

ቃላት እየተጠቀሙ አጫጭር አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ይጠይቋቸው። በመጠረሻም ደብተሮቻቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው፤ ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ሐ. በዚህ መልመጃ ስር ሌላ የቃላት ትምህርት ቀርቧል። ስለሆነም በትዕዛዙ እንደተመለከተው ወደኋላ በበመለስ ምንባቡን መሰረት በማድረግ አውዱ ውስጥ ለነበራቸው ፍቺ ተመሳሳይ የሚሆነውን እየመረጡ እንዲያዛምዱ ያበረታቷቸው። አፈፃፀሙንም እየተዘዋወሩ ይቃኙ። ተማሪዎችዎ ሰርተው ሲጨርሱም መጀመሪያ በጥንድ፣ ቀጥሎም በቡድን ሆነው በመልሶቹ ላይ እንዲነጋገሩባቸው ያድርጉ ወይም እርስዎ ደብተራቸውን ሰብስበው በማረምና እንደክፍል በመልሶቹ ላይ በመወያየት ስሯቸው።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

መ. መምህር በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ከግብይት ጋር የተያያዙ ፅንሰሀሳቦችን እንዲያነሱና እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል እድል ይፈጠራል። በመሆኑም ይህንን ከግምት እያስገቡ ጥያቄዎቹን ፅፈው እንዲመልሷቸው ይንገሯቸው (ሌላ የመፃፍ አጋጣሚ!)

በመጨረሻም ደብተራቸው ይሰብሰብና እርማት ይደረግበት፤ ምጋቤ ምላሽም ይሰጥበት።

### ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ስድስት

መምህር በዚህ መልመጃ ስር የቀረቡት አረፍተነገሮች በቅርቡ ስለሚማሩት ፅንሰ ሀሳብ ጥቆማ የሚሰጡ ናቸው። ስለሆነም ሁሉም ተማሪዎች አረፍተነገሮቹ ውስጥ ጠቆር ብለው የተፃፉት ክፍሎች ላይ ትኩረት እያደረጉ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።

### መልመጃ ሰባት

በዚህኛው መልመጃ ስር ደግሞ ተማሪዎቹ ከላይ የቀረቡትን የሚመስሉ የየራሳቸውን አረፍተነገሮች እንዲፅፉና እንዲያነቡ እድል ይሰጣቸዋል። በትዕዛዙ መሰረት ይሰሩ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

### መልመጃ ስምንት

መምህር ተማሪዎችዎ በአንድ አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ሀሳቦችን በማገናኘት መልሰው እንዲፅፉ የሚፈቅድ መልመጃ ቀርቦላቸዋል። ስሆነም በመጀመሪያ በ 'ሀ' ስር ያለውን ክፍል እንዲፅፉና ቀጥሎ ደግሞ እርግጠኛ ሲሆኑ ብቻ ቀጣዩን የአረፍተ ነገር ክፍል ቀድሞ ከፃፏቸው ቀጥለው እንዲያኖሩ ይግለፁላቸው፤ ለዚህም አስቀድመው ደብተራቸው ላይ ቦታ እየተው እንዲሄዱ ይንገሯቸው። ከዚያ መልሶቹ ልክ ስለመሆናቸው በቡድን ቀጥሎም በጋራ ይረጋገጥ፤ በአማራጭነትም ደብተራቸውን ተቀያይረው ሊተራረሙ ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ዘጠኝ

ሀ. በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎቹ የተሰጡ አያያዦችን እየተጠቀሙ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያስችል እድል ተመቻችቷል:: በዚህም የመፃፍ ክሂላቸውን ያሳልጡበታል:: ስለሆነም መምህር እርስዎ መጀመሪያ ምሳሌ በመስጠት ሰርተው ያሳዩአቸው ቀጥለውም እነሱ ራሳቸውን ችለው ይስሩ::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

ለ. ይህ መልመጃ በትእዛዙ መሰረት ይሰራ:: መጀመሪያ በግል፣ ቀጥሎ በጥንድ በመጨረሻም በቡድን ሀሳብ ይንሸራሸርበት:: የመልመጃዎቹ መደጋገም ተማሪዎቹ በጉዳዩ ላይ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲይዙ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ይታወቅ::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### ተግባር አራት

መምህር ይህ ተግባር የመጨረሻው ምዕራፍ የመጨረሻው ክፍለጊዜ ተግባር ነው:: ተማሪወችዎን እስካሁን በብዙ ነገሮች እያገዟቸው ስለመጡም ደስ የሚሰኙበት እለት ነው!

በዚህ የመሰነባበቻ ተግባር ተማሪዎችዎ እራሳቸውን ችለው የየራሳቸውን አረፍተነገሮች ይፅፋሉ:: ለዚህም የተለያዩ አያያዦችን ይጠቀማሉ:: ፅፈው ሲጨርሱ የሰሩትን ተለዋውጠው እንዲናበቡና በፍላጎትም ለክፍሉ አረፍተነገሮቻቸውን በንባብ እንዲያጋሩ ይጠይቋቸው፤ የተወሰኑትን አንዳንድ አረፍተ ነገር ሰሌዳ ላይ እንዲፅፉ ሊጋብዟው ይችላሉ::

# የመልመጃዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

**ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ**

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

ከተራ ቁጥር 1 - 2 ያሉትን ጥያቄዎች የአካባቢያቸውን ልምድ መሰረት አድርገው ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ማንኛውም ከጥያቄዎቹ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ምላሽ ተቀባይነት አላቸው፡፡

**ገበያ፡** የመሸጫና መግዢያ ስፍራ/ግብይት ማከናወኛ **ቴክኖሎጂ -** የፈጠራ ውጤት

**ግብይት -** የመግዛትና የመሸጥ ክንውን **ድረገፅ -** የኢንተርኔት ገፅ

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

ሀ. 1. **ሐ** 2. **መ** 3. **ሀ**

ለ. 1. **ሠ** 2. **መ** 3. **ለ** 4. **ሐ** 5. **ሀ**

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**መልመጃ ሁለት**

1. **ሠ** 2. **መ** 3. **ሀ** 4. **ለ** 5. **ሐ**

**መልመጃ ሦስት**

መ. ከ1-3 ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ምላሾች ከቀረበው ይዘት እስካላፈነገጡ ድረስ ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ትምህርት ሁለት፡ መናገር**

**ተግባር አንድ**

ስዕሎቹን እያዩ ማናቸውንም ተያያዥ ሀሳቦች ይሰጣሉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር ሁለት**

ምልልሱን አጥንተው ያቀርባሉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ተግባር ሦስት**

ገዢ እና ሻጭ በመሆን ሚና ይጫወታሉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ**

በለሆሳስ ወይም ድምፅ እያሰሙ ያነባሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**መልመጃ አራት**

**ሀ. 1. ሐሰት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. ሐሰት**

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

**ለ. 1. ለ 2. ሐ 3. ለ 4. ሀ 5. መ**

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ትምህርት አራት፡ ቃላት**

**መልመጃ አምስት**

ሀ. **ማስቀየም** - ማሳዘን/ማስኮረፍ/ማስከፋት፤

**በጥሞና** - በትዕግስት/በእርጋታ፤

**የማይረባ** - የማይጠቅም/ ዋጋ የሌለው፤

**የተከላከለልን** - የሸፈነልን/የከለለን/ ጥላ የሆነን፤

**በፀሐዩ ንዳድ** - በሀሩሩ/ በቃጠሎው/ በከፍተኛ ሙቀት

**አይገባም** - አይደረግም፣ አይሆንም

**ደረሰልን** - አገዘን/ጋሻ ሆነን

**ተቀበለ** - ወሰደ/ እሺ አለ

**አረፍ እንበል** - ትንሽ እንቀመጥ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

ለ. 1. **መ** 2. **ሠ** 3. **ለ** 4. **ሀ** 5. **ሐ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

ሐ. 1. **መ** 2. **ረ** 3. **ሰ** 4. **ለ** 5. **ሀ** 6. **ሐ** 7. **ሠ** 8. **ሸ** 9. **በ** 10. **ቀ**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

መ. 1. ክፍያ፣ መልስ/ምላሽ 2. ሻጭ 3. ጣልኩ 4. ትርፍ 5. ኪሳራ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ትምህርት አምስት፡ መፃፍ**

**መልመጃ ስድስት**

አያያዥ መስተፃምር መሆናቸውን እንዲለዩ የቀረበ (ከ1-5)

**መልመጃ ሰባት**

የየራሳቸውን አምስት አምስት አረፍተነገሮች ይፅፋሉ።

ከላይ ያሉትን የሚመስሉ (መልመጃ 6)

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ ስምንት**

1. ረ 2. ሀ 3. ሰ 4. ሠ 5. መ 6. ለ 7. ሐ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**መልመጃ ዘጠኝ**

ሀ. የተሰጡትን አያያዦችን የተጠቀሙና ሰዋስዋዊነታቸውን የጠበቁ ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተ ነገሮች ምላሽ ይሆናሉ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት (ለ.)**

1. ሳልማር ብቀር **ኖሮ** ይቆጨኝ ነበር።
2. **ምንም እንኳ** ገበያ ቢሄድም የሸመተው ነገር የለም።
3. ወንድሟ **ብቻም ሳይሆን** እህቷ**ም** ታታሪ ናት።
4. ደጋግማ ብትነግረኝ**ም እንኳ** ልሰማት አልቻልኩም ነበር።
5. ዛሬ **ስላ**ረፈድኩኝ መምህሬ የሚያዝኑብኝ ይመስለኛል።
6. የኮሮና ወረርሺኝ **ባይከሰት ኖሮ** ትምህርታችን አይቋረጥም ነበር።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ተግባር አራት**

ሰዋስዋዊነታቸውን የጠበቁ ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተ ነገሮች ምላሽ ይሆናሉ፡፡

**መልካም የእረፍት ጊዜ!**

# አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ 3ኛ ክፍል

# መርሀ ትምህርት

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በትምህርት አሰጣጥ ፈጣንና መሻሻል በታየበት ሁኔታ እየሰራች ነው፡፡ ልዩ ትኩረት የተሰጠው "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" ላይ ነው፡፡ ይኸውም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን እድገት እንደመሳሪያ ሆኖ በብቃት ህብረተሰቡን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ትምህርት ሚንስቴር የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምሮችን በማድረግ አዲስ ስርዓት ትምህርትን ቀርጿል፡፡ በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎቹ (የይዘት ፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀትምህርት) በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስርኣተ ትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣ በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳድጉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የስርዓተ ትምህርት መሳሪዎች በዋናነት እንዲቀረፁ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው፡፡

መርሃ ትምህርቱ የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶችን፣ ዋና ዋና ክሂሎችን፣ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትንና ብርቱ ብሄራዊ ጉዳዮችንና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም በብሄራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ታስቦ የተሰናዳ ነው፡፡ የይዘቱ ፍሰትም ከቀላል ወደ ውስብስብ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ ሆኖ ተማሪዎቹ አውዳዊ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያስችል ነው፡፡ መልመጃዎቹ ተማሪ ተኮር የሆኑ፣ አብዛኛውን እድል ለተማሪዎች የሚሰጡ፣ የታሰበውን የቋንቋ ክሂል ተለማምደው እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ሆነው በደረጃቸው የቀረቡ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በክልሉ ለሚገኙ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች ይህን በትምህርት ሚኒስቴር የቀረበ ስርዓተ ትምህርት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አስማምቶ አቅርቦታል፡፡

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ግቦችና አላማዎች**

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ግቦች ፡-**

- ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በስኬታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ቀጥለው ያሉትን ግቦችና አላማዎች እንዲያሳኩ ይጠበቃል፡፡

**ግቦች**

- የመሰረታዊ ፊደላትን ክሂል ማበልጸግ የተማሪውን አእምሮታዊ፣ስሜታዊና ማህበራዊ ክሂሎችን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤
- ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ስነልሳናዊ እውቀት ማስተዋወቅ ለተግባቦት ብቃት ማዳበር ስለሚያግዛቸው ሀሳባቸውንና ስሜታችውን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎቹን አገር በቀል እውቀትና እሴቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል፡፡

**አላማዎች**

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና የመማር አበይት አላማዎች፡-**

- መሰረታዊ ትምህርትን በማዳበር ተማሪዎች ለወደፊት የትምህርት ግባቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ጽናት ይሰጣቸዋል፤
- የቋንቋውን ዋና ዋና ክሂሎች መረዳት የተግባቦት ችሎታቸውን ለማሳደግ እና ሀሳባችውንና ስሜታቸውን ውጤት ባለው መንገድ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- የቋንቋውን ንዑሳን ክሂሎች ማወቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፤
- ከሳይንሳዊ ምርምር የተገኙትን የቋንቋና የስነልሳን ባህሪያት እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፤
- የቋንቋ አጠቃቀምን በትምህርት፣ በማህበራዊ ኑሮና በምጣኔ ሀብት ሁነቶች ውስጥ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤
- የአገር በቀል ቋንቋ ስልቶችን በተለያዩ የቋንቋ ይዘቶች በማቅረብ እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡

**ራዕይና እሴቶች**

**ራዕይ**

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአለም ቋንቋዎች ሁሉ ዋጋ ይሰጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ እያንዳንዱ ሰው በተለይም ህጻናት ቋንቋውን መናገር ብቻ ሳይሆን መማር በመቻል ያንን ቋንቋ በቀላሉ ይረዳሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠንካራ መሰረቶች የሚኖሩ ከሆነ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ስርዓተ ትምህርቱን እየተረዱ እንደዚሁም አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከህጻንነታቸው ጀምሮ ጠበቅ አድርገው ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ በየክፍል ደረጃው የተሻለ ጥረት በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የህጻናት አእምሮ ብስለትን በማሳደግ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ይረዳቸዋል፡፡ ይህን እሳቤ ውስጥ በማስገባት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተምረው ያለፉ ኢትየጵያዊ ተማሪዎች በሰላምና በመተሳሰብ አብሮ በመኖር ፡-

- ብቃት ያለው የቋንቋ ክሂል ባለቤት፣ ባህልንና ማንነትን አክባሪ፣የማሰብና የመፍጠር ባለቤት፣ በራስ የሚተማመኑ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ትጉኃን፣ ትኩረት ሰጪዎች፣ ምክንያታዊያን ተባባሪና ራስን በመስጠት የሚሰሩ ይሆናሉ፤

**እሴቶች**

እሴቶች አስፈላጊና ፍትሃዊ ስለሆኑ ነገሮች ያሉን እምነቶች ናቸው፡፡ እሴቶች ድርጊታችንንና ውሳኔያችንን ይመራሉ፤ ስለዚህ ይህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው ጽሁፍ ተማሪዎቹ፡-

አገር በቀል እወቀቶችን አክባሪና ተጠቃሚ፣ የህብረተሰቡን የግጭት አፈታት ባህሎችን የሚተገብሩ፣ የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የመረዳዳት መንፈስ ያላቸው፣ የመቻቻል ባህል የተላበሱ፣ ብሄራዊና አለማቀፋዊ ቅርስ የሚንከባከቡ፣ በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚቀበሉ፣ እርስ በእርስ የሚከባበሩ፣ ጠንክሮ የመስራት ባህል ያላቸው፣ በላቀ ሁኔታ የሚያስቡ፣ የፈጠራ ችሎታን የተላበሱ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያስቡ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

# አንደኛ ወሰነ ትምህርት

**ምዕራፍ አንድ፡- ጤና (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን የምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ከሚያዳምጡት ምንባብ ዋና ዋና ነጥቦችን ይዘግባሉ
- በትክክል ያነባሉ
- ከምንባቡ ለወጡት ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፤
- አያያዞችን በአረፍተ ነገር ውስጥ ለይተው ያስገባሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| **ተማሪዎቹከትምህርቱ በኃላ፡-**<br>አዳምጠው ይዘግባሉ<br>የቀረበውን ምንባብ በትክክል ያነባሉ<br>ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ | **ማዳመጥ**<br>ለክፍለ ጊዜው የተዘጋጀውን ምንባብ አዳምጠው መዘገብ<br>***ማንበብ***<br>ዋና ነጥቦችን ለማግኘት ማንበብ<br>**ቃላት**<br>ለቃላት ፍቺ መስጠት<br>**መጻፍ**<br>አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ምንባብን መርጦ ለተማሪዎች ማንበብ ወይም መተረክ፡፡<br>ለምሳሌ የምግብን ለጤና አስፈላጊነት መውሰድ ይቻላል፡፡ከዚያም ተማሪዎቹ አዳምጠው በቃል እንዲገልጹት ይጠበቃል<br>ተማሪዎቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተራ በተራ ማንበብ፣ ከዛም ለጓደኞቻቸው እንዲያሰሙ ሆኖ መምህር እየተዘዋወሩ ማንበባቸውን መከታተል፡፡<br>ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ | ተማሪዎቹ በሚናገሩበት ጊዜ ተከታትሎ ግብረ መልስ መስጠት፡፡ ካዳመጡ በትክክል መናገር ይችላሉ፡፡<br>ሲሳሳቱ ማስተካከል፡<br>ተማሪዎች የጻፏችወን የቃላት ፍቺ መረጋገጥ፤<br>ተማሪዎቹ የጻፏችወን ቃላት ማረጋገጥ<br>በሚጽፉበት ጊዜ ክትትል ማድረግ፤<br>ተማሪዎቹ የጻፏችውን አረፍተ ነገሮች ማስተካከልና ግብረ መልስ መስጠት፡፡ |

**ምዕራፍ ሁለት፡ጎረቤታሞች (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ምንባብን አዳምጦ ደግሞ መናገር
- አጫጭር አንቀጾችን ድምጽ እያሰሙ በትክክል ማንበብ
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ፡<br>• ቀለል ቀለል ያሉ ትረካዎችን አዳምጠው ለክፍል ጓደኞቻቸው ደግመው ይናገራሉ፡፡<br>• ከምንባቡ የወጡ አንቀጾችን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለመምህራቸውና ለጓደኞቻቸው ይተርካሉ<br>• ሥርዓተ ነጥብንተጠቅመው ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡<br>• የቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ | **ማዳመጥና መናገር**<br>አንድን ታሪክ አዳምጦ መናገር<br>**ማንበብ**<br>ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>አረፍተነገሮችን በተገቢ ውርቀት መጻፍ<br>**ቃላት**<br>የአገባብ ፍቺ | ቀለል ያሉ ታሪኮችን አዘጋጅቶ ተማሪዎቹ አዳምጠው ደግሞ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>ምሳሌ መምህር የሚያውቁትን ቀለል ያለ ታሪክ መንገርና ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ (ደጋግሞ እንዲተርኩ ማድረግ)<br>ከአዳመጡት ታሪክ ባለ ታሪኮችን እንዲያወጡ መጠየቅ፡፡<br>አጭር ታሪኮችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከፍ አድረገው እንዲያነቡ ማድረግ ፡፡<br>ካነበቡት ታሪክ ዋና ዋና ባለታሪኮችን እንዲጽፉ ማድረግ፡፡<br>ከምንባቡ ስሞችን እንዲለዩ ማድረግ፡፡ | ታሪኩን በሚነግሯቸው ሰዓት ተማሪዎች በትክክል ማዳመጣቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>ከዚያም የተወሰኑትን ተማሪዎች ታሪኩን እንዲተርኩ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>ምንባቡን ወደነሱ አውድ በመቀየር ተማሪዎች እንዲሳተፉበት በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>ለተማሪዎቹ መልስ ግብረ መልስ መስጠት፡፡<br>ቃላትን አሳስተው ሲጠሩ እርማት ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎች በድብተራቸው ላይ ስርዓት ነጥብ በትክክል መጠቀማቸወን ማረጋገጥ፡፡<br><br>ለቃላት የሰጧቸውን ፍቺዎች ማረም፡፡ |

**ምዕራፍ ሶስት፡ ስነቃል (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ስነቀልን አዳምጠው ደግመው ይተርካሉ፤
- ዋና ዋና ባለታሪኮችን ከስነቃል ውስጥ አውጥተው ይናገራሉ
- ድምጽ አሰማተው አጫጭር ስነቃሎችን አስተካክለው ያነባሉ
- የታሪኩን ዋና ሀሳብ ይጽፋሉ
- ከምንባቡ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ፍቺ በግምት ይናገራሉ፡
- ስሞችን ከምንባብ ውስጥ ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ፡<br>መምህራቸው ታሪኮች ሲተርኩላቸው አዳምጠው መልሰው ይተርካሉ፡፡<br>የታሪኩን ዋና ባለታሪክ ለይተው በቃላቸው ይናገራሉ፡፡<br>የታሪኩን ዋና ሀሳብ ይጽፋሉ፤<br>አጫጭር ታሪኮችን ድምጽ ከፍ አርገው ያሰማሉ፤<br>ስሞችን ከምንባብ ይለያሉ፤ | **ማዳመጥ**<br>ትረካዎችን ማዳመጥ<br>**መናገር**<br>የሚያውቁትን ታሪክ መናገር<br>**ማንበብ**<br>ድምጽ አሰምቶ ከፍ አድርጎ ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>በቀረበ ታሪክ ውስጥ ያሉትን ባለታሪኮች መጻፍ<br>**ስዋሰው**<br>ስሞችን መለየት | አጭር ትረካዎችን ለተማሪዎቹ ነግሮ ደግሞ እንዲተርኩት ማድረግ<br><br>ካዳመጡት ታሪክ ባለታሪኮችን እንዲናገሩ መጠየቅ<br><br>የሚነበብ አጭር ታሪክ አዘጋጅቶ ድምጽ አሰምተው እንዲያነቡ ማድረግ<br>ካነበቡት ታሪክ ውስጥ ዋና ዋና ባለታሪኮችን እንዲጽፉ ማድረግ<br>ስሞችን ከምንባብ ውስጥ እንዲለዩ ማስቻል፡፡ | አጭር ታሪክ አዘጋጅቶ ለተማሪዎቹ መተረክ ከእዛም በራስ ተማምነው እንዲተርኩ ማድረግ፡፡<br>ከታሪኩ ውስጥ ባለታሪኮችን አውጥተው በሰጡት መልስ ላይ ግብረ መልስ መስጠት<br>ድምጽ አሰምቶ እንዲያነቡ ማበረታታትና ግብረ መልስ መሥጠት<br>ካነበቡት ታሪክ ዋና ዋና ባለታሪኮችን ለይተው የጻፉትን መከታተል |

**ምዕራፍ አራት፡የጊዜ አጠቃቀም (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የሰዓት አጠያየቅንና አመላለስን አዳምጠው ይወያያሉ፤
- የምንባብን መልዕክት አንብበው ደረጃ ይሰጣሉ፤
- የሚነበብላቸውን አረፍተ ነገር አዳምጠው ይጽፋሉ፤
- የተውሶ ቃላትን ይለያሉ
- ግሶችን ይለያሉ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ፡ አዳምጠው መልስ መስጠት በተለያዩ ጊዜ የሰሩትን ስራዎች መናገር ጽሁፍን አንብቦ ለመልዕክቱ ደረጃ መስጠት አዳምጦ መጻፍ የተውሶ ቃላትን መለየት በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች መለየት | **ማዳመጥ** ስለጊዜ አጠቃቀም አዳምጦ( የትምህርት ሰዓት፣ የእረፍት ሰዓት፣ የጥናት ሰዓት)ለክፍል ተማሪዎች መናገር **መናገር** ልምድ መለዋወጥ **መጻፍ** አዳምጦ መጻፍ **ማንበብ** በጭውውት መልክ ማንበብ **ስዋሰው** ግሶችን ከአረፍተ ነገር ውስጥ ሌቶ መጻፍ | ስለጊዜ አጠቃቀም ሲነገራቸው ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ማድረግ ምሳሌ( የትምህርት ቤትና የቤት ውስጥ የጊዜ አጠቀቀማችወን መንገር ትችላል፡፡ ሰዓታቸውን በቤትና በትምህርትቤት ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀሙ (የትምህርት ቤት ሰዓት፣ጠዋት- የትምህርት ቤት ሰዓት፣ምሳ-ቀትር፣ የመኝታ ሰዓት-ማታ)መንገር ተማሪዎች በጥንድ በማደራጀት ሰዓት እየተጠያየቁ እንዲጨዋወቱ ማድረግ ስንት ሰዓት ነው? 5፡20 ( አንዱ ሲጠይቅ አንዱ ይመልሳል) የተወሰኑ አረፍተ ነገሮችን በቃል በመንገር ተማሪዎችን ማጻፍ ተማሪዎች የተውሶ ቃላትን ( እንደ ሬድዮ፣ቴሌቪዥን፣ሞባይል) እንዲለዩ ማስቻል፡፡ ተማሪዎቹ ግስን እንዲለዩና በአረፍተ ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙ መርዳት | በማዳመጥና በመናገር ላይ ያላቸውን ተሳትፎ መከታተል በሀሳብ አደረጃጀት ላይ የፈጠሯችወን ጉልህ ስተቶች እንዲያርሙ መምራት ሲያነቡ መከታተልና በጭውውት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ግብረ መልስ መስጠትና መምራት በደብተራቸው ላይ የጻፏችወን ማረም የተወሰኑ የተውሶ ስሞችን ነግሮ ቀሪዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፤ አዳምጠው በደብተሮቻቸው ላይ የጻፏችውን ማርም |

**ምዕራፍ አምስት፡- መጓጓዣ (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ምንባብን አዳምጠው ዘገባ ያቀርባሉ፤
- ምንባብን አንብቦ ከነባረዊ ሁኔታዎች ጋር ያመሳክራሉ፤
- የተዘበራረቁ አረፍተ ነገሮችን አስተካክለው ይጽፋሉ፤
- ቅጽሎችን ይለያሉ
- ተማሳሳይ ፍቺ ያላችውን ቃላት ይለያሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ፡<br>• በተሰጡት ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ዘገባ ያቀርባሉ፤<br>• አጭር ምንባብ አንብበው የመጓጓዣ አይነታችወን ይለያሉ<br>• ምንባቡን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አገናኝተው ይጽፋሉ፤<br>• ቁልፍ ቃለትን እንደ አገባባችው ፍቺ ይሰጣሉ፤<br>• ቅጽሎችን ከምንባቡ ለይተው ያወጣሉ፡፡ | **ማዳመጥና መናገር**<br>አዳምጦ መዘገብ<br>**ማንበብና መጻፍ**<br>የተሰጠውን ምንባብ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ መጻፍ<br>**ቃላት**<br>ተመሳሳይ ፍቺ ያላችወን ቃላት መስጠት<br>**ስዋሰው**<br>ቅጽሎችን ለይቶ በአረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም | ምንባብን አዘጋጅቶ ለተማሪዎች ማንበብና መጀመሪያ በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ፤ከዚያም ጉዳዩን እንዲዘግቡ ማበረታታት<br><br>አጭር ምንባብ እንዲያነቡ ና የማጓጓዣ አይነቶችን ማጻፍ ለምሳሌ(በአካባቢያቸው ያሉትን የመጓጓዣ አይነቶችን ሊጽፉ ይችላሉ)<br>ቃላትን ከምንባብ መርጦ ተማሪዎች ፍቺያቸውን እንዲሰጡ ማድረግ<br><br>ለተማሪዎች አረፍተ ነገሮችን ሰጥቶ ቅጽሎችን ማስለየት፡፡<br>ለምሳሌ <u>ቀይ</u> ብዕር አለኝ፡፡) | በሚያዳምጡበት ጊዜ ክትትል ማድረግ፤<br>እንዲናገሩ ማበረታታትና በልምምዱ ጊዜ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>ምንባቡን እንዲያነቡ ማድረግና የምንባቡን ሀሳብ የሚመለከቱ ጥያቄዎች መስጠት፤<br>ከምንባቡ የተወሰኑ ቃላትን ፍቺ ጠይቆ የሰጡትን ፍቺ ማረም፤<br>በቅጽል ላይ የሰሩትን መልመጃ ዎች ማረም፤ |

# ሁለተኛ ወሰነ ትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት፡- ስነ ምግባር (18 ክፍለ ጊዜያት)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ምንባብን አዳምጠ አስፈላጊ ነጥቦችን መልሰው ይናገራሉ፤
- ምናባቡን አንብበው ጥሩና መጥፎ ስነምግባሮችን ይለያሉ፤
- ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ በመጠቀም አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ
- የቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ፡<br>• የቀረበላቸውን ታሪክ አዳምጥው ጥሩና መጥፎ ስነምግባርን ደግመው መናገር<br>• ለመረጃ አጭር ጽሁፍን ማንበብ<br>• ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቆ አረፍተነገሮችን መጻፍ<br>• ቃላትን ከተቃራኒ ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዶ መጻፍ፤፤ ይህውም ጥሩና መጥፎ ስነምግባርን የሚያመለክቱትን ቃላት መጻፍ | **ማዳመጥና መናገር**<br>ታሪክን አዳምጦ መልሶ መናገር<br>**ማንበብ**<br>ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቆ መጻፍ<br>**ቃላት**<br>ቃላትን ማዛመድ | ስለ ጥሩ ስነምግባር ምን እንደተረዱ ተማሪዎችን መጠየቅ<br>**ተግባር** ምሳሌ፡ አጭር ቪዲዮ በማሳየት ወይም መልካም ስነምግባርና መጥፎ ስነምግባር የሚያሳዩ ባለታሪኮች ያሉበትን ታሪክ ማንበብ<br>ጥሩና መጥፎ ስነምግባር ያላቸውን ለይተው ጥሩ ወይም መጥፎ ብለው እንደናገሩ ማድረግ፡፡<br>ጥሩ ስነምግባር ለህዝብ ጠቃሚ እንደሆነና መጥፎ ስነምግባር ህዝቡን እንደሚጎዳ ለይቶ ማሳወቅ፤<br>ከህይወት ልምዳቸው የቱ ጠቃሚ እንደሆነና የቱ ጎጂ እንደሆነ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲነጋገሩ መጠየቅ፤<br>የተማሪዎችን መልስ ዋና ዋናዎችን ሀሳቦች በሰሌዳ ላይ መጻፍ፤ጥሩና መጥፎ ስነምግባር የሚያሳዩ ስዕሎችን በቡድን ሆነው እንዲለጥፉ ማድረግ፤<br>ስዕሎቹን መጥፎና ሊወገዱ የሚገቡትን እንዲለዩ ማድረግ ፤<br>ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በምሳሌ መልክ መስጠትና የተቀሩትን እንዲጽፉ ማድረግ፤<br>ተማሪዎቹ በተሰጣችወ ምሳሌ መሰረት በምንባቡ ላይ ተመስርተው ቁልፍ የሆኑትን ቃላት እንዲጽፉ ማስቻል፤፤<br>ተማሪዎቹ ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቀው አረፍተነገሮችን እንዲጽፉ ማድረግ | ካዳመጡት ነገር ቀለል ያለ ጥያቄ መጠየቅ፤<br>የተማሪዎችን ተሳትፎ መከታተል፤<br>ጭውውት በሚያደርጉበት ሰዓት ግብረ መልስ መሥጠት<br>በቃል ንባብ ጊዜ ክትትል እያደረጉ ስህተት ካለ ማረም፤<br>ተማሪዎች ከተሰጠው ምንባብ ቁልፍ ቃላትን አውጥተው መጻፋቸወን መጠየቅ፤<br>ያዛመዷችውን ሀሳብ ማረም<br>የመሰረቷችወን አረፍተ ነገሮች አይቶ ግብረ መልስ መስጠት፡፡ |

**ምዕራፍ ሰባት፡-ግብርና (18 ክፍለ ጊዜያት)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የቀረበላችወን ምንባብ አድምጥው የሚናጨዋ ይጫወታሉ፤
- አጩር አንቀጽን አንብበው ዋናውን ሀሳብ ይጽፋሉ፤
- በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ጉዳዮች ይጽፋሉ፤
- ተውሳከግሶችን ለይተው ይጠቀማሉ

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• የግብርና መዝሙሮችን አድምጠው የሚና ጨዋታ ይጫወታሉ፤<br>• ከመዝሙሩ ያዳመጧችወን ቁልፍ ቃላትን ይጽፋሉ<br>• በመጻፋቸው ላይ ያለውን አጭር አንቀጽ ያነባሉ(ስለ ግብርና)<br>• ተውሳከ ግሶችን ተጠቅመው አረፍተ ነገር ይጽፋሉ፤ | **ማዳመጥ( ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት)**<br>ምንባብን አዳምጥው ግንዛቤያችወንና ስሜታችውን በሚና ጨዋታ መልክ ማቅረብ፤<br>**ማንበብ**<br>አንብበው የምንባቡን መልዕክት አሳጥሮ ማቅረብ<br>**መጻፍና ሰዋሰው**<br>የተሰጡትን ተውሳከ ግስ ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን መጻፍ | የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የእርሻ መዝሙር ማዘጋጀት፤(በሬድዮ ወይም በቪዲዬ መቅረጽ ትችላለህ)ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ በማደራጀት አንዱን ነጋዴ ሌላውን ገበሬ በማድረግ የሚፈልጉትንእንዲጠይቁ ( ለምሳሌ ገበሬው  እህሉን ሸጠ ነጋዴው ደሞ ሊገዛ ፈለገ)<br>**መምህር** በቅድሚያ ድምጽን ከፍ አድርገው ማንበብ ፤ ከዚያም ተማሪ እንዲሳተፍ ማድርግ፤ አረፍተነገር እንዴት እንደሚመሰረት ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎቹ የራሳቸውን አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ማበረታታት | ተማሪዎች እንዲዘምሩ ማበረታታት(መጀመሪያ አዳምጠው የመዝምሩን ግጥም እንዲረዱ ማድረግ)፤ በሚና ጨዋታ ውስጥ ያሏችውን ተሳትፎ በመገምገም ለተሳትፏቸው ማበረታቻ ማድረግ፤ ሲያነቡ የተሳሳቱባቸውን ቦታዎች እራሳቸው እንዲያስተካክሉ ማድርግ፡፡ ደብተራቸውን ማየትና ግብረ መልስ መስጠት፡ ፡ |

**ምዕራፍ ሰምንት፡- ስራ (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ከምንባቡ ውስጥ የተነሱትን ጉዳዮች አዳምጠው ይተገብራሉ፤
- ምንባቡን አንብበው አንድምታዊ ፍቺዎችን ይሰጣሉ፤
- የወደፊት እቅዳችወን ይጽፋሉ( ምን መሆን እንደሚፈልጉ )
- ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፤
- በአረፍተ ነገር አመሰራረት ውስጥ ተዛማጅ አረፍተነገሮችን ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ ፡<br>• ምንባቡን አዳምጥው ለቀረበት ጥያቄዎች በቃል መልስ መስጠት፤<br>• በክፍሉ ደረጃ ያሉትን ምንባቦች በግል አንብበው ተዛማጅ መልዕክቶችን መስጠት፡<br>• የወደፊት እቅዳችወን መጻፍ፤ (ካደጉ በኋላ ምን መሆን እንደሚፈልጉ)<br>• የቃላትን ፍቺ ምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መስጠት | **ማዳመጥና መናገር**<br>ምንባቡን አዳምጠ በየተራ መናገር<br>**ማንበብ**<br>ምንባብን በግል አንብቦ ዋናውን ሀሳብ ማውጣት፡፡<br>**መጻፍ**<br>የወደፊት እቅዳችወን መጻፍ<br>**ስዋሰው**<br>አያያዝ ቃላት | መምህርበማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ማዘጋጀትና በሰሌዳ ላይ መጻፍ ከዚያ ምንባቡን ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ ከዚያም ተማሪዎቹ የተዘጋጁትን ጥያቄ በቃል እንዲመልሱ ማስቻለል፡<br><br>ተማሪዎች በረፍ ጊዜያቸው ምን እንደሚሰሩ እንዲናገሩ መጠየቅ(ምሳሌ በርፍት ጊዜ እቤትህ ሆነህ ምን ትሰራለህ?)<br>ከምንባቡ ጥያቄዎችን አዘጋጅና ተማሪዎቹ እያነበቡት እንዲመልሱ መስጠት ታማሪዎች በእረፍ ሰዓታቸው ዘወትር የሚሰችወን ስራዎች እንዲጽፉ መምራት<br>አያያዦችን ተጠቅመው የራሳችወን አረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ መምራት (ምሳሌ ይህን ወይም ያን፣ ይህንንም ያንንም)<br>ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን በቃላት ላይ እንዲያጣምሩ ማድረግ (ምሳሌ የ + ቤት የቤት) | የማዳመጥ ክሂላችወን ለመፈተሸ እንዲረዳህ መልሳችወን ማየት፤<br>ለማበረታታት ግብረ መልስ መስጠት፤<br>እንዲናገሩ ማበረታታት፤<br>ማንበባችወን ለማረጋገጥ እንዲረዳህ መልሶቻችወን ማየት፤<br>ተማሪዎቹ የጻፉትን በማየት ግብረ መልስ መስጠት አደረጃጀታችወን መሸተካከልና የተሳሳተ ቃል ከጻፉ ማረም ፤<br>በአረፍተ ነገር ውስጥ የአያያዦችን እንደምሳሌ መስጠት እና ተሳትፏችወን መመዝገብ፤<br>የተሰጣችወን ምሳሌ ተከትለው መስራት መቻላችን ማረጋገጥ |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡-ባህል (18 ክፍለ ጊዜ)**

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በምንባቡ ውስጥ የተነሱትን ጉዳዮች አዳምጠው ይተገብራሉ፤
- ምንባቡን እንብበው የቃላት አንድምታዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ተወስነው በተሰጧቸው ቃላት አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፤
- የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ፤
- መስተዋድዶችን ለይተው በአረፍተነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ፤

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• የእንቆቅልሽን ህግ ጠብቀው እንቆቅልሽ መጫወት (የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማዳበር)<br>• አጫጭር ምንባቦችን (ስለ ባህልበማንበብ የቃላትን አንድምታዊ ፍቺ መስጠት)<br>• የቃላትን ፍቺ እንአገባባቸው መስጠት<br>• መሪ ቃላት ላይ ተመስርተው አረፍተ ነገሮችን መጻፍ<br>• በአረፍተ ነገሮች ውስጥ መስተዋድዶችን መጠቀም | **ማደመጥና መናገር**<br>በእንቆቅልሽ ጨዋታ መሳተፍ፤<br>**ቃላትን ማንበብ**<br>ለአዳዲስ ቃላት እንድምታዊ ፍቺ ለመስጠት ምንባቦችን ማንበብ<br>**መጻፍ**<br>በመሪ ቃላት ላይ በመመስረት አረፍተ ነገሮችን መጻፍ (ባህላዊ ምግብ፣ ልማድ፣ እንቆቅልሾች) | ለእንቆቅልሽ ጥያቄና መልስ መስጠት<br>የእንቆቅልሽን ህጎች መንገር፤ በመጨረሻም ተራ በተራ እንዲጠያይቁ ማስቻል፡፡<br>የማዳመጥና የመናገርን ክሂል ስለሚያዳብሩ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት፡፡<br>ምንባብን በሚያነቡበት ጊዜ ለቃት እንድማታዊ ፍቺ እንዲሰጡ መርዳት፤<br>ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎች የራሳችውን አረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ ማድረግ(ምሳሌ ባህል፣ጥሩ ባህል አለን፡፡ ባህላዊ ምግብ (ኢትዮጵያዊያን በባህላዊ ምግባቸው ይታወቃሉ) በዚህ መሰረት የተሰጡትን ቃላት ተጠቅማችሁ ስሩ እንቆቅልሾች፣ ክብር… | በየቡድናቸው ሆነው ሁሉም ተማሪዎች መጠያየቃቸውን መልስ መስጠታችወን ማረጋገጥ፤<br>ሁሉም ተማሪ በተመሳሳይ ሰዓት ተሳትፎ ስለሚያደርግ መምህርየሁሉም ቡድኖች አባል መሆን ይጠበቅበታል)<br><br>ተማሪዎች ማንበብ መማራቸውን ለማረጋገጥ የተወሰኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br><br>የቃላት ፍቺ በመጠየቅ ያሳዩትን ለውጥ መገምገም<br><br>ተማሪዎች የመሰረቷቸውን አረፍተ ነገሮች ማረም |

**ምዕራፍ አስር፡- ገበያ** (18 ክፍለ ጊዜ)

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-ይህን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ፡-

- ምንባቡን አድምጠው ስሜታቸውን ይገልጻሉ፤
- ምንባቡን አንብበው ዋናውን ነጥብ ይገልጻሉ፡
- ከምንባቡ የወጡትን ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ጥገኛ መስተጻምርን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፤

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ፡-<br>• ምንባቡን አዳምጠው ስሜታችወን መግለጽ፤<br>• የተሰጣቸውን ምንባብ አንብውወ ዋና ሀሳብ መጻፍ፤<br>• ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቺ መስጠት፤<br>• በአረፍተ ነገር አመሰራረት ውስጥ ጥገኛ መስተጻምርን መጠቀም | **ማዳመጥና መናገር**<br>በግገርና በሽያጭ ላይ ጭውውት ማድረግ<br><br>**ማንበብና ቃላት**<br>አንቀጽ በአንቀጽ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመለየት የአሰሳ ንባብ ማድረግ<br>**መጻፍና ሰዋሰው**<br>ጥገኛ መስተጻምር | ገገርና ሻጭ ሆነው እንድጫወቱ ተማሪዎችን በጥንድ ማደራጀት፤ ከዚያም ጭውውት ወይም ሚና ጨዋታ እንዲያደርጉ ማዘዝ፡ያም ማለት ጭውውትን እንደመሳሪያ በመጠቀም የማዳመጥና የመናገርን ክሂል ማዳበር፡፡<br>አውናዊውን ሀሳብ እንዲያገኙ ተማሪዎች ምንባቡን አንቀጽ በአንቀጽ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡<br>ጥገኛ መስተጻምሮችን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ተማሪዎችን መምራት (ምሳሌ እራቴን ዳቦ ወይም እንጀራ እበላለሁ፡፡<br>እቤቱ ውጪው ብቻ ሳይሆን ወስጡም እንደዚሁ ይቀባል፡፡<br>መምህር እንደ አካባቢያቸው የተለያዩ ምሳሌዎችን ሊሰጥ ይችላል፡ ፡) | ጭውውታቸውን ተከታትሎ ለድክመታቸው አስተያየት መስጠት፤ ለጥንካሬያቸው ማበረታታት፡፡<br><br>የንባብ ችሎታቸውን መሻሻሉን ማረጋገጥና ማበረታታት፡፡<br><br>ለጽሁፋቸው ግብረመልስ መስጠት፤ ወዲያውም ጥገኛ መስተጻምሮችን ተጠቅሞ አረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ማበረታታት፡፡<br><br>ለቃላት የሰጧቸውን ፍችዎች ማረም |